
456

# የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ታሪክ፡



ባጭር፡ ቃል፡ የወጣ፡

ከአለቃ፡ ታዬ፡

ታተመ፡ በሚሲኦን፡ ሱኤዶዋ፡ ማሕተሚያ፡ አስመራ

፲፱፻፲፬፡

www.ethiopianorthodox.org

# Abyssinian History

BY

ALEQA TAJE

SWEDISH MISSION ASMARA

1922

www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም ።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ መንግሥት፡ የነገሥታቱም፡ ታሪክ፡ ባጭር፡ ቃል፡ የሚነገር።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ መንግሥት፡ የነገሥታቱም፡ ታሪክ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ አሁን፡ ከተጻፈው፡ አጥኅተን፡ ዋና፡ ዋና፡ ነገሩን፡ በ፯፡ ክፍል፡ ከፍለን፡ በዚህ፡ እናሳያለን፡

ይህነንም፡ ታሪክ፡ በናወጣው፡ ከልብ፡ አንቅተን፥ ከሕሊና፡ አውጥተን፡ ልብ፡ ወለድ፡ የጻፍነው፡ አይደለም። ከመጻሕፍት፡ ቅዱሳት፥ ከቀድሞ፡ ሰዎች፡ ታሪክ፥ ከመሀከለኞች፡ ከኋለኞችም፡ ሊቃውንት፡ የታሪክ፡ መጻሕፍት፡ ተመልክተን፥ አርመን፥ አስማምተን፡ ያወጣነው፡ ነው፡ እንጂ።

የዚህ፡ ታሪክ፡ የሚገኘው፡ ከቅዱሳት፡ መጻሕፍት፡ ፩፡ ነገ፡ ፲፡ ፩ — ፲፫። ፪፡ ዜና፡ ፱፡ ፩ — ፲፪። ፲፬፡ ፩። ፴፡ ነገ፡ ፲፱፡ ፱። ኢሳ፡ ፵፯፡ ፱። ፪፡ ነገ፡ ፲፱፡ ፵፰ — ፵፯። ፪፡ ዜና፡ ፴፪፡ ፲፱ — ፳፫። ኢሳ፡ ፵፯፡ ፵፫ — ፵፯። ፪፡ ዜና፡ ፳፩፡ ፲፯ — ፲፯። ኤር፡ ፵፯፡ ፯ — ፲፫። ፵፱፡ ፲፯። ፵፯፡ ፱፡ — ፲። ሕዝ፡ ፴፰። ፩ — ፲። ዳን፡ ፲፩፡ ፵፫። ናሆም፡ ፫፡ ፯ — ፱። ዘፍ፡ ፲፡ ፲፫። ዘሁል፡ ፲፪፡ ፩ — ፲። ሶፎን፡ ፫፡ ፲። መዝ፡ ፷፯፡ ፴፡ — ፴፩። ፹፪፡ ፱ — ፲። ሮሜ፡ ፲፱። ግብ፡ ፰፡ ፳ — ፳። የሐዋ፡ ፳፡ ፳፯ — ፴፱። ልብ፡ አድርገህ፡ ተመልከት።

ይህን፡ ሁሉ፡ ምዕራፉንና፡ ቁጥሩን፡ አያወጣህ፡ ልብ፡ አድርገህ፡ ብትመለከት፥ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ ነገሥታት፡ በዚያ፡ የተናገረውን፡ ታገኘለህና፡ ትረዳለህ። ከቀድሞ፡ ሰዎች፡ ታሪክ፡ ያልነው፡ ከሙርታድ፥ ከግብጽ፥ አዙሮቴፕ፡ ነው።

ከሊቃውንት፡ የታሪክ፡ መጻሕፍት፡ ያልነው፡ ከብዙች፡ በጥቂቶች፡ ከግሪክ፡ ፕሮፌሶሮች፡ ከአሚሮስና ከሄሮዶቱስ፥ ከእንግሊዝ፡ ፕሮፌሶር፡ ከጀምስ፡ ብሩስ፥ ከፈረንግ፡ ሊቃውንት፡ ከሻንፓሊዮንና፡ ከምሬዮ፥ ከጀርመን፡ ሊቃውንት፡ ከኢዮብ፡ ልደልፍና፡ ከኢዘንበርግ፡ ከአስትራሮን፥ ከፃዐስንጀር፡ ዌርኔር፥ ከፕሮፌሶር፡ ሊትማን፥ ከኢጣሊያን፡ ሊቃውንት፡ ከዲማርቲኒስ፡ ጂ፥ ከጎምኒ፡ ኤሊ፥ ከጎትራቤርሲ፥ ከኤሊ፡ ቢዘኔ፥ ከጉኢዲ፡ ኢግናጥዮስ፥ ከምስር፡ ወይም፡ ከዓረብ፡ ሊቃውንት፡ ከአዝርቅይ፥ ከግብጽ፡ ሊቃውንት፡ ከኢደብሮ፡ ይስሐቅ፡ ከአበልዝና፡ ከአፈልፈረግ፡ ከየመን፡ ታሪክ፥ ከመጽሐፈ፡ አስክንድር፥ ከዮሐንስ፡ መድብር፥ ከጊዮርጊስ፡ ወልደ፡ አሚድ፡ በዘዋይ፡ ከተገኙ፡ የጥንት፡ ታሪክ፥ ከቀድሞው፡ ክብረ፡ ነገሥት፥ ከነዚህም፡ የሚበዛ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ታሪክ፡ ተቀብለን፡ ተለቅመን፡ ድርሶ፡ የወጣ፡ ነው።

ታሪክ፡ መማርና፡ ማወቅ፡ ለብዙ፡ ነገር፡ ይጠቅማል። መጀመሪያ፡ የድንቁርና፡ ዕውርነት፡ ዓይን፡ ይከፈታል። ሁለተኛ፡ በሰው፡ የእግዚአብሔርን፡ ሁሉን፡ ቻይነት፡ የፈጥረትንም፡ ብዛትና፡ የልዩ፡ ልዩ፡ ወገንንም፡ ዓይነት፡ የዓለምንም፡ ታላቅነትና፡ በፊት፡ ያይበታል።

ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ ዘመን፡ ከተቈጠረ፡ እስከ፡ ዘመን፡ የሆነውን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ቢማር፥ ጥንት፡ እንደ፡ ተፈጠረ፥ አስቀድሞ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ሁኖ፡ ያውቃል።

በዓለም፡ ያሉን፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ሕዝቡ፡ አገሬቸውንና፡ ጠባያቸውን፡ የአምልኮታቸውን፡ የመንግሥታቸውን፡ ሥራትና፡ አኗኗሮዋቸውን፡ በታሪክ፡ ቢመለከት፡ ቢመረምር፡ ቢያስተውልም፥ በቤቱ፡ ተቀምጦ፡ ዓለም፡ ሁሉ፡ ዞሮ፡ መርምሮ፡ እንዳየ፡ ሰው፡ ይሆናል።

የሰውን፡ ደግነትንና፡ ብርታትን፥ በጎነትንና፡ ክፋትን፥ በንፍገትንና፡ ብልሃትን፥ ሐሰትንና፡ እውነት፥ ቁም፡ ነገርንና፡ ጥረትን፥ ተንኮልንና፡ ቅንነትም፡ ያለበትን፡ ነገር፡ ሁሉም፡ እይቶ፡ ያውቃል። ላገሩና፡ ለመንግሥቱ፡ የሚጠቅመውን፡ ለማድረግ፡ ይተጋል። በዓለም፡ የሚደረገውን፡ ከንቱነት፡ ሁሉ፡ ይንቃል፡ ለበጎ፡ ነገርም፡ ይተጋል። የሰውም፡ ጠባይ፡ ደግምነትም፡ አውቆ፡ ልቡን፡ በማስፋት፡ ይታገሣል፥ ክፉ፡ ነገርንም፡ እየተው፡ ለበጎ፡ ነገር፡ ይነሣሣል። በለቱም፡ ወደፊት፡ በውቀትና፡ በብልሃት፡ በበጎነትም፡ ልቡ፡ ይታደጋል። በነፍቅንም፡ በምክሩና፡ በትምርቱ፡ ከድንቁርና፡ ወደ፡ ጥበብ፡ ይመልሳል። እንደሁም፡ አገሩንና፡ መንግሥቱን፡ ያደረጀልና፡ ያስፋል።

www.ethiopianorthodox.org

## ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዘር፡ ከምን፡ ትውልድ፡ እንደሆነ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ሕዝቦችም፡ በውስጥዋ፡ እንዳለበት፡ የሚያሳይ።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ መንግሥት፡ በዋናው፡ ነገር፡ ባራት፡ ክፍል፡ ይከፈላል፤ ነገደ፡ አሬት፥ ነገደ፡ ካም፡ ወይም፡ ነገደ፡ ኩሳ፡ ነገደ፡ ሴም፡ ወይም፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ ነገደ፡ እስራኤል፡ ናቸው።

ይህን፡ ስለ፡ አልን፡ የሕዝቡንና፡ የመንግሥቱን፡ ዋና፡ ዋና፡ የሆነ፡ ዓይነተኛውን፡ ክፍል፡ መናገራችን፡ ነው፡ እንጂ፡ በዝርዝሩ፡ ግን፡ በየዘመኑ፡ ከእስያ፡ እየፈለሱ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የገቡ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ሕዝቦች፡ እጅግ፡ ብዙች፡ ናቸው።

ከነዚህም፡ በስማቸው፡ የታወቁ፡ በየወገናቸው፡ በአምልኮ፡ በቋንቋ፡ በሥርዓትም፡ የተለያዩ፡ ናቸው።

ደግሞ፡ ጥቂቶች፡ ከምን፡ ዘር፡ እንደሆኑ፡ የማይታወቁ፡ በየጊዜው፡ ገብተው፡ የኋለኞች እየስለቀቀዋቸው፥ በኢትዮጵያ፡ ዳር፡ ለዳር፡ የሚኖሩ፡ አሉ። እነዚህም፡ በጣም፡ ስማቸውና፡ ነገዳቸው፡ ያልታወቁ፡ በመልካቸውና፡ በግብራቸው፡ የካም፡ ዘሮች፡ የከነዓን፡ ልጆች፡ ይመስላሉ።

---

### ፩፡ ነገደ፡ አሬት።

ከሁሉ፡ በፊት፡ አስቀድመው፡ በመጀመሪያ፡ ከእስያ፡ ተነሥተው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የገቡ፡ አገሪቱን፡ ይዘው፡ የነበሩ፡ ነገደ፡ አሬት፡ የተባሉ፡ ናቸው። የነዚህም፡ አበት፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ ከገጽ፡ ፵፡ እስከ፡ ፶፡ እንዳሳየነ፡ ከአዳም፡ ልጆች፡ አንዱ፡ አሬ፡ ወይም፡ አራም፡ የተባለው፡ ነው። እርሱ፡ ከ፩፡ ሺ፡ ፴፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ጀምሮ፡ ከነልጆቹ፡ ልጆቹ፡ ፳፩፡ ነገሥታት፡ እስከ፡ ፪፡ ሺ፡ ፪፻፶፮፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ፩ሺ፡ ፪፻፳፮፡ ዓመት፡ በኢትዮጵያ፡ ነገሡ። በመጨረሻው፡ ንጉሣቸው፡ በሶሊማን፡ ታጊ፡ ጊዜ፡ በኖህ፡ ዘመን፡ በጥፋት፡ ውሃ፡ ተደመሰሱ፥ አለቁ። የነዚህን፡ ሕዝብና፡ ነገሥታት፡ ታሪክ፡ ባዲሱ፡ ክብረ፡ ነገሥት፡ ከገጽ፡ ፫፻፲፯፡ እስከ፡ ፫፻፴፫፡ ተመልከት።

www.ethiopianorthodox.org

እነዚሁ፡ ሕዝብ፡ በማየ፡ አይኅ፡ ከጠፉ፡ ወዲህ፡ የኢትዮጵያ፡ አገር፡ ምድርም፡ ሁሉ፡ ከጥፋት፡ ውሃ፡ እስከ፡ ባቢሎን፡ ግምብ፡ መፍረስ፡ በቋንቋ፡ ተለያይተው፡ እስከ፡ ሰዎች፡ መበታተን፡ ፫፻፴፩፡ ዓመት፡ ከሆነ፡ ኢትዮጵያ፡ ሰው፡ የሌለበት፡ ባዶ፡ ነበረች። ከዚህ፡ በኋላ፡ ነገደ፡ ካም፡ መጡና፡ ወረሱዋት።

## ፩ ነገደ፡ ካም።

ካም፡ ከእስያ፡ በባብ፡ ኤልማንደብ፡ ተሻግሮ፡ መጥቶ፡ በኢትዮጵያ፡ ገባ። ይህም፡ የሆነ፡ በ፫ሺ፪፻፹፯፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ፪ሺ፪፻፲፫፡ ዓመት፡ ከጌታችን፡ ከየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ ነው።

ካም፡ በኢትዮጵያ፡ ፫፻፡ ዓመት፡ ገዝቶ፡ እንደገና፡ ወደ፡ እስያ፡ ሄዶ፡ ሰርያንም፡ አይዛለሁ፡ ብሎ፡ ከሴም፡ ልጆች፡ ጋራ፡ ተዋግቶ፡ በጦር፡ ሞተ። ልጆቹ፡ ግን፡ ታላቅ፡ ወንድማቸውን፡ ኩሽን፡ በላያቸው፡ አንግሠው፡ ኢትዮጵያን፡ ወረሱ። ነገደ፡ ካም፡ እስከ፡ የልጅ፡ ልጆቻቸው፡ ሽሬ፡ ነገሥታት፡ ከ፫ሺ፪፻፹፯፡ እስከ፡ ፫ሺ፭፻፲፰፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ፪፻፴፩፡ ዓመት፡ ነግሠው፡ ኢትዮጵያን፡ ገዙ። ከብር፡ ነገሥት፡ ከገጽ፡ ፫፻፵፫፡ እስከ፡ ፫፻፵፬፡ እዩ።

በነገደ፡ ካም፡ ወይም፡ በነገደ፡ ኩሳ፡ መንግሥት፡ ዘመን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ስለ፡ ገቡ፡ ሕዝብ፤

በነዚሁ፡ በነገደ፡ ኩሳ፡ መንግሥት፡ ዘመን፡ መካከል፡ ፫፡ ነገዶች፡ በየጊዜው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ። እነርሳቸውም፡ ነገደ፡ ሻንቅላ፡ ነገደ፡ ቅማንት፡ ነገደ፡ ወይጦ፡ ናቸው። ወንድማቸው፡ ሐማቲ፡ ሁሉም፡ የከነዓን፡ ልጆች፡ ናቸው። የነዚህም፡ ነገዶች፡ አባቶች፡ ሲኒ፡ አርዋዲ፡ ሳምራ፡ ናቸው። ፬ተኛ፡ ወንድማቸው፡ ሐሜቲ፡ የሱ፡ ልጆች፡ በኋላ፡ በነገደ፡ አግናዝያን፡ ዘመን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ።

ሲኒ፡ የሻንቅሎች፡ አርዋዲ፡ የቅማንቶች፡ ሳምራ፡ የወይጦች፡ ሐማቲ፡ የሽናሾች፡ አባቶች፡ ናቸው።

የሲኒ፡ ልጆች፡ በእስያ፡ ሲኖሩ፡ መልካቸው፡ እንደ፡ እስያ፡ ሰዎች፡ ነበሩ። በፊት፡ ወደ፡ አፍሪቃ፡ ከመጡ፡ ሻንቅሎች፡ ጋራ፡ ቢቀላቀሉ፡ በመጋባትም፡ ባገሩ፡ አየርም፡ እንደ፡ ሻንቅሎች፡ ጥቁሮች፡ ሆኑ። በፊት፡ በታችኛው፡ ኢትዮጵያ፡ በሱዳን፡ በኑቢያ፡ ይኖሩ፡ ነበር። በኋላ፡ ወደ፡ ደጋይቱ፡ ኢትዮጵያ፡ ወጡ።

www.ethiopianorthodox.org

እኒሁ፡ የሲኒ፡ ልጆች፡ ከሻንቅሎች፡ ጋራ፡ በመቀላቀል፡ ነው፡ ጥቍሮች፡ የሆኑ። ከሲዮኒ፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ በነገሠች፡ በ፫ተኛው፡ ዓመት፡ በ፫ሺ፫፻፱፡ ዓለም፡ በ፩ሺ፬፻፺፩፡ ዓመት፡ ከልደት፡ በፊት፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ። ብዙ፡ ሕዝብ፡ ሁነው፡ ወጡና፡ ከብታቸውን፡ ይዘው፡ ከጭልጋ፡ አፋፍ፡ እስከ፡ በሽሎ፡ አፋፍ፡ ሰፈሩ። ሰፈሩ፡ ስንል፡ በታ፡ እያዩ፡ ተሰማሩ፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ፡ ከጭልጋ፡ እስከ፡ በሽሎ፡ አፋፍ፡ አንድነት፡ ሰፈሩ፡ ማለት፡ አይደለም።

እኒህም፡ ሻንቅሎች፡ ከብት፡ ከመጠበቅ፡ ሥጋና፡ የዱር፡ ፍሬ፡ ከመብላት፡ በቀር፡ ቤት፡ መስራት፡ እህል፡ መዝራት፡ ሌላም፡ የሚጠቅም፡ ስራ፡ አያውቁም፡ ነበሩ። ዋሻ፡ ታላቅ፡ ደንጊያ፡ ያገኙ፡ ከዋሻ፡ ከደንጊያ፡ ተጠጉ። ያላገኙ፡ የቅጠል፡ ጎጆ፡ አድርገው፡ ተቀመጡ። ከብታቸውን፡ ይዘው፡ ሣር፡ ወዳለበት፡ እያዩ፡ ሲሰፍሩና፡ ሲያበሉ፡ ሲዞሩ፡ ይኖሩ፡ ነበሩና፡ ለጊዜው፡ ለነገድ፡ ኩሉ፡ መንግሥት፡ ገበሩ። ቀምበር፡ በከበዳባቸው፡ ጊዜ፡ ግን፡ ብርቱ፡ ጠብ፡ ተጣሉ፡ ጽኑ፡ ውጊያም፡ ተዋጉ። ድል፡ ሲያደርጉ፡ አንዳንድ፡ ጊዜም፡ ድል፡ ሲሆኑ፡ ሲታረቁ፡ ሲሸፍቱም፡ ሲገብሩ፡ እምቢ፡ ሲሉም፡ ሻንቅሎችንም፡ ነገደ፡ ኩሳንም፡ የኋለኞች፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ አበቶች፡ በነገደ፡ ሴም፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ አግናዝያን፡ ሁሉንም፡ አስለቀቀው፡ ወደ፡ ታችኛው፡ ኢትዮጵያ፡ ቆላ፡ በረሃ፡ እስኪያሳድዋቸው፡ ድረስ። ሻንቅሎች፡ ፬፻፵፯፡ ዓመት፡ በደጋይቱ፡ ኢትዮጵያ፡ ተቀመጡ። ከብ፡ ነገ፡ በገጽ፡ ፻፲፬፡ እስከ፡ ፻፲፮፡ እይ።

---

## ፫፡ ነገደ፡ ቅማንቶች።

ሖር፡ በነገሠ፡ በ፲፫፡ ዓመት፡ በ፫ሺ፯፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ፪ሺ፬፻፲፡ ከልደት፡ በፊት፡ የአርዋዲ፡ ልጅ፡ የከነዓን፡ የልጅ፡ ልጅ፡ አይነር፡ የቅማንቶች፡ አባት፡ ተከነዓን፡ አገር፡ ተሰዶ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገባ። የከንዓን፡ ልጅ፡ አርዋዲ፡ ፯፡ ወለደ። ከ፯ቱ፡ አንዱ፡ አይነር፡ የተባለው፡ ምሽቱን፡ እንተላን፡ ይዞ፡ ከወንድሞቹ፡ ተለይቶ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ወጣ፡ ፯ቱ፡ ወንድሞቹ፡ ግን፡ በአስያና፡ በምድረ፡ ግብጽ፡ ተበታትነው፡ ቀሩ። ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የወጣው፡ አይነር፡ በምድረ፡ እስያ፡ በከነዓን፡ አገር፡ ረሃብ፡ በጸና፡ ጊዜ፡ ከወንድሞቹና፡ ከወገኖቹ፡ ተለይ

www.ethiopianorthodox.org

ቶ፡ ምሽቱን፡ እንተላን፡ ይዞ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ወጥቶ፡ ሰው፡ ሳያየውና፡ ሳያውቀው፡ በከርከር፡ ዱር፡ በረሃ፡ እንስሳ፡ አድኖ፡ የዱር፡ ፍሬ፡ ለቅሞ፡ እየበላ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ተቀመጠ። ሰው፡ ሳያየውና፡ ሳያውቀው፡ ብዙ፡ ዘመን፡ በዱር፡ ስለ፡ ተቀመጠ፡ የቅማንቶችን፡ አባት፡ እንጨት፡ ወለደው፡ የእንጨት፡ ፍሬ፡ ነው፡ ከእንጨት፡ የተገኘ፡ ነው፡ የሚሉ፡ አሉ። ነገር፡ ግን፡ በዚህ፡ ነገራቸው፡ ከንቱ፡ የሐሰት፡ ተረትን፡ ያጫውታሉ፡ እንጂ፡ የውነት፡ ነገር፡ አይደለም። የሰው፡ ሁሉ፡ ምንጭና፡ አባት፡ አዳም፡ እንደሆነ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ይነግረናል። ዘፍ፡ ፩፡ ፳፮ — ፳፰፡ ፬፡ ፩፡ ፪፡ ፭—፴፪፡ ተመልከት። ጥቂት፡ ተማርን፡ መጽሐፍ፡ መረመርን፡ የሚሉ፡ ግን፡ ስለ፡ ቅማንቶች፡ ትውልድ፡ ሲተርኩ፡ እንዲህ፡ ይላሉ፡ በኢያሱ፡ ወልደ፡ ነዌ፡ ዘመን፡ ኢያሱንና፡ የእስራኤልን፡ አለቆች፡ በቅርብ፡ ሳሉ፡ የሩቅ፡ መስለው፡ አታለው፡ የማልዋቸው፡ ሰብአ፡ ገባዖን፡ በእስራኤል፡ ርስት፡ መከከል፡ ነበሩና፡ መሐላ፡ እንዳይፈርስባቸው፡ ሳያጠፉዋቸው፡ ለሕዝቡ፡ ሣር፡ አጫጅ፡ እንጨት፡ ለቃሚ፡ አደረጓቸው። ለልጅ፡ ልጅ፡ የእስራኤል፡ ዜጎች፡ ሆኑ። ኢያሱ፡ ፱፡ ፫—፳፯። ከዚህ፡ በኋላ፡ በሰሎሞን፡ ጊዜ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ሲመጣ፡ አብረው፡ የመጡ፡ ናቸው፡ በጥንት፡ ግብራቸው፡ ንጉሥ፡ በሚኖርበት፡ ከተማ፡ በዜግነት፡ ሣር፡ እያጨዱ፡ እንጨት፡ እየለቀሙ፡ ኖሩ፡ ሲሉ፡ ይተርካሉ። በጎንደር፡ ዙሪያ፡ ዜጎች፡ ሁነው፡ ተሠሩ፡ ይላሉ። ይሁንንም፡ በፍ፡ ብቻ፡ ይተርካሉ፡ እንጂ፡ የተጻፈ፡ ቁም፡ ነገር፡ ታሪክ፡ የለም።

ይህ፡ ሁሉ፡ ግን፡ ይወለደዋል፡ ከተባለ፡ ይመስለዋል፡ ማለት፡ አይገድምና፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ የሰሎሞን፡ ልጅ፡ ከሆነ፡ ሰብአ፡ ገባዖንም፡ የእስራኤል፡ ዜጎች፡ ከሆኑ፡ ብሎ፡ በምክንያት፡ ነገር፡ አስመስሎ፡ ማጫወት፡ ነው፡ እንጂ፡ ለልብ፡ የሚረዳ፡ እውነተኛ፡ ታሪክ፡ አይደለም። ምነው፡ ቢሉ፡ እኒህ፡ ቅማንቶች፡ በአምልኮት፡ በቋንቋ፡ በወገን፡ የተለዩ፡ አረማውያን፡ ሕዝብ፡ ከቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ እስከ፡ አጼ፡ ፋሲል፡ መንግሥት፡ ፪ሺ፮፻፸፱፡ ዓመት፡ ያህል፡ ሲቀመጡ፡ ጎንደር፡ ከተሠራ፡ ፫፻፹፱፡ ዓመት፡ ነው። ከዚያ፡ በፊት፡ ከኢትዮጵያ፡ አገሮች፡ ነገሥታት፡ በሚከትሙበት፡ አጠገብ፡ የት፡ የት፡ ተሠርተው፡ ነበር፡ ብለን፡ ለመጠየቅ፡ ግድ፡ ነው። የቅማንቶች፡ መኖሪያ፡ በከርከር፡ በጭልጋ፡ በጋላ፡ አገር፡ በበባ፡ በከሶጌ፡ በጀኒ፡ ፈንቀራ፡ ለዙሪያት

www.ethiopianorthodox.org

ውም፡ ባሉ፡ አገሮች፡ ነው። ይህ፡ ሁሉ፡ አገርስ፡ አጼ፡ ፋሲል፡ የጎንደርን፡ ከተማ፡ ሳይቈረቍሩ፡ በፊት፡ አስቀድሞ፡ የክርስቲያን፡ ሕዝብ፡ አልነበረበትምን፡ ወይስ፡ አጼ፡ ፋሲል፡ ክርስቲያኑን፡ ነቅለው፡ አገሩን፡ ለቅማንት፡ ሰጡትን፡ ብለን፡ ለመጠየቅ፡ ግድ፡ ነው። ለዚህ፡ ጥያቄ፡ እናውቅም፡ ተማለት፡ በቀር፡ ሌላ፡ ምላሽ፡ አይገኝለትም።

እኛ፡ ግን፡ እኒህን፡ አሁን፡ የተቈጠሩትን፡ የቅማንት፡ አገሮች፡ ቀንት፡ ከመሠረት፡ አገራቸው፡ እንደ፡ ነበረ፡ በኋላ፡ ግን፡ በዘመን፡ ክርስትና፡ የክርስቲያን፡ ነገሥታት፡ ቅማንትን፡ የክርስቲያን፡ ዜጋ፡ አድርገው፡ በላያቸው፡ ሥራ፡ እንደሰሩባቸው፡ በገራቸውም፡ መሀከል፡ ጉልተኛ፡ ሁኖ፡ ክርስቲያን፡ እንደ፡ ገባባቸው፡ በገራቸውም፡ ሁሉ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ እንደ፡ ተሠሩባቸው፡ እናውቃለንና፡ ብዙች፡ ታሪክ፡ ጸፎች፡ እንደሚሉ፡ የቅማንቶች፡ አባት፡ አይነር፡ በፊት፡ እንደመጣ፡ አገርንም፡ ይዞ፡ እንደነበረ፡ ነገራችንን፡ በዚህ፡ እናጸናለን።

አይነር፡ ከምሽቱ፡ ከአንተላ፡ ፱፡ ወንዶች፤ ፫፡ ሴቶች፡ ወለደ። ስማቸውም፡ እኒህ፡ ናቸው፡ ክብርዋ፡ አይደረኪ፡ እንግሚ፡ ነዚ፡ ይዘና፡ በእቴ፡ ዳዮን፡ ሸመኒ፡ ከደሴተ። የሴቶች፡ ስማቸው፡ ይህ፡ ነው፡ ውሽን፡ እቴቴ፡ ፍርዳቀን፡ ኒማልጊን፡ ይባሰስ። እኒህ፡ ፳፪፡ ሁሉ፡ ባል፡ ሳያገቡ፡ በድንግልና፡ ሞቱ፡ ይላል። ይባዕስ፡ ከሁሉ፡ የበለጠች፡ ታላቅ፡ ሰው፡ ነበረች፡ ይላሉ።

የክብርዋ፡ መኖሪያ፡ በጃኒ፡ ፈንቀራ፡ ሰራኩ፡ ሰገር፡ በሚሉት፡ አገር፡ ነው። አይደረኪ፡ መኖርያው፡ በከርከር፡ ነው። አይደረኪን፡ ቅማንቶች፡ አከበርነው፡ ብለው፡ አባት፡ እናት፡ የለውም፡ ከሰማይ፡ የወረደ፡ ነው፡ ይሉታል። ነገር፡ ግን፡ ይህ፡ ተረት፡ ይቅርና፡ ያለ፡ ጥርጣሬ፡ የአይነር፡ ልጅ፡ ነው።

እንግሚ፡ ነዚ፡ ይዘና፡ ሸመኒ፡ ከደሴቲ፡ የከርከር፡ ቅማንቶች፡ አባቶች፡ ናቸው፡ ዲዮን፡ የጭልጋ፡ ቅማንቶች፡ አባት፡ ነው፡ በእቴ፡ የጋላ፡ አገር፡ ቅማንቶች፡ አባት፡ ነው።

እንበቢ፡ ሆይ፡ ጋላ፡ አገር፡ ማለት፡ ጋላ፡ ቤት፡ ሁሉ፡ አይምሰልህ፡ በጭልጋና፡ በጋበ፡ አጠገብ፡ ያለ፡ አገር፡ ነው። ትንከበሊ፡ የበእቴ፡ ልጅ፡ ብጋበ፡ የሚኖሩ፡ ቅማንቶች፡ አባት፡ ነው። የቅማንቶች፡ ትውልድ፡ ማዕርግና፡ አምልኳቸው፡ ሥራትና፡ ሕጋቸው፡ እንዴት፡ እንደሆነ፡ ባዲሱ፡ ክብረ፡ ነግሥት፡ ገጽ፡ ፻፲፯፡ እስከ፡ ፻፴፡ ተመልከት።

---

www.ethiopianorthodox.org

## ፩፡ ነገደ፡ ወይጦ።

ከኩሳ፡ የልጅ፡ ልጆች፡ ሰበ፡ ዕኛ፡ የሚባል፡ ንጉሥ፡ በነገሠ፡ በ
፲፫፡ ዓመት፡ በ፫ሺ፻፵፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ፪ሺ፫፻፫፡ ዓመት፡ ከልደት፡ በ
ፊት፡ ነገደ፡ ወይጦ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ። ስማቸው፡ በበታቸው፡
ስም፡ ዋቶ፡ ነው። ከዋቶ፡ እያደረ፡ ወደ፡ ወይጦ፡ ተመለሰ። ስምሪ፡ ዋ
ቶን፡ ወለደ፡ ዋቶ፡ የወይጦች፡ አባት፡ ነው።

መጀመሪያ፡ በ፫ሺ፻፵፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በምስርና፡ በሱዳን፡ አገር፡
ብርቱ፡ ርሃብ፡ ሆነ። የዚያን፡ ጊዜ፡ የዋቶ፡ ነገድ፡ ወይጦች፡ በበያ፡ መ
ንገዝ፡ ለመንገዝ፡ እየሄዱ፡ አዘውን፡ ጉማሬውን፡ ዶብራውን፡ ጋጋኖውን፡
ሌሎችንም፡ አእዋፍ፡ ዓሣውንም፡ እየበሉ፡ እስከ፡ ኢትዮጵያ፡ መ
ጡ፡ ተከፍለው፡ በጣና፡ በሐር፡ ዙሪያ፡ ተቀመጡ። ተከፍለው፡ ግን፡
ወደ፡ ከፋ፡ ሄዱ፡ በጋላ፡ አገርም፡ ተቀመጡ። በጋላ፡ አገር፡ በከፋ፡ ያ
ሉት፡ እስከ፡ ዛሬ፡ በበታቸው፡ በዋቶ፡ ስም፡ ዋቶ፡ ወይም፡ ዋታ፡ ይባላሉ።
በጣና፡ በሐር፡ ዙሪያ፡ ያሉ፡ ግን፡ በዘመን፡ ብዛት፡ ዋቶ፡ ተለውጦ፡ ወ
ይጦ፡ ተባሉ። ዳግመኛም፡ በኋለኛው፡ ዘመን፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ ወይም፡
ነገደ፡ አግዓዝያን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ በገቡ፡ ጊዜ፡ ከሌላው፡ ሕዝብ፡ ተ
ለይተው፡ በአምልኮ፡ የመይቀላቀሉ፡ ያገኙትንም፡ እንስሳ፡ ርኩስና፡
ቅዱስ፡ ሳይለዩ፡ ሁሉን፡ የሚበሉ፡ እንደሆኑ፡ አይተው፡ እኒህ፡ ምን፡
ዓይነት፡ ሕዝብ፡ ናቸው፡ ብለው፡ ጠየቁ። ዋቶ፡ ይባላሉ፡ ያገኙት
ንም፡ ሁሉ፡ ይበላሉ፡ አልዋቸው። ነገደ፡ አግዓዝያንም፡ የኒህስ፡ ስማቸ
ው፡ ዋቶ፡ አይደለም፡ ያገኙትን፡ ሁሉ፡ የሚበሉ፡ የማይጸየፉ፡ ናቸ
ውና፡ ስማቸው፡ ውሒጦ፡ ነው፡ አሉ። ስለዚህም፡ በዚያ፡ ዘመን፡ ው
ሒጦ፡ ተባሉ። ውሒጦ፡ ማለትም፡ ዋጪ፡ ማለት፡ ነው። ከዘመን፡ ብዛ
ት፡ ግን፡ ውሒጦ፡ እያደረ፡ ተለውጦ፡ ወይጦ፡ ተባለ፡ ይላሉ። በፊት፡ እ
ንዳልነ፡ ወይጦ፡ የተባሉ፡ በጣና፡ በሐር፡ ዙሪያ፡ ያሉ፡ ናቸው። በጋላና፡
በከፋ፡ ያሉ፡ ግን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ዋታ፡ ይባላሉ።

ሁለተኛ፡ በምስርና፡ በሱዳን፡ አገር፡ ያን፡ ጊዜ፡ ተከፍለው፡ ቀርተ
ው፡ የነበሩ፡ ወይጦች፡ ወንድሞቻቸው፡ ደግሞ፡ ከስጋዌ፡ በኋላ፡ በ፮፻፵፡
ዓመት፡ ለትም፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ በነገሠ፡ በ፲፡ ዓመት፡ ወደ፡ ኢ
ትዮጵያ፡ መጡና፡ በጣና፡ በሐር፡ ዙሪያ፡ ከሚኖሩ፡ ወንድሞቻቸው፡
ተቀላቀሉ። ከነሱም፡ የእስላሞችን፡ ነቢይ፡ መሐመድን፡ ወሬ፡ ሰምተ
ው፡ መሐመድ፡ የአላህ፡ ነቢይ፡ ነው፡ ብለው፡ ተቀበሉ፡ አመኑም።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ፡ እንዶት፡ ሞላችሁ፡ ሲልዋቸው፡ አልሐምዱ ሊላ፡ ይላሉ። ሙስባሐም፡ በንግታቸው፡ ያሰራሉ፡ ቍርዓንን፡ ግን፡ አይቀበሉምና፡ እንደ፡ እስላም፡ መስጊድና፡ መጸም፡ ጸሎትም፡ አያውቁም። መሐመድ፡ የአላሁ፡ ነቢይ፡ ነው፡ ብለው፡ አምነው፡ ቍርዓንን፡ የማይቀበሉበትን፡ ምክንያት፡ ምን፡ እንደሆነ፡ ቍርዓን፡ የከለከለውን፡ ሁሉም፡ የመብላታቸውን፡ ታሪክ፡ ለማወቅ፡ ብትሻ፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ ገጽ፡ ፻፴፩፡ እስከ፡ ፻፴፬፡ ስለ፡ ነገደ፡ ወይጦ፡ የተጻፈውን፡ አንብብና፡ ተመልከት።

## ፫፡ ነገደ፡ ሸናሽ።

የሸናሽ፡ መጀመሪያ፡ አባታቸው፡ ሐማት፡ ነው። ሐማት፡ ጉማን፡ ዠገትን፡ ጎንጋን፡ ዱራን፡ ወለደ። እነሆም፡ አራቱ፡ ወንድማማች፡ የሸናሾች፡ አባቶች፡ በዘመነ፡ አማዕዝያን፡ አይባ፡ ሁለተኛ፡ ስሙ፡ ሰቢዩና፡ የተባለ፡ በነገሡ፡ በ፳፱፡ ዓመት፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ። ይህም፡ የሆነ፡ በ፫ሺ፯፻፸፱፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ያዕቆብ፡ ወደ፡ ምስር፡ በገባበት፡ ዘመን፡ ፩ሺ፭፻፳፭፡ ዓመት፡ ከልደት፡ በፊት፡ ነው።

እኒህ፡ የነገደ፡ ሸናሽ፡ አባቶች፡ ከምድረ፡ ከነዓን፡ ርስትን፡ በጡ፡ ጊዜ፡ ከዚያ፡ ተሰደው፡ ወደ፡ ምድረ፡ ግብጽ፡ ገቡ። በምድረ፡ ግብጽም፡ እጅግ፡ ሀብታሞች፡ ሆኑ፡ የግብጾችንም፡ ጥበብ፡ ያስማትንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ተማሩ። ይህ፡ ሳይቀር፡ በዚያ፡ አንድ፡ ቃዳ፡ የሚሆን፡ መሬት፡ አልነበራቸውምና፡ ለከብታቸው፡ መሰማሪያ፡ ሰፍራ፡ አጡ። እርሰው፡ ዘርተው፡ እህል፡ አግብተው፡ የሚበሉበት፡ መሬትም፡ አላገኙም፡ ስለዚህ፡ በግብጽ፡ ሰዎችና፡ በነሣቸው፡ መሀከል፡ ሁልጊዜ፡ ጠብ፡ ክርክር፡ ሁከትም፡ ሆነ። ስለዚህ፡ ነገደ፡ ሸናሽ፡ በጠብና፡ በረሃብ፡ ምክንያት፡ ከምድረ፡ ግብጽ፡ ተሰደው፡ ብዙ፡ ሥራዊት፡ ሁነው፡ በባይ፡ ላባይ፡ ወንዝ፡ ለወንዝ፡ ወጥተው፡ በዳሞትና፡ በኩታይ፡ በሞሩ፡ መሀከል፡ በባይ፡ ወዲህ፡ ማዶና፡ ወዲያ፡ ማዶ፡ ሰፈሩ። ከዶጋው፡ ኢትዮጵያ፡ ተሰዶ፡ ባባይ፡ ወንዝ፡ ለወንዝ፡ ከቈላው፡ ተቀምጦ፡ የነበረውን፡ ሻንቅላ፡ ተዋግተው፡ ድል፡ አደረጉትና፡ አጠፉት፡ አገሩንም፡ ያዙት። ከሞት፡ የተረፈውን፡ ሻንቅላ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ የልጅ፡ ባሪያ፡ አድርገው፡ ገዙት። አገሩን፡ አራቱ፡ ነገድ፡ ተካፍለው፡ በየአባታቸው፡ ስም፡ ጠሩት። የጉማ፡ ልጆች፡ የተካፈሉትን፡ አገር፡ ባባታቸው፡ ስም፡ ጉማ፡

www.ethiopianorthodox.org

እሉት። የዝግት፣ ልጆችም፣ በባታቸው፣ ስም፣ ዝግት፣ አሉት። የጎንጋ፣ ልጆችም፣ በበታቸውም፣ ስም፣ ጎንጋ፣ አሉት። ባገሙ፡ ምድርና፡ በኑሮ ሳቸው፣ መለያየ፣ ባለው፡ ታላቅ፡ ወንዝ፡ ዳር፡ ያሉ፣ የዱራ፡ ልጆችም፡ ወንዙን፣ በባታቸው፣ ስም፣ ዱራ፣ አሉት። ይህም፡ ዱራ፣ የተባለ፡ ወንዝ፡ ያገሙ፣ ምድርና፡ የሸናሽ፣ የሻንቅላ፡ መለያያ፡ ነው።

ሸናሾች፡ ቀድሞ፣ በየነገዳቸው፣ የተማ፡ ልጆች፡ተማ፡የዝግት፣ ልጆች፡ ዝግት፣ የጎንጋ፡ ልጆች፣ ጎንጋ፡ የዱራ፣ ልጆች፡ ዱራ፣ ይባሉ፡ ነበሩ። ሸናሽ፡ ወይም፡ ሸናሻ፡ የሚለ፡ የጥቅል፡ ስም፡ አልነበራቸውም። አሁን፣ በቅርቡ፣ ያማራ፡ ሕዝብና፣ ቋንቋ፣ ከሰለጠነ፡ እጅግ፡ በዝተው፡ ቀድሞ፣ ሻንቅላን፡ ያጠፉትና፣ አጥቅተው፡ የያዙት፣ አገር፡ አልበቃቸው፣ ብሎ፣ ደግሞ፣ ወደላይ፣ ወጥተው፡ አገሙን፡ ዳሞትን፣ ይወጉ፡ ይዘርፉ፡ ነበሩና፡ ከዕለት፡ አንድ፣ ቀን፡ ጨኸት፡ ሸብር፡ ሆነ። ምን፣ ጨኸትና፣ ሸብር፡ ነው፡ ብለው፣ የዳሞት፣ ሰዎች፣ እርሰበርሳቸው፣ ቢጠያየቁ፡ እጅግ፡ ብዙ፡ ሸናሽ፡ የሆነ፡ ሕዝብ፡ ለጦርና፣ ለዘረፋ፣ መጣብን፣ አሉ። ስለዚህም፡ እነዚህ፣ ሕዝብ፣ ሸናሽ፡ ማለትም፣ በማሪኛ፡ ቋንቋ፡ እጅግ፣ ብዙ፣ ማለት፣ ነው።

ሸናሾች፣ አረማውያን፣ ናቸው፡ ዛሬ፡ ግን፣ በዳሞት፡ ደምበር፡ በጉመር፣ አጠገብ፡ በማቢቢል፡ በኩሉ፣ ያሉ፣ ክርስቲያኖች፡ ከሆኑ፡ ብዙ፣ ጊዜያቸው፣ ነው። ከዱራ፣ ወዲያ፣ ማዶና፣ በበይ፡ ዙሪያ፡ ያሉት፣ እስከ፣ ዛሬ፣ አረማውያን፡ ናቸው። አምልኳቸውም፣ እንደ፣ ጋላ፡ በወፍ፡ በሞራ፣ በዛፍ፡ በደንጊያ፡ በዛጎል፡ መጣል፡ በሙዋርተኝነት፣ ነው። የቀድሞ፣ አባቶቻቸው፡ ከምድረ፡ ግብጽ፡ አስማተኞች፣ እንደተማሩት፣ እስከ፣ ዛሬ፡ ብዙ፡ አስማተኞችና፣ ባለ፡ መድኃኒቶች፡ አሉ። ጽሬትና፣ መጻፍ፡ ግን፣ አያውቁም፣ የላቸውም። ከዚህ፡ የቀረን፡ የሸናሾችን፣ ሙሉ፣ ታሪክ፡ በኑብረ፡ ነገሥት፣ በገጽ፣ ፲፻፴፩፣ እስከ፣ ፲፻፵፫፡ ተመልከት።

## ፮፣ ነገደ፡ ዮቅጣን።

እኒሁ፡ ነገደ፣ ዮቅጣን፣ የሴም፡ የልጅ፣ ልጆች፣ ናቸው። ሴም፣ ፲፫፡ ልጆች፡ ወለደ። ከ፲፫ቱ፣ ፫ኛው፣ አርፋክሳድ፣ ነው። አርፋክሳድ፡ ቃይናንን፡ ወለደ፣ ቃይናንን፡ ሳላን፡ ወለደ፣ ሳላ፡ ዔቦርን፡ ወለደ፡ ዔቦር፡ ፋሌክንና፡ ዮቅጣንን፣ ወለደ። ዮቅጣን፡ በግዕዝ፡ ዮቃጤን፡ ባምርኛው፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ዮቅጣን፡ በወዲያ፡ አገር፡ መጽሐፍ፡ ዮቅታን፣ የካታን፣

www.ethiopianorthodox.org

ይበላል። ዮቅጣን፥ ፲፫፡ ልጆች፥ ወለደ፤ ስማቸውም፡ አልሞዳድ፥ ሣል
ፍ፥ ሀስረሞት፥ ያራሀ፥ ሀዶራም፥ አውዛል፥ ዶቅላ፥ ኡባል፥ ወይም፥ ኑባ
ል፥ አቢማኤል፥ ሳባ፥ አውፊር፥ ሀዊላ፥ ዮባብ፥ ናቸው። ዘፍጥ፥ ፲፥ ፳፭፡
፴፪። ስፍራውም፥ በእስያ፥ ምድር፥ ከሜሻ፥ እስከ፥ ሶፋር፥ እስከ፥ ምሥ
ራቅ፥ ተራራ፥ ድረስ፥ ነው። ዘፍ፥ ፲፥ ፴።

ከነዚሁ፥ ከ፲፫ቱ፥ የዮቅጣን፥ ልጆች፥ ፭ቱ፥ ሳባ፥ አውፊር፥ ሀዊላ፥
አባል፥ አቢማኤል፥ በታ፥ በነሳቸው፥ ስፍራ፥ በጠበባቸው፥ ጊዜ፥ ከእስ
ያ፥ ተነሥተው፥ ብዙ፥ ሠራዊት፥ ሁነው፥ ሲፈልሱ፥ ሲሄዱ፥ ሲጕዙ፥ የ
መን፥ ደረሱ። እኒሁ፥ የሴም፥ ዘር፥ ነገደ፥ ዮቅጣን፥ ወደ፥ የመን፥ በገቡ፥
ጊዜ፥ ምንም፥ በፖሊቲክ፥ ምክር፥ በይሰማሙ፥ ለኩሳ፥ የመን፥ ይገብሩ፥
ነበር። በኋላ፥ ግን፥ የኩሳ፥ የመንን፥ ደከምነት፥ አይተው፥ በተንኰልም፥
በሌላም፥ ጥበብም፥ እርስ፥ በርሱ፥ አሸፍተው፥ ከወገናቸው፥ ያሮብ፥ የሚ
ባልም፥ ብልሃተኛ፥ ጀግና፥ አንግሠው፥ ለየመን፥ ሁሉ፥ ባለቤቶች፥ ሆኑ።
ከነዚሁ፥ ነገድ፥ በነገደ፥ ካም፥ መንግሥት፥ መጨረሻ፥ በጺኦሬ፥ ፩ኛ፥ ዘመ
ን፥ በነገሠ፥ በ፲፥ ዓመት፥ በ፫ሺ፭፻፲፥ ዓመተ፥ ዓለም፥ በሺ፭፻ን፥ ዓመት፥
ከልደት፥ በፊት፥ አግናዝያን፥ ተባሉ። ከነገደ፥ ሴም፥ ነገደ፥ ዮቅጣን፥ ከ
የመን፥ ተነሥተው፥ ብዙ፥ ሠራዊት፥ ሁነው፥ በባብ፥ ኤልመንደብ፥ ተ
ሻግረው፥ ወደ፥ ኢትዮጵያ፥ ገቡ።

በዚያን፥ ዘመን፥ ነገደ፥ ዮቅጣን፥ በየጊዜው፥ በ፫፥ ስም፥ ይጠሩ፥ ነ
በሩ። ሳቦች፥ በደዎች፥ አረኞች፥ ትግሬዎች፥ አግያዝያን፥ ይባሉ፥ ነበሩ።
በየጊዜው፥ በዚህ፥ ስም፥ የተጠሩበት፥ ምክንያት፥ በክብረ፥ ነገሥት፥ ከ
ገጽ፥ ፫፻፶፫፥ ፫፻፶፰፥ እዩ።

ኢትዮጲስ፥ የአክሱናስ፥ ሁለተኛ፥ ሳባ፥ የተባለው፥ የልጁ፥ ልጅ፥
የቡልቃያ፥ ልጅ፥ ነው። እናቱም፥ የቱት፥ ንጉሥ፥ ልጅ፥ አግለዓ፥ ትባ
ላለች። ከብ፥ ነገሥት፥ ገጽ፥ ፫፻፷፩፥ ፫፻፷፷፥ ተመልከት። ኢትዮጲስ፥
፩ኛ፥ ከ፫ሺ፮፻፶፱—፫ሺ፮፻፲፥ ዓመት፥ ዓለም፥ ከ፲፰፻፶፯—፲፰፻፲፥ ዓመት፥
ከልደት፥ በፊት፥ ፶፮፥ ዓመት፥ ነገሠ። አገሩም፥ በስሙ፥ ኢትዮጵያ፥ ተ
ባለ። ኢትዮጲስ፥ ወይም፥ ኢትዮጲያ፥ ትርጓሜው፥ ምን፥ እንደሆነ፥ በክ
ብረ፥ ነገሥት፥ ከገጽ፥ ፻፴፥ —፻፲፱፥ ተመልከት። ደግሞ፥ ገጽ፥ ፫፻፳፥ — ፫
፻፳፩፥ እዩ።

ኢትዮጲስ፥ ፩ኛ፥ ከሞተ፥ በኋላ፥ በመንግሥቱ፥ ልጁ፥ ላከንዱ
ን፥ ሁለተኛ፥ ስሙ፥ ኖወርአሬ፥ የተባለው፥ ተከተለው። ክብረ፥ ነገ፥
፫፻፳፯—፫፻፳፯፥ እዩ።

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጲስ፡ ፭ቱ፡ ልጆች፡ ፭፡ ናቸው፡ እነርሳቸውም፡ ላኩንዱን፡ ሳባ፡ ኖባ፡ በለው፡ ከለው፡ ናቸው። የመጀመርያ፡ ልጁ፡ ላኩንዱን፡ መንግሥትን፡ ወረሰ፡ ፬ቱ፡ ግን፡ ያገር፡ ርስትን፡ ተካፍለው፡ ያዙ። ሳባ፡ አሁን፡ ትግሬ፡ ተብሎ፡ በሚጠራው፡ አገር፡ የተቀመጡት፡ ሕዝብ፡ አባት፡ ነው፡ አገሩም፡ በርሱ፡ ስም፡ ሳባ፡ ተብሎ፡ ይጠራ፡ ነበር። የመንግሥት፡ መብቀያና፡ ግንዱ፡ ግንዱ፡ ሆኖ፡ የሚሉ፡ አሉ። ነገር፡ ግን፡ በስም፡ ሞክሼ፡ ነው፡ እንጂ፡ አገሩ፡ ሳባ፡ የተባለ፡ በሁለተኛው፡ ሳባ፡ በኢትዮጲስ፡ አያት፡ ነው፡ እንጂ፡ በኢትዮጲስ፡ ልጅ፡ ሳባ፡ አይደለም። ይህም፡ በዚህ፡ ዘመን፡ አገሩ፡ በስሙ፡ ሳባ፡ ይባል፡ የነበረ፡ የኢትዮጲስ፡ አያት፡ የነገደ፡ አግያዝያን፡ መጀመሪያ፡ ንጉሥ፡ ነገሥት፡ በታቹ፡ ወንድሞቹንና፡ የወንድሞቹን፡ ልጆች፡ አንግሦ። እርሱ፡ በነዚያ፡ በላይ፡ ንጉሥ፡ ነገሥት፡ የሆነ፡ ታላቅ፡ ንጉሥ፡ ነው።ክ፡ ነገ፡ ገጽ፡ ፻፷፫—፻፷፭፡ እዩ።

በለው፡ የአንሰሴና፡ የባርካ፡ ወንዝ፡ መሬትም፡ የሚወርድበት፡ ከሰባ፡ ወደ፡ ሰሜን፡ በለው፡ ምድር፡ ሁሉ፡ ተቀመጠ። አሁንም፡ በዱጭና፡ (ሃርጊጎ) ያሉት፡ ናይባች፡ ከበለው፡ የወረዱ፡ ዘር፡ ናቸው፡ በላባቶችም፡ ናቸው። በላገሮችም፡ በለዎች፡ በሰገላና፡ በሐማሴን፡ ይቀመጣሉ።

በበለው፡ ምድር፡ የሚነገሩ፡ ቋንቋች፡ በዱውኛና፡ ትግሬ፡ ሀድ፡ ዓረብ፡ ናቸው። በዶውኛ፡ ከግዕዝና፡ ከትግሬኛ፡ ከዓረብኛም፡ ጋራ፡ ይመሳሰላል። ከዕብራይስጥም፡ ጋራ፡ እንዲሁ፡ በጣም፡ ይመሳሰላል። የበለው፡ አገር፡ እጅግ፡ በለኸብት፡ ሰፊ፡ ያንድ፡ ንጉሥ፡ አገር፡ ነበር። ውስጡ፡ በምዕራብ፡ አትባራ፡ ወይስ፡ ተከዜ፡ ነው።

ኖባ፡ ምድሩ፡ ከበለው፡ ወደ፡ ምዕራብ፡ ከአትባራ፡ ወዲያ፡ ነው፡ ነጭ፡ አባይና፡ ጥቁር፡ አባይ፡ ከገሩ፡ ላይ፡ ይፈሳሉ። ይህ፡ አገርና፡ ሕዝብ፡ መንግሥቱ፡ ኃይለኛ፡ ነበረና፡ ግብጾችን፡ ያጠቃቸው፡ ነበር፡ አገሩም፡ እጅግ፡ ፍሬያም፡ ነው። እስላም፡ ሳያሸንፉቸው፡ በፊት፡ የበለው፡ መንግሥትና፡ የኖባ፡ መንግሥት፡ ለሳባ፡ መንግሥት፡ ይታወቁ፡ ነበሩ። የኖባ፡ መንግሥት፡ ዛሬ፡ እስላም፡ ሆነ።

ከለው፡ ከሳባ፡ ወደ፡ ምዕራብና፡ ወደ፡ ደቡብ፡ ያለ፡ ያማራ፡ የወልቃይት፡ የጠገዴ፡ ሕዝብ፡ አባት፡ ነው። ከነዚህም፡ የኢትዮጲስ፡ ልጆች፡ የወንድማማቹ፡ ነገድ፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ በመልካቸውና፡ በቁርበታቸው፡ ይመሳሰላሉ። ከሌሎች፡ ከአፍሪቃ፡ ሕዝብ፡ ተለይተው፡ በልዩ

www.ethiopianorthodox.org

ነት፡ የሰው፡ ልጆች፡ ተብለው፡ ይጠራሉ። እኒህም፡ ሕዝብ፡ የያዙት፡ አገር፡ በጥቀሉ፡ ባባታቸው፡ ስም፡ ኢትዮጵያ፡ ተብሎ፡ ይጠራል።

ከኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዋና፡ ባላባቶች፡ የሴም፡ ዘሮች፡ ፪፡ ዋገን ናቸው። እርሳቸውም፡ አማራ፡ ትግሬ፡ አገው፡ በደው፡ አስገዴ፡ በቅላ፡ ሐበብ፡ ናቸው። በደው፡ አስገዴ፡ ብቅላ፡ ሐበብ፡ እኒህ፡ ፬ቱ፡ ነገድ፡ በእስላም፡ ሃይማኖት፡ ገብተው፡ ከወንድሞቻቸው፡ ተለይተው፡ ልዩ፡ ወገኖች፡ ሁነዋል።

አማራ፡ ትግሬ፡ አገው፡ ግን፡ በፊት፡ በቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጊዜ፡ በሕግ፡ ኦሪት፡ ያመኑ፡ በኋላም፡ በክርስትና፡ ያመኑ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሃይማኖት፡ የጸኑ፡ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ መንግሥት፡ ያልጠፋባቸው፡ ባዕድ፡ ገገር፡ ያልገባባቸው፡ የእግዚአብሔር፡ ረዴት፡ ያልራቀባቸው፡ ሕዝብ፡ ናቸው።

ከዚህም፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ አማሮች፡ ትግሮች፡ የኢትዮጵያ፡ ዓይነተኛ፡ ባላገሮችና፡ ባላባቶች፡ የሆኑ፡ ከሴም፡ ዘር፡ ከነገደ፡ ዮቅጣን፡ ልጆች ከእስራኤልም፡ ዘሮች፡ እንደሆኑ፡ የሚያስረዳ፡ ብዙ፡ ምስክር፡ አላቸው። እርሱም፡ ባ፲፪፡ ክፍል፡ ይከፈላልና፡ ምስክሩ፡ ይነግራል።

መጀመርያ፡ ምስክር፡ ከሴም፡ ዘር፡ ከእስራኤል፡ ወገን፡ እንደሆኑ፡ የሚያስረዳ፡ ከልዩ፡ ወገን፡ በመብል፡ በመጠጥ፡ በመጋባትም፡ አለመቀላቀላቸው፡ ነው። ሁለተኛ፡ ምስክር፡ ስለነርሳቸው፡ የሚናገር፡ በዓለም፡ የሚገኝ፡ ታሪክ፡ ነው። ሶስተኛ፡ ከመጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ የተነገረ፡ ትንቢት፡ ነው። አራተኛ፡ አምልኮዋቸው፡ ነው። አምስተኛ፡ ግዝረታቸው፡ ነው። ስድስተኛ፡ መልካቸው፡ ነው፡ ሰባተኛ፡ ጠባያቸው፡ ነው፡ ስምንተኛ፡ ቋንቋቸው፡ ነው፡ ዘጠነኛ፡ ስማቸው፡ ነው፡ አስረኛ፡ ስመ፡ ሃገራቸው፡ ነው፡ አስራአንደኛ፡ ልማድ፡ ሃገራቸው።

የነዚህ፡ ያ፲፪ቱን፡ ክፍሎች፡ ምስክሮች፡ ዋና፡ አስረጁን፡ በዚህ፡ እንዳንጽፈው፡ በየክፍሉ፡ እጅግ፡ ብዙ፡ ነውና፡ ነገር፡ እንዳይበዛ፡ በዚህ፡ ተውነው። ሙሉ፡ ክፍሉን፡ ልታይ፡ ብትወድ፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ ከገጽ፡ ፲፯ — ፻፹፱፡ በየክፍሉ፡ እያነበብህ፡ ልብ፡ አርገህ፡ አስተውለህ፡ ተመልከት።

---

www.ethiopianorthodox.org

## ፮፡ የትግሬ፡ ሕዝብ፡ ታሪክ።

በነገደ፡ ኵሳ፡ መንግሥት፡ ጊዜ፡ በዚያ፡ ዘመን፡ የሀንድ፡ ነገሥታት፡ በርትተው፡ ወደ፡ የመን፡ የመጡ፡ በጦር፡ በዘረፉም፡ ባወኳቸው፡ ጊዜ፡ በየመን፡ ከነበሩ፡ ፳ቱ፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ ሁለቱ፡ ነገደ፡ አቢማኤልና፡ ነገደ፡ ሀዊላ፡ ከዚያው፡ በየመን፡ ቀሩ።

ሶስቱ፡ ነገደ፡ ሳባ፡ ነገደ፡ አባል፡ ኦፌር፡ በነገደ፡ ካም፡ በኵሳ፡ ዘር፡ መንግሥት፡ መጨረሻ፡ ንጉሥ፡ በጺአሬ፡ ፩ኛ፡ ዘመን፡ ከየመን፡ ተነሥተው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መጡ። ጥቂት፡ ጊዜ፡ ባንድ፡ ተቀመጡ፡ ከዚሁ፡ በኋላ፡ ሶስቱ፡ ወንድማማች፡ ነገዶች፡ በምክር፡ ተለያይተው፡ አገሩን፡ ያዙ። አግያዝያን፡ የተባሉ፡ ነገደ፡ ሳባ፡ በትግሬ፡ ሰፈሩ። ነገደ፡ አባል፡ በአዳል፡ አገር፡ ተቀመጡ፡ ነገደ፡ ኦፌር፡ በውጋዴን፡ ተቀመጡ።

ነገደ፡ ሳባ፡ ነጋዶች፡ መስለው፡ ሁነውም፡ ለነገደ፡ ኵሳ፡ መንግሥት፡ ቀረጥና፡ ግብር፡ በመስጠት፡ ጥቂት፡ ዘመን፡ ስለ፡ ተቀመጡበት፡ የዚያን፡ አገር፡ ስም፡ ትግሬ፡ አሉት። ትግሬ፡ ማለትም፡ በቋንቋቸው፡ ባረብኛም፡ ነጋዴ፡ ማለት፡ ነው፡ ከነዚሁ፡ ሕዝብ፡ በላይ፡ የኢትዮጲስ፡ ፩ኛ፡ ልጅ፡ ሰስተኛ፡ ሳባ፡ ጉልተኛ፡ ሁኖ፡ ተሠርቶባቸዋል።

ትግሬ፡ አማራ፡ ማለት፡ የግብር፡ ስም፡ ነው፡ እንጂ፡ እንደ፡ ሳባ፡ እንደ፡ ኖባ፡ የተጸውኦ፡ ስም፡ አይደለም። የትግሬ፡ ታሪክ፡ በነገር፡ ምክንያት፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ በገጽ፡ ፻፹፪፡ ተጽፎልሃል፡ እዩ። የትግሬ፡ ሕዝብ፡ በጊዜው፡ ፫፡ ስም፡ ወጥቶለታል፡ ሳባ፡ በደው፡ እረኞች፡ ወይም፡ ዘላን፡ ትግሬ፡ አግአዚ። ክብ፡ ነገ፡ ፻፹፬፡ ደግሞ፡ ከ፫፻፵፬-፫፻፵፭፡ ፫፻፶፫- ፫፻፵፫፡ እዩ።

---

## ፯፡ የአማራ፡ ሕዝብ፡ ታሪክ።

ስለ፡ አማራ፡ ሕዝብ፡ ታሪክ፡ አቶ፡አጽሜ፡ ስለ፡ ጋላ፡ በጻፉት፡ ታሪክ፡ በ፳፱ኛውና፡ በ፴፫ኛው፡ ገጽ፡ የሚገኝ፡ እንዲህ፡ ይላል፤ ጨዋና፡ ባለጌ፡ ባላገር፡ ልዩ፡ እንደሆነ፡ ተመልከት። ባለጌ፡ ባለርስት፡ ባለመሬት፡ ነው። ጨዋ፡ የንጉሥ፡ አሽከር፡ ነው። እርሱም፡ በባላገር፡ ላይ፡ የተሠራ፡ ምሪተኛ፡ ነው፡ በዛሬ፡ ቋንቋ፡ ወታደር፡ ይባላል። ለዚህም፡ ወታደር፡ በየነገሠው፡ ንጉሥ፡ ዘመን፡ በየአለቃው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የጀግንነት፡ የክብረት፡ ስም፡ ያወጡለታል። ደግሞ፡ ያንዱን፡ ነገድ፡ ካንዱ፡ ነገድ፡ ለመደባለቅ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለንጉሦች፥ ልማድ፥ አላቸው። ስለዚህም፡ ለወታደሮች፡ መልከኞነት፥ እያሉ፥ ፩፡ ጭቃ፥ ፪፡ ጭቃ፥ ፫፡ ጭቃ፥ መሬት፥ እያደረጉ፥ ~~ይሰጥዋቸ~~ ዋል። ያም፥ ወታደር፡ በማያውቀው፥ ሕዝብ፡ ላይ፥ ጨዋ፥ ይሆናል። የመጣበት፥ የማይታወቅ፥ ብዙ፥ ዓይነት፥ ጨዋ፥ በኢትዮጵያ፥ ተሠርት ልዋ። በደምብ፥ ጭዋ፥ እየተባለ፥ ጋላ፥ ሳይቀር፥ ከጨዋ፥ ተቈጥሮ፥ ከ ባላገር፡ ላይ፥ ተሠርትዋል።

ያማራና፥ የትግሬ፡ አበት፡ የሴም፥ የልጁ፥ ልጅ፥ የኤቦር፥ ልጅ፥ ዮቅጣን፥ ነው። በመልክ፥ በጠባይ፥ በቋንቋ፥ ጥቂት፥ ጥቂት፥ ይለያሉ፥ እንጅ፥ ብዙ፥ነገር፡ ይዋረሳሉ። አማሮችና፥ ትግሮች፡ ደግሞ፥ እንደ፥ ነ ገደ፡ እስራኤል፥ ልጆች፥ ሹልዳ፥ ሥጋ፥ አይበሉም። ከብ፥ ነገ፡ ገጽ፥ ፱፻፶፮፡ ተመልከት፤ ደግሞ፥ ፲፻፶፰፡ ገጽ፡ እይ።

ያማራ፥ ሕዝብ፥ የነገደ፥ ሴም፥ ወገኖች፥ የዮቅጣን፥ ልጆች፥ የእስራኤ ል፥ ዘሮች፥ እንደሆኑ፤ ፈጽሞ፥ የሚያስረዳ፥ ጠባያቸው፥ ልማዳቸው መል ካቸው፥ ስማቸው፥ ስም፥ ግራቸው፡ ቋንቋቸው፥ ነው። ከብ፥ ነገ፡ ገጽ፡ ፲፻፶፯ -፲፻፷፬፥ ተመልከት። መንግሥቱ፥ ያማራ፡ ስለሆነ፥ አማርኛ፥ ሰለጠነ። ልዩ፥ ልዩ፥ ሕዝብ፥ ቋንቋቸውን፥ እያጠፉ፥ አማርኛ፡ የሚናገሩ፥ ብዙ፥ ወገኖች፥ አሉ። እኒህም፥ ደምቢያዎች፥ ቋሮች፡ ጋፋቶች፡ የወሎ፥ ጋሎች፥ የጆች፥ ወይም፥ ወረ፥ ሴሆች፥ ናቸው። እንዲሁም፥ የወፍላ፥ ሀሸንጌ፡ ጋሎች፥ ጋሊ ኛን፡ አጥፍተው፥ ትግሪኛ፥ ይናገራሉ። ደግመኛም፥ እንዲህ፥ ይላል፤ አን ዱ፥ ጨዋ፥ መዳባይ፥ በቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጊዜ፡ የነበረ፡ ነው። ብትግ ሬ፥ በጠለምት፥ በስሜን፡ በወገራ፡ የተሠራ፥ ወታደር፡ነው። ከርሱም፡ በኋላ፡ የነገሡ፥ እንዲሁ፡ አደረጉ።

ሶስተኛም፡ በዚያ፥ የታሪክ፡ መጽሐፍ፡ እንዲህ፡ ይላል፤ ኋላም፥ በ፲፮፻፸፫፥ ወይም፥ ፵፡ ዓመተ፥ ምሕረት፥ በላሊበላ፥ ንጉሥ፥ ዘመን፥ አማራ፥ የተባለ፥ ወታደር፡ በዋድላ፥ በበጌምድር፥ በሳይንት፥ በወለቃ፥ ጨዋ፥ ሁኖ፥ በባላገሩ፥ ላይ፡ ተሠራበት። ሳይንት፥ ባላገሩ፥ አረመኔ፡ ነበረ፥ በ እባብና፥ በዘንዶ፥ ያመልክ፡ ይታመን፡ ነበረ። መታመኛ፡ ሲሉ፡ ዘንዶ ውን፡ እባቡንም፥ ተመን፥ አሉት። ይህንኑ፥ ሕዝብ፡ አቡነ፡ ተክለ፡ ሃይ ማኖት፥ ያስተምሩት፥ ነበሩ። ፲፪፡ ዓመት፥ በዚያ፡ ወንጌልን፥ ሲሰብኩ፥ ከማሮች፥ ጋራ፥ ተዋወቁ። ከዛን፥ ቤት፥ ወደ፥ ምኒሊክ፡ ቤት፥ መንግሥ ትን፥ ለመመለስ፡ በዚያ፥ ነው፥ የመከሩ።



www.ethiopianorthodox.org

አማሮች፡ ጥንቱንም፡ ክርስቲያኖች፡ ናቸው፡ የነበሩ፡ ስለዚህ፡ ጋላ፡ ወይም፡ እስላም፡ ክርስትና፡ ሲነሣ፡ አማራ፡ ሆነ፡ ይባላል። በግሩ፡ ልማድም፡ አንድ፡ ሰው፡ ከባልንጀራው፡ ጋራ፡ ሲጣላ፡ አንተና፡ እኔ፡ ከንግዲህ፡ ወዲህ፡ እስላምና፡ አማራ፡ ነን፡ ይላል። ይህም፡ አንተና፡ እኔ፡ እንደ፡ ክርስቲያንና፡ እንደ፡ እስላም፡ በሃይማኖት፡ በኑብረት፡ አንድነት፡ የሌለን፡ ነን፡ ማለት፡ ነው።

አምሃራ፡ ወይም፡ አማራ፡ ማለት፡ አራሽ፡ ማለት፡ ነው፡ ሰይንት፡ ማለትም፡ በረቢኛ፡ የእህል፡ መከማቻ፡ ጎተራ፡ ማለት፡ ነው።

አማሮችም፡ ይኩኖ፡ አምላክን፡ አንግሠው፡ ከዛን፡ ነገድ፡ የሚሆን፡ ይትባረክ፡ ንጉሥን፡ ዋድላ፡ ላይ፡ ገደሉት። ከማራ፡ ሕዝብ፡ ነገር፡ ታሪክ፡ መርማሮች፡ ከኤውሮጳም፡ የመጡ፡ አማራ፡ ከወዴት፡ የመጣ፡ ሕዝብ፡ ነው፡ ሲሉ፡ እጅግ፡ አድርገው፡ ይጨነቃሉ። ሕዝብ፡ ከንድ፡ አገር፡ የወጣበትና፡ የፈለሰበት፡ ይታወቃልና። ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በኋላ፡ ከእስያ፡ ፈልሰው፡ ወደ፡ ኤውሮጳ፡ የገቡ፡ ሕዝብ፡ በየነገዳቸው፡ ስማቸው፡ ተለይቶ፡ ይታወቃሉ፡ መቸም፡ እስያ፡ የሕዝብ፡ መፈለቅያ፡ ምንጭ፡ ናትና።

አማራ፡ ግን፡ ከወዴትም፡ አልመጣም፡ ጥሩ፡ የላስታ፡ ወታደር፡ ከያይነቱ፡ የተጠራቀመ፡ ኃይለኛ፡ ግፈኛ፡ አድመኛ፡ እውቀት፡ ያለው፡ ያልተማረ፡ ጨካኝ፡ ጭፍራ፡ ነው።

ብዙ፡ አዋቆች፡ ታሪክ፡ መርማሮች፡ ግን፡ እንደ፡ መሰላቸውና፡ እንደ፡ አገራቸው፡ ልማድ፡ ጽፈዋል፡ እንዲህ፡ ሲሉ፤ ንጉሥ፡ ላሊበላ፡ ወንድሙ፡ በሳደደው፡ ጊዜ፡ ምስር፡ ወረደ። ከዚያ፡ እስላም፡ ያቀበዘበዛቸውን፡ ክርስቲያኖች፡ ሺሺ፡ የሚያህሉ፡ ሰብስቦ፡ በባይ፡ ወንዝ፡ ለወንዝ፡ ይዞአቸው፡ ሲመጣ፡ ነጭ፡ ዓባይና፡ ጊላባይ፡ በሚገናኙበትም፡ ውሃውን፡ ወደ፡ ሰሃራ፡ ሊመልሰው፡ ቈፈረው። ይህንንም፡ ማድረጉ፡ እስላሞች፡ ክርስቲያኖችን፡ ስለ፡ በደሉ፡ ብድር፡ እስላሞችን፡ ለመበደል፡ ነው። ያ፡ ስፍራ፡ ዛሬ፡ ከርቱም፡ ይባላል። ከርቱም፡ ማለት፡ በትግሪኛ፡ ቁርጥ፡ ማለት፡ ነው። ከዚያ፡ ወጥቶ፡ ጎጃም፡ ሰፈረ። ይህን፡ ሠራዊት፡ ይዞ፡ ከወንድሙ፡ ከጼ፡ ጋራ፡ ተዋግቶ፡ መንግሥትን፡ ያዘና፡ ሮሀ፡ ገባ። በሮሀ፡ ያስወቀራቸው፡ ቤተ፡ ክርስቲያኖች፡ በነዚህ፡ እጅ፡ ነው፡ ይላሉ።

እኛስ፡ የሰማነው፡ አባቶቻችንም፡ የነገሩን፡ ከጥንት፡ የነበረውን፡ ያቆዩን፡ ኢትዮጵያ፡ የአፍሪቃ፡ ሰሜን፡ ምሥራቁ፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳባ፡ ኖባ፡ በሏው፡ ከለው፡ የሚባሉ፡ ኢትዮጵያን፡ እንደ፡ ገዙዋት፡ ሀምያር፡ የሚባል፡ ዓረብ፡ ሁሉን፡ ጠቅልሎ፡ እንደ፡ ነገሠ። ከነሱም፡ የሚሰብሰበው፡ ወታደር፡ ስለ፡ አገልግሎቱ፡ በባላገሩ፡ ላይ፡ ጨዋ፡ መሠራቱን፡ ነገሩን።

አማሮች፡ ግን፡ ይኩኖ፡ አምላክን፡ ከነገሡ፡ በኋላ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ አማርኛ፡ ይናገር፡ ጀመር። ይኸውም፡ አማርኛ፡ ከባታችን፡ ከኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ የመጣ፡ ቃል፡ ነው፡ እንጂ፡ እንደ፡ ሌሎች፡ እንደ፡ ጋሎች፡ ከውጭ፡ ሕዝብ፡ የመጣ፡ ቋንቋ፡ አይደለም። አማርኛ፡ ከዕብራይስጥ፡ ከትግሬ፡ ከዓረብ፡ የመጣ፡ ነው፡ እንጂ፡ በምንም፡ ምንም፡ ከሌላ፡ ቋንቋ፡ የሚገናኝበት፡ ቃል፡ የለም።

አማርኛ፡ ቋንቋ፡ መናገር፡ የጀመሩት፡ ዘመን፡ ግን፡ የተንኰል፡ ዘመን፡ ኑርዋል፡ ፲፻ከ፺፡ ዓመት፡ የኖረው፡ የላስቶችን፡ መንግሥት፡ አፈረሰ። በብርቱ፡ ግዕዝና፡ ዓረብ፡ ትግርኛ፡ የማያውቅ፡ አማርኛ፡ ቢነግሩት፡ አይሰማም፡ ከቶውንም፡ አማራው፡ ያማራውን፡ ቃል፡ አይሰማውም። ያመሰገነው፡ መስሎ፡ ቢረግመው፡ ደስ፡ ይለዋል፡ ይስቃል። ይሰድበው፡ መስሎ፡ ቢያመሰግነው፡ የረገመው፡ መስሎ፡ ቢመርቀው፡ ያመርኛን፡ ጥልቅ፡ አነጋገር፡ የሚያውቅ፡ ይከፋዋል፡ ይቈጣል።

አዝማሪ፡ በጥሩ፡ አማሪኛ፡ ቢዘምር፡ በላይ፡ የሚሰማ፡ አማርኛ፡ አልብሶ፡ በውስጥ፡ ቢሳድብ፡ ወይም፡ ቢያከብርና፡ ቢያመሰግን፡ አማርኛን፡ እጅግ፡ አጥብቀው፡ ካወቁ፡ በቀር፡ ሁሉ፡ አያውቀውም። የሚያስተውለው፡ የለም። ጎጃሜ፡ ሲናገር፡ ሺ፡ ይቅርና፡ ቤገምድሬ፡ አያውቀውም፡ እግሌከ፡ እገሌን፡ ባማርኛ፡ ተናገረው፡ ይባላል። አማርኛ፡ ማለት፡ በፈረንጅ፡ ቋንቋ፡ ፖለቲከ፡ ማለት፡ ነው። ስለዚህ፡ አማራ፡ የኢትዮጲስ፡ ልጅ፡ ነው፡ ቋንቋውን፡ የረዘመውን፡ አሳጥሮ፡ በተንኰል፡ አዛውሮ፡ በመናገሩ፡ ፲፻፺፡ ዓመት፡ የኖረውን፡ መንግሥት፡ አፈረሰ። እርሱም፡ በባላገር፡ ላይ፡ ጨዋ፡ ሁኖ፡ የተሠራ፡ ሠራዊት፡ ነው። እስከዚሁ፡ ከቶ፡ አጽሜ፡ መጽሐፍ፡ የተቀዳ፡ ታሪክ፡ ነው።

የወዲያ፡ አገር፡ ታሪክ፡ ጻፎች፡ ያማራ፡ ሕዝብ፡ ከወዴት፡ እንደ መጣ፡ አይታወቅም። ዳግመኛም፡ ንጉሥ፡ ላሊበላ፡ አስቀድሞ፡ ሳይነግሥ፡ ወንድሙ፡ በሳደደው፡ ጊዜ፡ ምስር፡ ሄዶ፡ እስላም፡ ያቅበዘበዛቸውን፡ ክርስቲያኖች፡ ፳፡ ሺ፡ የሚያህሉ፡ እንህን፡ አማሮች፡ ይዞ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደመጣ፡ ከወንድሙ፡ ከጼ፡ ጋራ፡ ተዋግቶ፡ ድል፡ አድርጎ፡ መንግሥትን፡ እንደ፡ ያዘ፡ እኒህም፡ አማሮች፡ በሮሀ፡ አገር፡ የደ

www.ethiopianorthodox.org

ንጊያ፥ ቤት፥ ክርስቲያኖች፥ ወቅረው፥ እንደ፥ ሠሩለት፥ ስለሚሉም፥ ይህ፥ ፍጹም፥ ሐሰት፥ እንደሆነ፥ አቶ፥ አጽሜ፥ መልከም፥ አድርገው፥ ምላሽ፥ ሰጥተውበታልና፥ አማራ፥ የኢትዮጵያ፥ ልጅ፥ እንደሆነ፥ ከሌላ፥ ወገን፥ እንዳይደለ፥ ቋንቋውም፥ ከአያቱ፥ ከዕብራይስጥ፥ ከባቱ፥ ከግዕዝ፥ ከወንድሞቹ፥ ከዓረብ፥ ከትግርኛ፥ የመጣ፥ እንደሆነ፥ አስረድተዋል።

እኛም፥ ስለ፥ ኢትዮጲስና፥ ስለ፥ ኢትዮጵያ፥ በጻፍነው፥ ከሴም፥ ዘር፥ ከዔበር፥ ልጅ፥ከነገዶ፥ ዮቅጣን፥ ከአግያዝያን፥ ዘር፥ እንደሆነ፥ የግዕዝ፥ የትግሬ፥ ያማራ፥ ቋንቋም፥ ከዕብራይስጥ፥ የመጣ፥ እንደሆነ፥ በብዙ፥ ምስክር፥ አሳይተን፥ አስረድተናል።

ባጼ፥ ይኩኖ፥ አምላክ፥ ጊዜ፥ ያማርኛ፥ ቋንቋ፥ ተጀመረ፥ ማለት፥ ፍጹም፥ ጨዋታና፥ ተረት፥ ተርታ፥ ነገር፥ ነው። ባጼ፥ ይኩኖ፥ አምላክ፥ ጊዜስ፥ ያማርኛ፥ ቋንቋ፥ ፈጽሞ፥ ሰለጠነ። ያማራ፥ የተወደደ፥ ጉሮሮ፥ የማያንቅ፥ ለንግግር፥ የሚያውቅ፥ ሁኖ፥ ስለ፥ ተገኘ፥ የቤት፥ መንግሥት፥ ቋንቋ፥ ሆነ፥ እንጂ፥ ንግግሩስ፥ አስቀድሞ፥ ከዚህ፥ በፊት፥ እጅግ፥ ብዙ፥ ዘመን፥ የነበረ፥ ነው። አጼ፥ ይኩኖ፥ አምላክ፥ የነበሩና፥ የነገሡ፥ አሁን፥ በቅርቡ፥ በ፯ሺ፬፻፶፫፥ ዓመት፥ ዓለም፥ ብ፲፱፻፶፫፥ ዓመት፥ ምሕረት፥ ነው። ካጼ፥ ይኩኖ፥ አምላክ፥ መጀመሪያ፥ መ ንግሥት፥ እስከሁን፥ እስከ፥ ዘመናችን፥ እስከ፥ ፲፱፻፲፫፥ ዓመት፥ ምሕረት፥ ፮፻፺፥ ዓመት፥ ነው። አማርኛ፥ ቋንቋ፥ በዚህ፥ ዘመን፥ ብቻ፥ ተነገረ፥ ማለት፥ እንደ፥ ተረት፥ ያለ፥ የጨዋታ፥ ታሪክ፥ ነው። ከዚህ፥ አስቀድሞ፥ ከ፮፡ ሺ፰፻፶፡-፯፡ ሺ፡ ፬፻፴፫፥ ዓመት፥ ዓለም፥ ካጼ፥ ይኩኖ፥ አምላክ፥ በፊት፥ ከ፲፪፻፷፥ ዓመት፥ የሚበልጥ፥ አማርኛ፥ ቋንቋ፥ እንደ፥ ነበረ፥ በፊተኛው፥ ክብረ፥ ነገሥት፥ ተጽፍዋል። ከዚያ፥ ዘመን፥ ውስጥ፥ ከነገሡት፥ አያሌ፥ የነገሥታቱ፥ ስም፥ ባማርኛ፥ ቋንቋ፥ ነበረ።

ይህም፥ ሊታወቅ፥ ወረደ፥ ነጋሽ፥ አግባ፥ ጉም፥ አስጉምጉም፥ ለትም፥ ተላትም ፥ያደ፥ ጎሽ፥ አይዘር፥ መራ፥ ተከለ፥ ሃይማኖት፥ በመባላቸው፥ ይገለጣልና፥ ይታያል። በፊት፥ አማርኛ፥ ቋንቋ፥ ተሌለ፥ ይህ፥ ሁሉ፥ ስም፥ ከምን፥ መጣ። ይህ፥ ሁሉ፥ በግዕዝ፥ በትግርኛ፥ የሌለ፥ ያማርኛ፥ ስም፥ ነው። ነጋሽ፥ ጎሽ፥ ይህ፥ የዓረቢ፥ ፊደል፥ ያማርኛ፥ ቃል፥ ነው፥ እንጂ፥ በግዕዝ፥ ሽ፥ ኛ፥ ጅ፥ ጨ፥ የሚል፥ ቃል፥ አንድ፥ ስንኳ፥ አይገኝም። በግዕዝ፥ ነጋሽ፥ ነጋ፥ ጎሽ፥ ሲል፥ ጋሙስ፥ ይባል፥ ዓረቢ፥ ፊደል፥ ምንም፥ የለበትም።

www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም፡ ይህ፡ አስቀድሞ፡ በፊት፡ የነበረ፡ ባማርኛ፡ ቋንቋ፡ ስማቸው፡ የተጠራ፡ የነገሥታቱ፡ ስም፡ በንጉሥ፡ ላሊበላ፡ ዘመን፡ አማሮች፡ ከምስር፡ መጡ፡ ብለው፡ ታሪክን፡ የጻፉ፡ ሰዎችን፡ አሳብ፡ ያፈርስባቸዋል። ያማራ፡ ሕዝብ፡ ከነገደ፡ ዮቅጣን፡ ከኢትዮጲስ፡ ዘር፡ እንደ ሆነ፡ ገልጦ፡ ያሳይባቸዋል። ከዚህ፡ ቀጥለን፡ ስለ፡ ነገደ፡ እስራኤል፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መምጣት፡ እንጽፋለን።

---

## ፱፡ ነገደ፡ እስራኤል፡ መምጣት።

በእስራኤል፡ ንጉሥ፡ በሰሎሞን፡ ዘመን፡ መክዳ፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ በመጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ የሳባ፡ የአዜብ፡ ንግሥት፡ የተባለች፡ (፩፡ ነገሥት፡ ፲፡ ፩። ማቴ፡ ፲፪፡ ፵፪።) የሰሎሞንን፡ ጥበብ፡ ወሬውን፡ ሰምታ፡ እሱን፡ ለማየትና፡ ጥበቡን፡ ለመስማት፡ ከብዙ፡ ጓዝ፡ ጋራ፡ ወረደች። ከሰሎሞን፡ ቀዳማዊ፡ ምንልክን፡ ጸንሳ፡ ወዳገርዋ፡ ተመለሰች። ካገርዋ፡ ስትደርስ፡ ወለደችው፡ ስሙንም፡ የብልሃተኛ፡ ልጅ፡ ስትል፡ እብነ፡ ሐኪም፡ አለችው። ከእናቱ፡ ጋራ፡ አድጎ፡ ፳፪፡ ዓመት፡ ሲሆነው፡ አባቱን፡ ሰሎሞንን፡ ለማየት፡ ወደ፡ የሩሳሌም፡ ወረደ። በዚያ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ ሕገ፡ መንግሥትን፡ የዕብራይስጥን፡ ቋንቋ፡ እየተማረ፡ ፫፡ ዓመት፡ ተቀመጠ። ከዚህ፡ በኋላ፡ አባቱ፡ ንጉሥ፡ ሰሎሞን፡ በኢትዮጵያ፡ እንዲነግሥ፡ ከ፲፪ቱ፡ ነገደ፡ እስራኤል፡ ፲፪፡ ሺህ፡ የበኵር፡ ልጆቻቸውን፡ ብልሆችና፡ አዋቂዎች፡ የሆኑትን፡ መርጦ፡ ከተማራት፡ ከካህናት፡ ልጆችና፡ ከመኳንንት፡ ልጆች፡ ፳፪፡ ታላላቆች፡ አላቆች፡ ሹሞ፡ ልጁ፡ ቀዳማዊ፡ ምንልክ፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ልብሰ፡ መንግሥት፡ አሰፍቶ፡ ቅብአ፡ መንግሥት፡ በሊቀ፡ ካህናቱ፡ እጅ፡ አስቀብቶ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ ሥርዓተ፡ መንግሥትን፡ ሰጥቶ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መልሶ፡ ሰደደው። እኒህ፡ የእስራኤል፡ ነገድ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ኢትዮጵያ፡ ገቡ። የገቡበት፡ ዘመንም፡ በ፭፡ ሺ፭፻፲፫፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በ፱፻፹፪፡ ከልደት፡ በፊት፡ ነው። ክብ፡ ነገ፡ ገጽ፡ ፻፹፫ና፡ ፻፹፱፡ እይ።

የእስላሞች፡ ዋና፡ መጽሐፋቸው፡ ፉርቃን፡ ወይም፡ ቁርዓን፡ የሚሉትና፡ የየመን፡ ታሪክ፡ ስለ፡ ንግሥት፡ መክዳ፡ ወይም፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ ሲናገር፡ እንዲህ፡ ያላል፤ የሳባ፡ ንግሥት፡ የተባለች፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ የየመን፡ ንግሥት፡ ናት፡ እንጂ፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ አይ

www.ethiopianorthodox.org

ዶለችም፡ ስምዋም፡ በልቂስ፡ ነው፡ እንጂ፡ መከዳ፡ አይደለም። የበል
ቂስ፡ የእናትዋ፡ አባት፡ የዛር፡ ወይም፡ የጅን፡ ንጉሥ፡ ነበረ፡ ሲሉ፡ ከ
ንቱ፡ የሐሰት፡ ተረትን፡ ያጫውታሉ።

እኛም፡ በኢትዮጵያን፡ ንግሥተ፡ ማከዳን፡ ስምዋን፡ ለወጠው፡
በልቂስ፡ ወይም፡ በልቂሳ፡ ብለው፡ በየመን፡ የተወለደች፡ የየመን፡ ንግ
ሥት፡ ነብሣ፡ ናት፡ ብለው፡ በቁርዓንና፡ በየመን፡ ታሪክ፡ የተጻፈውን፡
ሐሰት፡ በውነት፡ ታሪክ፡ ምስር፡ ቁርተን፡ እንጥላለን። በቁርዓንና፡ በየ
መን፡ ታሪክ፡ ስለ፡ ንግሥት፡ ማከዳ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ሐሰትና፡ ተረት፡
ተጽፍዋል፡ የሚል፡ ሰው፡ ቢኖር፡ በቁርዓንና፡ በየመን፡ ታሪክ፡ ስለ፡
ማከዳ፡ ወይም፡ ስለ፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ ስምዋን፡ በልቂስ፡ ያልዋት፡ የ
ተጻፈ፡ ታሪክ፡ ፍጹም፡ ተረት፡ የሆነ፡ ፲፫፡ ሐሰት፡ አለበት።

መጀመርያ፡ ሐሰት፡ የእምቤታችንን፡ የእግዝእትን፡ ማርያምን፡ አ
ባት፡ ኢልያቂምን፡ ስሙን፡ ለውጠው፡ ማርያም፡ የእምራን፡ ልጅ፡ የ
ሙሴና፡ የአሮን፡ እት፡ ናት፡ እንዳለ፡ (ዘፀ፡ ፮፡ ፳፡ ፩፡ ዜና፡ ፮፡ ፫፡ )
እንዲሁም፡ የንግሥት፡ ማከዳን፡ አባት፡ የተዋስያን፡ ስም፡ ለውጦ፡ የን
ግሥትን፡ በለመዋል፡ ሶርሀቢል፡ የምትባለውን፡ ወይዘሮ፡ ስምዋን፡ ወ
ሰዶ፡ ጥቂት፡ ዘወር፡ አድርጎ፡ በሰ፡ ሸን፡ አግብቶ፡ ሸርሀቢል፡ አለው።

ሁተኛ፡ ሐሰት፡ ንግሥት፡ ማከዳን፡ ስምዋን፡ ለውጦ፡ በልቂስ፡
ውይም፡ በልቂሳ፡ አላት።

ሶስተኛ፡ ሐሰት፡ እርሰዋም፡ በኢትዮጵያ፡መንግሥትን፡ ከባትዋ፡
ከተዋስያ፡ ወርሳ፡ ከኢትዮጵያ፡ እስከ፡ የመን፡ ከዚያም፡ አልፋ፡ እስ
ከ፡ ማዳጋስካር፡ የገዛችውን፡ ንግሥት፡ የየመን፡ ንግሥት፡ ብቻ፡ ናት፡
አላት።

የኢትዮጵዮ፡ ንግሥት፡ ሁና፡ መከዳ፡ እስከ፡ የመን፡ ከዚያም፡ አ
ልፋ፡ እስከ፡ ማዳጋስካር፡ እንደ፡ ገዛች፡ ምን፡ ምስክር፡ አለ፡ የሚል፡
ሰው፡ ቢኖር።

ምላሽ፤ ጀምስ፡ ብሩስ፡ የሚባል፡ የእንግሊዝ፡ አገር፡ ሰው፡ በታ
ሪክ፡ መጽሐፉ፡ በ፪ኛው፡ ክፍል፡ በገጽ፡ ፺፩፡ ስለዚች፡ ንግሥት፡ ሲና
ገር፡ ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ በወንጌል፡ እንዲያው፡ ባጭር፡ ቃል፡
ንግሥተ፡ አዜብ፡ ብሎ፡ አነሣት። የመጣችውም፡ ከዓለም፡ ዳርቻ፡ ነው፡
ይላል። (ማቴ፡ ፲፪፡ ፵፪።) ግዛትዋ፡ የታወቀ፡ አንድ፡ ክፍል፡ ከአፍሪቃ፡
እስከ፡ ማዳጋስካር፡ ድረስ፡ ነው፡ ዛሬ፡ ዘመን፡ ሳፍላ፡ እንለዋለን። ይህ
ች፡ ንግሥት፡ የሰሎሞንን፡ ጥበብ፡ ለመስማት፡ ኢየሩሳሌም፡ ልትሄድ፡

www.ethiopianorthodox.org

በተነሣች፡ ጊዜ፥ ሐበሾች፡ የበርበር፡ አሕዛብ፡ ያረበች፡ የሙር፡ ሰዎች፡ ተከተልዋት። በዙሪያዋ፡ ያለ፡ አገር፡ እርስዋን፡ የማያመሰግን፡ አልነበረም፥ ይባላል። ከዚህ፡ የቀረን፡ በክብረ፡ ነገ፡ ገጽ፡ ፩፻፶፩፡ እይ።

ሞሬዮ፥ የፈረንሳዊ፡ ሊቅም፥ ንግሥት፡ ማክዳ፡ በውነት፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ እንደ፡ ሆነች፡ ሲያስረዳ፥ ንግሥት፡ ማክዳ፡ በዚች፡ በአክሱም፡ አጠገብ፡ ሳባ፡ ከተማ፡ ተቀበረች፥ በመቃብሩዋ፡ ፳፱፡ ሀውልቶች፡ አሉባት፥ አሁን፡ ግን፡ ተሰባብረዋል፥ ይላል። ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ በጻፈው፡ ታሪክ፡ በሁለተኛ፡ መጽሐፉ፡ ፹፩ና፡ ፹፰፡ እይ። ዳግመኛም፡ ክብረ፡ ነገሥት፡ ፩፻፹፩፡ ገጽ፡ ተመልከት።

ዳግመኛም፡ ጀምስ፡ ብሩስ፡ የኢትዮጵያን፡ ታሪክ፡ በጻፈበት፡ መጽሐፉ፡ በ፪ኛው፡ ክፍል፡ በገጽ፡ ፺፫፥ የሰሎሞንን፡ ጥበብና፡ ስራውን፡ ሰምታ፡ በየሩሳሌም፡ በአይሁድ፡ ሃይማኖት፡ ተጠመቀች፡ ልጅም፡ ወለደችለት፡ ስሙም፥ ምኒልክ፡ ተባለ፥ ይላል። ክብረ፡ ነገ፡ ፩፻፺፰፡ ተመልከት።

፩ኛ፡ ሐሰት፥ የበልቂሳ፡ የእናትዋ፡ እናት፡ የዛር፡ ወይም፡ የጅን፡ ንጉሥ፡ ናት፥ የናትዋ፡ አባትም፡ የዓረብ፡ ንጉሥ፡ ነው፡ ያለው፡ ሐሰት፡ ነው። የናትዋ፡ ስም፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ የታወቀች፡ ኤስሜኒ፡ ንግሥት፡ የተባለች፡ ናት። እርስም፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ ነገሥት፡ የተዋስያ፡ ምሽት፡ ናት። ክብረ፡ ነገ፡ ገጽ፡ ፩፻፴፡ እይ።

፫ኛ፡ ሐሰት፥ የበልቂሳ፡ የእናትዋ፡ እናት፡ የዛር፡ ወይም፡ የጅን፡ ንጉሥ፡ ልጅ፡ የዓረብ፡ ንጉሥ፡ አደን፡ በሄደ፡ ጊዜ፥ ነጭ፡ ቡሆር፡ ወይም፡ ሌላ፡ የምታምር፡ ነጭ፡ እንስሳ፡ ሁና፡ ታየችው፡ አለ።

፬ኛ፡ ሐሰት፤ ይች፡ የምታምር፡ ነጭ፡ እንስሳ፡ የሆነች፡ የዛር፡ ንጉሥ፡ ልጅ፡ በእንስሳ፡ ተመስላ፡ በታየችው፡ ጊዜ፡ ቢሆን፡ እይዛታለሁ፡ አል፡ ያዘኝ፡ ብትልም፥ እገላታለሁ፡ ብሎ፡ የዓረብ፡ ንጉሥ፡ ለገቻ፡ ገብቶ፥ ፈረሱን፡ በኀይል፡ እስነሥቶ፡ እየጋለበ፡ ሲቀርባት፥ ሩጣ፡ እየሸሸች፡ ወደ፡ ኋላ፡ ሲቀር፡ ቁማ፥ እየቴየች፡ አልያዘው፡ አልገደለው፡ ብላ፡ ብዙ፡ አደከመችው። ከሠራዊቱም፡ ተለይቶ፡ እጅግ፡ ሩቅ፡ መንገድ፡ ወሰደችው። ከዚህ፡ በኋላ፡ ይችው፡ በነጭ፡ እንስሳ፡ የተመሰለች፡ የዛር፡ ንጉሥ፡ ልጅ፡ በደረሰበት፡ ጊዜ፡ ልብሰ፡ መንግሥት፡ ለብሳ፡ የምታምር፡ ሴት፡ ወይዘሮ፡ ሁና፡ ታየችው፡ ይላል።

፭ኛ፡ ሐሰት፥ በዚህ፡ ነገር፡ ደንግጦ፡ ሳለ፥ ሜዳው፡ ሁሉ፡ የዛር፡

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ፡ ቁም፡ ለፍርበት፡ ድንኳን፡ በድንኳኑ፡ ተቆላልፎበት፡ ከሠራዊቱ፡ ጋራ፡ ሚዳውን፡ መልቶት፡ ተገልጦ፡ ታየው፡ አለ።

፰ኛ፡ ሐሰት፡ ወደ፡ ዛሮ፡ ንጉሥ፡ አባትዋን፡ ይዛው፡ ገባችና፡ አስተዋወቀችው፡ የሁለቱን፡ ፍቅርና፡ መዋደድ፡ አይቶ፡ ጠይቆ፡ ለዓረብ፡ ንጉሥ፡ ምሽት፡ ትሁንህ፡ ብሎ፡ ሰጠውና፡ የበልቂስን፡ እናት፡ ወለደችለት፡ አለ።

፱ኛ፡ ሐሰት፡ ሰሎሞን፡ ከየሩሳሌም፡ ወደ፡ የመን፡ ሁድሁድ፡ ለሚባል፡ ወፍ፡ ደብዳቤ፡ አሲዞ፡ ወደ፡ በልቂስ፡ ላከውና፡ አደረሰላት፡ አለ።

፲ኛ፡ ሐሰት፡ ሰሎሞን፡ ለበልቂስ፡ ብዙ፡ ተአምራት፡ አሳያት፡ ብዙው፡ አንዱ፡ ግንድ፡ ያለ፡ መሮ፡ በወፍ፡ አፍ፡ አስነድሎ፡ አሳያት፡ አለ።

፲፩ኛ፡ ሐሰት፡ በልቂስ፡ ንግሥት፡ ኢየሩሳሌም፡ ሂዳ፡ ከቤተ፡ መንግሥት፡ አጠገብ፡ በደረሰች፡ ጊዜ፡ እሱዋ፡ ገና፡ ሳትገባ፡ አስቀድሞ፡ የሱዋን፡ ባገርዋ፡ ከቤትዋ፡ ያለውን፡ አልጋዋን፡ ለሱዋ፡ መቀመጫ፡ እንዲሆን፡ አሁን፡ ማን፡ ያመጣልኛል፡ ቢል፡ ለሰሎሞን፡ ኢጋንንት፡ ይታዘዙለት፡ ነበርና፡ የኢጋንንት፡ አለቃ፡ እኔ፡ እስተ፡ እኩል፡ ቀን፡ አመጣዋለሁ፡ አለ።

፲፪ኛ፡ ሐሰት፡ ከዚህ፡ የበለ፡ መጉመድ፡ ይህማ፡ ምን፡ ይሆናል፡ ላሁን፡ እሱዋ፡ ሳትገባ፡ ነበር፡ እንጅ፡ ቢል፡ አንድ፡ የመጽሐፍ፡ አውቀት፡ ያለው፡ ሰው፡ ነበረና፡ ዓይንህን፡ ከድነህ፡ እስክትከድው፡ እኔ፡ አሁን፡ በቅጽበት፡ ዓይን፡ አመጣዋለሁ፡ ብሎ፡ ወዲያው፡ አመጣውና፡ የጠራ፡ ውሃ፡ ባሕር፡ መስሎ፡ እየተብረቀረቀ፡ ባተቀመጠበት፡ ስፍራ፡ ላይ፡ ዘረጋው።

፲፫ኛ፡ ሐሰት፡ በልቂስ፡ ንግሥት፡ በገባች፡ ጊዜ፡ ይህን፡ አልጋዋን፡ አይታ፡ ባሕር፡ መስሎዋት፡ ልብስዋ፡ እንዳይነከርባት፡ ልብስዋን፡ ሰብስባ፡ አድርጋ፡ ያዘች፡ አለ።

ይህም፡ በዚያ፡ ከቁርዓንና፡ ከየመን፡ ታሪክ፡ ከተጻፈ፡ የሐሰቱ፡ የውዳሴ፡ ከንቱ፡ የተረቱም፡ ሁሉ፡ ፍጻሜና፡ ማሕተም፡ ነው። እንኳን፡ ያልሆነውን፡ ቢሆንስ፡ በቤትዋ፡ ያኖረችው፡ ባሕሪውን፡ ስራውን፡ ያወቀችውና፡ የለመደችውን፡ የምትቀመጥበትን፡ የምትተኛበትን፡ የገዛ፡ አልጋዋ፡ ጠፋትና፡ ውሃ፡ መስሎዋት፡ ልብስዋን፡ ሰበሰበች፡ ማለት፡ ፍጹም፡ ሐሰትና፡ ተረት፡ የልጆች፡ ጨዋታ፡ ነው። ቢጠናስ፡ አልጋዋን፡ ካላሰበችውና፡ ካልጠረጠረችው፡ በዚያ፡ ስታየው፡ ይህ፡ አልጋ፡

www.ethiopianorthodox.org

በኋ፡ አልጋ፡ ምሳሌ፡ የተሰራ፡ ነው፡ ብላ፡ ትደነቃለች፡ እንጂ፡ አልጋ ዋን፡ የማታውቀው፡ ይመስል፡ ውሃ፡ ነው፡ ብላ፡ ልብስዋን፡ ሰበሰበች፡ ማለት፡ ሰነፎችን፡ አእምሮ፡ የጎደላቸውን፡ እውቀት፡ የሌላቸውን፡ ለ ማስደነቅና፡ ለማስገረም፡ የተጻፈ፡ ከንቱ፡ ተረት፡ ነው።

ይህንንም፡ የመሰለ፡ ከንቱ፡ የባልቴት፡ ተረት፡ ፋርቃን፡ ወይም፡ ቍርዓን፡ በሚሉት፡ በእስላሞች፡ ዋና፡ መጽሐፍ፡ ተጽፎ፡ ይገኛል። የ እስላሞች፡ ነገር፡ ከውነት፡ ይልቅ፡ ሐሰትን፡ ከቁም፡ ነገር፡ ይልቅ፡ ተ ረትን፡ ይወዳሉና፡ ከወንጌል፡ እውነት፡ ይልቅ፡ የቍርዓንን፡ ሐሰትና፡ ተረት፡ ለማድመጥ፡ ጆሮዋቸውን፡ ይመልሳሉ። በነሳቸውም፡ የቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ ቃል፡ ይፈጸምባቸዋል፡ እንዲህ፡ የሚል፡ እውነትን፡ ከመስ ማት፡ ወደ፡ ተረት፡ ይመለሳሉ፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፫።

የቍርዓንና፡ የየመን፡ ታሪክ፡ በአምልኮት፡ በሃይማኖት፡ በንግሥ ት፡ አዜብ፡ በሌላም፡ ታሪክ፡ ሁሉ፡ የተጻፍውና፡ የሚመኩበት፡ ፍሬ፡ ይህ፡ ነው።

ከኤውሮጳ፡ ሰዎችም፡ አያሎች፡ ከዚህ፡ ፍሬ፡ የተቀዳን፡ ይዘው፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ የየመን፡ ንግሥት፡ ናት፡ ሳባ፡ የሚባል፡ በኢትዮጵያ፡ የለምና፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ አይደለችም፡ ብለው፡ ታሪካቸውን፡ ጽፈው፡ እስከ፡ ዛሬ፡ የየመን፡ ሳባ፡ ንግሥት፡ መሆኑዋን፡ ያምናሉ። የ ኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ መሆንዋን፡ ፈጽመው፡ ይጠራጠራሉና፡ ይክዳሉ።

አንዳንዶች፡ ግን፡ እንደ፡ ጀምስ፡ ብሩስ፡ የእንግሊዝ፡ ሊቅ፡ እን ዱ፡ ሞሬኖ፡ የፈረንሳዊ፡ ሊቅ፡ እንደ፡ ኦሚሮስ፡ እንደ፡ ሂሮዶቱስ፡ ያሉ፡ የግሪክ፡ አገር፡ ሊቃውንት፡ እንደ፡ መልዚ፡ እንደ፡ አኬሊ፡ ዜዘኒ፡ ያሉ፡ የኢጣልያ፡ ሊቃውንት፡ እነርሳቸውንም፡ የመስሉ፡ ብዙች፡ የኤውሮጳ፡ የእስያ፡ ታሪክ፡ በጣም፡ መርማሪዎች። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ከሴም፡ ዘር፡ እንደሆኑ፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ ወይም፡ የሳባ፡ ንግሥት፡ የተባለች፡ ከተማዋ፡ በትግሬ፡ ሳባ፡ ይባል፡ እንደ፡ ነበረ፡ መርምረው፡ አውቀው። የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ መሆንዋን፡ ከኢትዮጵያ፡ እስከ፡ የመን፡ ከዚያ ም፡ አልፎ፡ እስከ፡ ማዳጋስካር፡ መግዛትዋን፡ በታሪካቸው፡ ጽፈዋል።

ከዚህም፡ ጋራ፡ አስተዋይ፡ ልቡና፡ አደላዳይ፡ ሕሊና፡ ያለው፡ ሰው፡ ስለ፡ ንግሥተ፡ አዜብ፡ በቍርዓንና፡ በየመን፡ ታሪክ፡ የተጻፈው ን፡ በኢትዮጵያ፡ ከተጻፈው፡ ታሪክ፡ ጋራ፡ ቢያስተያየው፡ የቍርዓንና፡ የየመን፡ ታሪክ፡ ከመጀመሪያው፡ እስከ፡ መጨረሻው፡ ፍጹም፡ ተረት፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደ፡ ሆነ፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ ግን፡ እውነተኛ፡ እንደሆነ፡ ፈጽሞ፡ ይረዳዋል።

የሳባ፡ ንግሥት፡ የተባለች፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ ማከዳ፡ በትግሬ፡ ያለች፡ በአክሱም፡ አጠገብ፡ ቀድሞ፡ በዚያ፡ ዘመን፡ ሳባ፡ ከምትባል፡ ከተማዋ፡ ተነሥታ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሂዳ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክን፡ የወለደች፡ በእርግጥ፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ ናት፡ እንጂ፡ የየመን፡ ንግሥት፡ ብቻ፡ አይደለችም። የርስዋንና፡ የልጅዋን፡ ታሪክ፡ በሙላው፡ ለማየት፡ 'የሚሻና፡ እውነቱን፡ ሊረዳ፡ የሚወድ፡ በክብረ፡ ነገ፡ ገጽ፡ ፬፻፴፩፡ ፳፻፲፱፡ በየክፍሉ፡ እየወጣ፡ ያንብብና፡ ልብ፡ አድርጎ፡ ይመልከት። ስለ፡ ንግሥት፡ ማከዳና፡ ስለ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ከሚነገር፡ ታሪክ፡ ከረጅም፡ በጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ይበቃናል። ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የነገደ፡ አገውን፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

## ፲፡ ነገደ፡ አገው።

ነገደ፡ አገው፡ በሬት፡ ነገደ፡ አዲል፡ ይባሉ፡ ነበሩ። አዲል፡ የዳዊት፡ የልጁ፡ ልጅ፡ የይትረሃም፡ ልጅ፡ ነው፡ ይላሉ፡(፪ ዜና፡ መ፡ ፲፡ ፫።) እሱ፡ ከሃሠራዊቱ፡ ከቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጋራ፡ መጣ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ንጉሥ፡ ነገሥት፡ ሲባል፡ ከርሱ፡ በታች፡ የአገው፡ የላስታ፡ የገነት፡ ዛሬ፡ የጁ፡ የተባለው፡ በዙሪያው፡ ላለው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ንጉሥ፡ ነበር። የዳዊት፡ የልጁ፡ ልጅ፡ የአምኖን፡ ልጅ፡ ኖን፡ የሚባል፡ ነበር። እርሱም፡ ከቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጋራ፡ መጥቶ፡ ከርሱ፡ በታች፡ ከቋራ፡ እስከ፡ መተማ፡ በታች፡ ለገር፡ ንጉሥ፡ ነበር፡ ይላሉ። ከተማውን፡ በቋራ፡ አደረገ፡ አገሪቱንም፡ ቋራ፡ ብሎ፡ ጠራት። በቋራ፡ የሚኖሩ፡ የርሱ፡ ዘሮች፡ በኖን፡ ልጅ፡ በሔት፡ ስም፡ ነገድ፡ ሔት፡ ተባሉ። ቋንቋቸውም፡ ጥንት፡ ልዩ፡ ነበር፡ አሁን፡ ግን፡ ቋንቋቸውን፡ አጥፍተው፡ በማራ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ። በጥንት፡ ቋንቋቸው፡ ኳራ፡ ወይም፡ ቋራ፡ ማለት፡ ፀሐይ፡ ማለት፡ ነው፡ ይላሉ። ቋንቋቸውም፡ ከአገዎች፡ ጋራ፡ ይቀረብ፡ ነበሩ፡ ይባላል።

አገዎች፡ ግን፡ ከ፫፡ ተከፍለው፡ ቋንቋቸውም፡ ስሩ፡ አንድ፡ ሲሆን፡ በየክፍላቸውና፡ በየአገራቸው፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ ልዩነት፡ ያለው፡ ሆነ። እነርሳቸውም፡ በ፫፡ አገር፡ ስም፡ ይጠራሉ። የላስታ፡ አገው፡ የ

www.ethiopianorthodox.org

ዳሞት፡ አገው፡ የሐሉል፡ በጎስ፡ አገው፡ ይባላሉ። የሁሉ፡ መሠረትና፡ ምንጭ፡ የላስታ፡ አገው፡ ነው።

የዳሞት፡ አገዎች፡ ከላስታ፡ አገው፡ ፺፡ ሆነው፡ ዘሆንና፡ ጎሽ፡ አደን፡ ብለው፡ ሄዱ። ከዚያ፡ ሰው፡ እንደ፡ ሌለበት፡ ጠፍ፡ እንደሆነ፡ ተመልክተው፡ ያገሪቱንም፡ ደግነት፡ አይተው፡ በየዱሩ፡ በየዛፉ፡ እጅግ፡ ንብ፡ የበዛበት፡ ብዙ፡ ማር፡ የሚገኝበት፡ አገር፡ ነውና፡ ማርና፡ የዱር፡ እንስሳ፡ ሥጋ፡ አድነው፡ እየበሉ፡ ፺፡ ወር፡ አገሪቱን፡ ደኅና፡ አድርገው፡ ዞሩና፡ መረመሩ፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ምሽቶቻቸውንና፡ ልጆቻቸውን፡ ላሞቻቸውን፡ ፍየላቸውን፡ ጓዛቸውን፡ ሁሉ፡ አምጥተው፡ በዚያች፡ አገር፡ ተቀመጡባትና፡ አቀኑዋት። ባላገሮች፡ ባላባቶችም፡ ሆኑባት፡ አገሩም፡ አገው፡ ምድር፡ ተባለ። በ፺ቱ፡ አባቶችም፡ በየክፍሉ፡ ሲዘረዘር፡ ፺፡ ቤት፡ አገው፡ ይባላል። በ፺ቱ፡ አባቶቻቸው፡ ስም፡ አገራቸውን፡ ሰይመው፡ ፺፡ ቤት፡ አገው፡ ተብለው፡ በየአገራቸው፡ በየክፍላቸው፡ ይጠራሉ።

የሀልሀል፡ በጎስ፡ አገዎች፡ ግን፡ በአንድ፡ ዘመን፡ በያገሩ፡ ረሃብ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ እንዲሁ፡ በላስታ፡ አገው፡ ፺፡ ወንድማማች፡ አገዎች፡ ከነሚስቶቻቸው፡ ከነልጆቻቸው፡ ፫፡ እቶቻቸውም፡ ከነባሎቻቸው፡ ተሰደው፡ ሀልሀል፡ በጎስ፡ ገቡ፡ በዚያም፡ ዱሩን፡ መንጥረው፡ አባቡን፡ ገድለው፡ ቤት፡ ሠርተው፡ አገር፡ አቅንተው፡ ተቀመጡ፡ ይባላል።

የላስታ፡ አገዎች፡ በጥግ፡ የማኖሩ፡ ጥኖች፡ እነርሳቸው፡ ናቸውና፡ በቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጊዜ፡ የያዙትን፡ አገር፡ አለቀቁም፡ እስከዛሬ፡ አልተነቃቁም። ስለ፡ አገዎች፡ ከሚነገር፡ ታሪክ፡ ከዚህ፡ የቀረን፡ በክቡ፡ ነገሥ፡ ከገጽ፡ ፻፹፱፡ —፻፺፩፡ በገጽ፡ ፺፻፱፡ ከተጻፈው፡ ጋራ፡ አስተያይተህ፡ ተመልከት። ስለ፡ ነገደ፡ አገው፡ ከሚነገር፡ ታሪክ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ይበቃናል።ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የነገደ፡ አስማክህን፡ ነገር፡ ታሪክ፡ እንጽፋለ።

---

## ፲፩፡ ነገደ፡ አስማክህ፡

ነገደ፡ አስማክህ፡ በ፬ሺ፡ ፫፻፹፫፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በ፭፻፳፯፡ አመት፡ ከልደት፡ በፊት፡ ከጥላሜቲክ፡ ፩ኛ፡ ፈዖርን፡ ከምስር፡ ንጉሥ፡ ተጣልተው፡ ፪፻፺ሺ፡ ሠራዊት፡ ከምስር፡ ንጉሥ፡ ከድተው፡ ወደ፡ ኢት

ዮጵያ፡ መጥተው፡ ለዊያንኪ፡ ፬ኛ፡ ለኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ ገቡ። እር ሱም፡ በናዋታን፡ ሳለ፡ ያላሰቡቸውን፡ ረዳቶች፡ በድንገት፡ ስለ፡ አገኘ፡ በታላቅ፡ ደስታ፡ ተቀበላቸው። ከደስታውም፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ፈጥኖ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ አገር፡ ሰጣቸው። ለሱም፡ ጠላቶቹ፡ ይዘውት፡ የነበሩ ትን፡ አሉ፡ በምዕራብ፡ የነበረውን፡ አገር፡ እዲያቀኑለት፡ ፈቀደላቸው። ያለ፡ ጥርጥር፡ በዚህ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ያለ፡ ሕዝብ፡ በአኩስም፡ መንግሥ ት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ መንበሩን፡ ትቶ፡ ነበረና፡ ነገደ፡ አስማክሁ፡ እንዲህ፡ ሁ ነው፡ በኢትዮጵያ፡ ቀሩ፡ በፊት፡ በሰናሒት፡ ነበሩ፡ በኋላ፡ ግን፡ ነጭ አባይና፡ ጥቁር፡ አባይ፡ በሚገናኙበት፡ ወንዞች፡ መሀል፡ ተቀመጡ፡ ታላቅ፡ ሕዝብም፡ ሆኑ። የነሱ፡ ወገን፡ ከ፫፻፡ ዓመት፡ የሚበልጥ፡ የያዙ ትን፡ ኤዛር፡ የሚባልን፡ ከተማ፡ ሰሩ። ብዙ፡ የምስርን፡ ልማድ፡ ለኢ ትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ አስተማሩ፡ አገራቸውም፡ የመጡ፡ የአሉ፡ መንግሥት፡ ዛሬ፡ ሴዩክ፡ ለሚባሉት፡ አለፈ። በአስትራቦን፡ ዘመን፡ እንዲት፡ መ ንግሥት፡ ነበረች፡ በጵሊን፡ ጊዜያት፡ ያቆሙት፡ መንግሥት፡ ግን፡ እ ንዳልነበረ፡ ሆነ።

ይህም፡ የ፪፻፵ሺ፡ ሠራዊት፡ ከዳት፡ ያገሩ፡ ዋና፡ ሠራዊት፡ ነበር ና፡ ለምስር፡ መንግሥት፡ እጅግ፡ አጥብቆ፡ ጎዳውና፡ አደከመው። የው ጭ፡ ሰዎች፡ በዘመቱበት፡ ጊዜ፡ ሊቃወም፡ አልተቻለውም፡ የፒርስ፡ ሰዎችም፡ ምስርን፡ በዘንግ፡ ሊገዙት፡ ሆነ። የምስር፡ ፈርዖኖችም፡ በየ ዘመናቸው፡ ነገደ፡ አስማክህን፡ ፩ኛ፡ ከሄደበት፡ አሳብ፡ አልተሻለም። የነገደ፡ አስማክሁ፡ ታሪክ፡ ብዙ፡ ነው። ከምስር፡ ምድር፡ ተጣልተው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ የገቡበትን፡ ምክንያት፡ ሙሉ፡ ታሪኩን፡ ል ትሰማ፡ ብትወድ፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ ገጽ፡ ፻፺፪—፻፺፰፡ ደግሞ፡ ፺፻፸፩፡ ተመልከት።

---

## ፲፱፡ ነገደ፡ ፈላሻ።

ስለ፡ ነገደ፡ ፈላሻ፡ የሚነገር፡ አንድ፡ እንዱ፡ እውነት፡ ያልሆነ፡ ሁለቱ፡ የታመነ፡ ፬፡ ታሪክ፡ አለ። አንድ፡ እውነት፡ ያልሆነ፡ ያልነው፡ ሞሪዬ፡ በመጀመሪያ፡ መጽሐፉ፡ ስለ፡ ካም፡ ልጆች፡ ታሪክ፡ ሲናገር፡ የኩስ፡ ወይም፡ የኩሽ፡ ልጅ፡ ረሁም፡ ሁለተኛ፡ ስሙ፡ ሮሙስ፡ የተባ ለ፡ ሁለት፡ ልጆች፡ ወለደ። እነርሳቸውም፡ ዩዳና፡ ሳቢውስ፡ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ዩዳ፣ በኢትዮጵያ፡ ያሉ፣ ፈላሾች፡ አባት፣ ነው፡ ብሎ፣ ፈላሾችን፣ የከም፣ የልጅ፣ ልጆች፣ አድርጎ፡ ዩዳ፡ የሚባል፡ አባት፡ ይሰጣቸዋል። ይህ፣ ግን፡ ላም፣ አልዋለበት፣ ኩበት፡ ለቀማ፡ በልታረሰበት፡ ገለባ፡ ሸማ፣ እንደሚሉት፡ ተረት፣ ከንቱ፡ ጨዋታ፣ ነው፡ እንጂ፣ እውነት፣ ነገር፣ አይደለምና፣ የማይታመን፡ እውነት፡ ያልሆነ፡ ነገር፡ ያልነው፡ ስለዚህ፡ ነው።

ስለ፣ ፈላሾች፣ ነገር፣ ታሪክ፣ ፫፣ የታመነ፣ ነው፣ ያልነው፣ እንዲህ፣ ነው፤ በኢትዮጵያ፣ ያሉ፣ ፈላሻ፣ ሕዝብ፣ ስራቸውና፡ ምንጪቸው፣ ያለ፡ ጥርጣሬ፡ የእስራኤል፣ ዘር፣ ናቸው። ከፓለስቲና፣ ከእስራኤል፣ አገር፣ ወደ፡ ኢትዮጵያ፣ የመጡ፡ ግን፣ በየዘመኑ፡ ሰስት፡ ጊዜ፣ ነው።

መጀመሪያ፡ ከቀዳማዊ፡ ምኒልክ፣ ጋራ፣ ከመጡት፣ ከእስራኤል፣ ሕዝብ፡ አብረው፣ የመጡ፡ ናቸው፤ እስከ፣ ዘመነ፣ ወንጌል፡ በንድ፡ የተቀመጡ፡ ናቸው። በአብ፣ ሰላማ፡ ከሳቴ፡ ብርሃን፣ የኢትዮጵያ፣ ሕዝብና፣ ነገሥታት፡ የመንግሥትም፣ ዘር፣ ሁሉ፡ በወንጌል፡ ቃል፡ አምነው፣ ክርስትና፣ ሲገቡ፣ እነርሳቸው፣ ግን፣ ከወንድሞቻቸው፣ ከሕዝባቸው፣ ተለይተው፤ በወንጌል፡ ቃል፡ አናምንም፡ ክርስትና፡ አንገባም፡ ሕግ፣ ኦሪትን፣ አንለቅም፡ ብለው፣ የቀሩ፣ የተለዩ፡ ናቸው።

ሁለተኛ፤ አስብያኖስና፣ ጢጦስ፡ የሮም፣ ነገሥታት፡ ኢየሩሳሌምን፡ በፈርስዋት፡ ቤተ፣ መቅደስን፡ በቃጠሉት፡ እስራኤልን፡ በፈጅዋቸው፣ ጊዜ፡ ከሞት፡ የተረፉ፣ እስራኤል፡ በየገሩ፡ ሲበታተኑ፣ አንድ፡ ክፍል፣ ከፓለስቲና፣ ተሰደው፣ ወደ፣ ኢትዮጵያ፣ ገቡ።

ሶስተኛ። በጉዲት፡ ዘመን፣ ከምስር፣ ንጉሥ፣ ሸሽተው፣ ከጉዲት፣ ጋራ፣ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ገብተው፡ የክርስቲያንን፡ መንግሥት፣ የገለበጡና፡ ያፈረሱ፣ የአክሱምንም፣ ቤተ፣ ክርስቲያን፣ ያቃጠሉና፣ ክርስቲያንን፣ ያረከሱ፣ ናቸው። እነሆም፡ የፈተኖች፣ ፈላሾች፣ ከኋለኞች፡ ጋራ፡ ተቀላቅለው፣ ለጉዲት፡ ረድተው፣ መንግሥትን፡ ቢያፈርሱ፣ በክርስቲያን፣ ላይም፣ ግፍ፣ እየሰሩ፣ ሃይማኖተ፡ ወንጌል፡ ቢያረክሱ፡ ጉዲት፡ በሞተች፣ የክርስቲያን፣ ንጉሥ፣ አንበሳ፡ ውድም፣ በነገሠ፣ ጊዜ፡ እንህን፡ ፈላሾች፣ ፈጃቸውና፡ የክርስቲያንን፣ ደም፡ ብድሩን፡ መለሰ።

ከዚህ፣ በኋላ፡ ጥቂት፣ ከሞት፣ የተረፉ፣ በዱር፡ በገደል፡ የነበሩ፣ ፈላሾች፣ ሁሉ፤ ማረን፡ ለእግዚአብሔር፣ ብለህ፡ ይቅር፡ በለን፣ ብለው፣ ደንጊያ፣ እየተሸከሙ፣ ገቡና፡ ቢለምኑት፤ ንጉሡም፣ ነፍሳቸውን፣ ምሬያቸዋለሁ፤ ክርስትና፣ ከጉልት፣ ግን፣ ነቅያችኋለሁ፡ ብሎ፣ ነቀላቸው። በ

www.ethiopianorthodox.org

ዚህም፡ ከጉልት፡ ተነቅለው፡ ስደተኞች፡ የክርስቲያን፡ ዜጎች፡ ጭገኞች፡ ጢሰኞች፡ ሁነው፡ ኖሩ። ስለዚህም፡ ፈላስያን፡ ተባሉ። ፈላስያን፡ ማለትም፡ ስደተኞች፡ ማለት፡ ነው። በዘመን፡ ብዛት፡ ሲለወጥ፡ ፈላሻ፡ ተባሉ። እኒህ፡ ሕዝብ፡ እስከ፡ አጼ፡ ዓምደ፡ ጽዮን፡ ዘመን፡ ከዚያም፡ ወዲህ፡ እስከ፡ ፲፻፭፻፰፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ እስከ፡ አጼ፡ ሠርጸ፡ ድንግል፡ ዘመን፡ ድረስ፡ ከክርስቲያን፡ መንግሥት፡ እየሸፈቱ፡ ያውኩ፡ ነበሩ። በዚህም፡ ምክንያት፡ ነገሥታት፡ ቀጠቀጥዋቸውና፡ አደከምዋቸው፡ ያለ፡ ምሕረትም፡ አጠፍዋቸውና፡ አጠቁዋቸው። ዛሬ፡ ግን፡ ጥቂት፡ በቀሩ፡ በክርስቲያን፡ ላይ፡ ራሳቸውን፡ የማያቀኑ፡ የተጠቁ፡ ሆኑ። በያገሩ፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ አሉ፤ ያሚበዙ፡ ግን፡ በጭልጋ፤ በጋበ፡ በርማጮሆ፤ በወልቃይት፤ በጠገዴ፤ በቆላ፡ ወገራ፤ በጎንደር፡ ከተማ፡ ዙሪያ፡ ይኖራሉ።

እኒህ፡ ሕዝብ፡ ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስን፡ በመስቀል፡ ከገደሉ፡ የእግዚአብሔር፡ ቁጣ፡ በላቸው፡ ወርዶባቸው፡ ደሙ፡ በኛ፡ በልጆቻችንም፡ ላይ፡ ይሁን፤ ያሉት፡ መርገም፡ ደርሶባቸው፡ በዓለም፡ ሁሉ፡ ሕዝብ፡ የተናቁና፡ የተጠሉ፡ የተዋረዱም፡ ናቸው። ስለዚህም፡ የከበሩ፡ የእግዚአብሔር፡ ሕዝብ፡ በተባሉበት፡ ፈንታ፡ ዓመጸኛ፡ ሕዝብ፡ ተባለው፡ በአሕዛብ፡ ሁሉ፡ ተበትነው፡ የተጠሉ፡ የተዋረዱ፡ ሐፍረት፡ የለበሱ፡ ሆኑ። የነቢዩ፡ ሕዝቅኤል፡ ትንቢት፡ በነርሳቸው፡ ተፈጸመባቸው። ሕዝ፡ ፳፪፡ ፩፡—፲፫። ፳፬፡ ፮—፲፬። ፳፫፡ ፴፭—፵፱። ይህ፡ ሁሉ፡ ውርደትና፡ ሐፍረት፡ የደረሰባቸው፡ ለወንጌል፡ ሃይማኖት፡ በይቃዘዙ፡ ለጌታችን፡ ለየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ባይገዙ፡ ነው። ሮሜ፡ ፲፡ ፲፪—፳፩። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፩፡—፫። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፲፯—፲፱። ፲፯፡ ፳። ስለ፡ ነገደ፡ ፈላሻ፡ ታሪክ፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ በገጽ፡ ፻፺፰—፻፺፱፡ ተመልከት።

ስለ፡ ፈላሻ፡ ሕዝብ፡ ደግሞ፡ በዘመነ፡ አጼ፡ ካሌብ፡ ዙዋኑስ፡ ወይም፡ ፊንሓስ፡ የተባለ፡ አይሁዳዊ፡ አገረ፡ ናግራንን፡ በየመን፡ ክፍል፡ የምትሆን፡ በጠፋ፡ ጊዜ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንን፡ አቃጥሎ፡ ክርስቲያኖችን፡ ገሎ፡ በባላሸ፡ ጊዜ፡ አጼ፡ ካሌብ፡ ሄደው፡ ይህን፡ ዙዋኑስ፡ ወይም፡ ፊንሓስ፡ የተባለን፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ገደለው፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ የተባበሩ፡ አይሁድን፡ ፈጅዋቸውና፡ የክርስቲያንን፡ ደም፡ መለሱ። ከዚያ፡ ከሞት፡ ያመለጡ፡ አይሁድ፡ ወይም፡ ፈላሾች፡ በባብ፡ እልመንደብ፡ ተሻግረው፡ በኢትዮጵያ፡ ከሚኖሩ፡ ፈላሾች፡ ወንድሞቻቸው፡ ተጨመሩ፡ የሚሉም፡ አሉ። ነገር፡ ግን፡ የክርስቲያን፡ ባለደሞች፡ ሁነው፡ ተጠልተ

www.ethiopianorthodox.org

ዋልና፡ ደፍረው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የመጡ፡ አይመስልም። ስለ፡ ነገደ፡ ፈላሻ፡ የሚነግር፡ ታሪክ፡ ይህ፡ ይበቃናል፡ ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ ስለ፡ ነገደ፡ ጋፋት፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

## ፲፫ ፡ ነገደ ፡ ጋፋት ።

የጋፋት፡ ሁለት፡ ወገን፡ ሁለት፡ ክፍል፡ ናቸው፤ መጀመሪያ፡ የኩሳ፡ ወገን፡ ጋፋት፡ ሁለተኛ፡ የእስራኤል፡ ወገን፡ ጋፋት፡ ይባሉ፡ ነበሩ። ከጥቂት፡ ጊዜ፡ በኋላ፡ ግን፡ ባንድ፡ መጋባት፡ በንብረትም፡ ተቀላቀሉና፡ አንድ፡ ጋፋት፡ ተባሉ።

የኩሳ፡ ጋፋት፡ አባት፡ ስሙ፡ ጋፋት፡ የተባለ፡ አንድ፡ ታላቅ፡ ሰው፡ ነበረ። ተከም፡ ልጅ፡ ከኩሳ፡ ዘር፡ ነበር። ነገደ፡ ኩሳ፡ የኢትዮጵያን፡ መንግሥት፡ ለቀው፡ አግያዝያን፡ የተባሉ፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ የኢትዮጵያን፡ አገርና፡ መንግሥት፡ በያዙ፡ ጊዜ፡ ይህ፡ ጋፋት፡ ከነልጆቹ፡ ያዘዛችሁትን፡ ሰርቼ፡ ለናንተ፡ ተገዝቼ፡ እኖራለሁ፡ ወደማላውቀው፡ አገር፡ አልሰደድ፡ በለመድሁት፡ ልኑር፡ ብሎ፡ ወደ፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ ላከ። እነርሳቸውም፡ የዘዝንህን፡ ሰርተህ፡ ለኛ፡ ተገዝተህ፡ ከኖርህ፡ ምረንሃል፡ ግባ፡ አሉት። እሱም፡ መጥቶ፡ ከነልጆቹ፡ ገባ። ከነልጆቹም፡ ያዘዙትን፡ እየሰራ፡ ለነርሳቸው፡ እየተገዛ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ዜጋ፡ ሁኖ፡ ተቀመጠ።

የእስራኤል፡ ወገን፡ ጋፋት፡ የተባሉ፡ በቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ዘመን፡ ከእስራኤል፡ ንጉሥ፡ ከሮብዓም፡ ከሰሎሞን፡ ልጅ፡ ከወንድሙ፡ በክፋቱ፡ ሸፍተው፡ ተዋጉትና፡ ድል፡ ሁነው፡ የሸሹ፡ ቢያገኛቸው፡ እንዳያጠፋቸው፡ ፈርተው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መጡ፡ በዳሞት፡ ሰፈሩ፡ ጋፋት፡ ተባሉ። ጋፋት፡ ማለትም፡ ስደተኛ፡ ማለት፡ ነው።

በፊት፡ እንዳልነ፡ እኒህ፡ ሁለት፡ ወገን፡ ጋፋት፡ በመጋባት፡ በግብር፡ በሥርዓት፡ አንድ፡ ሁነው፡ ተቀላቀሉ፡ ባንድ፡ ስምም፡ ጋፋት፡ ተባሉ። ጋፋቶች፡ ግን፡ ስለ፡ ትውልዳቸው፡ ቢጠይቋቸው፡ ከምን፡ ዘር፡ እንደሆኑ፡ አያውቁምና፡ የኛ፡ አባት፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጽላተ፡ ሙሴን፡ ከየሩሳሌም፡ ይዞ፡ የመጣ፡ ጊዜ፡ አብሮ፡ የመጣ፡ ነው። ከጉዞ፡ ላይ፡ ከጠባብ፡ ስፍራ፡ አልፋለሁ፡ ሲል፡ ታቦቲቱን፡ ገፋት፡ ገፋት፡ ገፋት፡ እያሉ፡ ተቈጡ። በዚህ፡ ምክንያት፡ አባታችን፡ ስሙ፡ ጋፋት፡

www.ethiopianorthodox.org

ተባለ፡ ብለው፡ ብቻ፡ ይተርካሉ፡ የተጻፈ፡ ግን፡ የለም። ይህ፡ ከሆነ፡ የፊተኛው፡ ስሙ፡ ማን፡ ይባል፡ ነበረ፡ ቢሉዋቸው፡ ምንም፡ የለምና፡ ሊመልሱ፡ አይችሉም። ይህ፡ ተረት፡ የሆነ፡ ያፍ፡ ታሪካቸው፡ ግን፡ ፍጹም፡ ጨዋታ፡ ነው፡ እንጂ፡ እውነት፡ ነገር፡ አይደለም። ጋፋት፡ ያማርኛ፡ ቋንቋ፡ ነው። በቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ጊዜ፡ ባማርኛ፡ ቋንቋ፡ መቸ፡ ይናገሩ፡ ነበሩና፡ ገፋት፡ ብለው፡ ባማርኛ፡ አፍ፡ ተናገሩት፡ ብለን፡ ለመጠየቅ፡ ግድ፡ ነው። ይህንስ፡ አናውቅም፡ ከማለት፡ በቀር፡ ለዚህ፡ የሚበቃ፡ ሌላ፡ ምላሽ፡ የላቸውም።

ጋፋት፡ ፲፡ ወንዶች፡ ልጆች፡ ወለደ፡ ስማቸውም፡ እሌህ፡ ናቸው፤ አብድራይ፡ ገምበ፡ ቢረበበ፡ የዘምበል፡ የሱብሊ፡ አሽመን፡ ሀርበዋሽ፡ ሀርብ፡ አከል፡ ወንጌ፡ ድን። እኒህም፡ አስሩ፡ የጋፋት፡ ልጆች፡ በየልጆቻቸው፡ በየወገናቸው፡ ደግሞ፡ ባ፲፡ ነገድ፡ ተከፍለው፡ በውስጥ፡ በየአባቶቻቸው፡ ስም፡ ይጠራሉ። በላይ፡ ግን፡ ነገደ፡ ጋፋት፡ በመባል፡ ባያታቸው፡ ስም፡ ባንድ፡ ተጠቅልለው፡ ይጠራሉ።

የአብድራይ፡ ልጆች፡ ነገደ፡ አብድራይ፡ ይባላሉ። ሁሉም፡ እንዲሁ፡ በየአባቶቻቸው፡ ስም፡ ነገደ፡ ገምበ፡ ነገደ፡ ቢረበበ፡ ነገደ፡ የዘምበል፡ ነገደ፡ የሱብሊ፡ ነገደ፡ አሽመን፡ ነገደ፡ ሀርበዋሽ፡ ነገደ፡ ሀርብ፡ አከል፡ ነገደ፡ ወንጌ፡ ነገደ፡ ድን፡ ይባላሉ።

እኒህም፡ ሕዝብ፡ ከብዙ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ቀማኞች፡ ሌቦች፡ ግፈኞች፡ ሆኑ። ስለዚህም፡ ነገሥታት፡ በየዘመናቸው፡ ይዘርፍዋቸው፡ ያጠፍዋቸው፡ ነበሩ። ይልቁንም፡ በጼ፡ ሱስንዮስ፡ ዘመን፡ ይዘርፍዋቸው፡ ይማርክዋቸው፡ ያጠቁዋቸው፡ እንደነበሩ፡ አባ፡ ጢኖ፡ በጻፈው፡ በጼ፡ ሱስንዮስ፡ ታሪክ፡ ይገኛል።

ነገደ፡ ጋፋት፡ በፊት፡ በሸዋ፡ ይኖሩ፡ ነበሩ፡ በኋላ፡ ግን፡ ከሸዋ፡ ፈልሰው፡ ጎጃም፡ ተሻገሩ። የሚበዙት፡ ቆላውን፡ ያበይን፡ ዳር፡ ለዳር፡ ይዘው፡ እስከ፡ ድን፡ በዳሞት፡ ይኖራሉ። በሸዋ፡ በበጌ፡ ምድርም፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ አሉ። ስለዚህም፡ በደብረ፡ ታቦር፡ አጠገብ፡ ሰላምኮ፡ አጠገብ፡ የነበሩት፡ አገር፡ በስማቸው፡ ተጠርቶ፡ እስከሁን፡ ጋፋት፡ ይባላል። በእስቴም፡ መከነ፡ ኢየሱስ፡ አጠገብ፡ ያሉበት፡ አገር፡ በስማቸው፡ ጋፋቶች፡ ይባላል።በሸዋም፡ በደብረ፡ ሊባኖስና፡ በጅር፡ መሀከል፡ በል፡ ጋፋት፡ ይባላል።

ነገደ፡ ጋፋት፡ ጥንት፡ አረማውያን፡ ነበሩ፡ አሁን፡ ግን፡ ክርስቲያኖች፡ ናቸው። ባማራ፡ ሕዝብ፡ መሀከል፡ ስለ፡ ተቀመጡ፡ ቋንቋቸው

www.ethiopianorthodox.org

ን፡ አጥፍተው፡ በማርኛ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ፡፡ አንዳንዶች፡ ግን፡ የጥንት፡ ቋንቋቸውን፡ ያልረሱ፡ እርሱበርሳቸው፡ የምስጢር፡ ነገር፡ ሲነጋገሩ፡ በጥንት፡ ቋንቋቸው፡ ይነጋገራሉ፡ እንደ፡ ዋና፡ ቋንቋ፡ ግን፡ አይነጋገሩበትም። ቋንቋቸው፡ ጠፍቶ፡ አማርኛ፡ አሸንፍዋቸዋልና፡ አማርኛ፡ ብቻ፡ ይናገራሉ።

ዛሬ፡ ክርስቲያን፡ ሁነው፡ በክርስቲያን፡ መሀከል፡ ሲኖሩ፡ ስራቸው፡ ሸማ፡ ብረት፡ ቆርበት፡ መሰንቆ፡ መምታት፡ አዝማሪች፡ ሀማናዎችም፡ ሌላም፡ የጅ፡ ስራ፡ የሚያቁ፡ ሰራተኞች፡ ዋናች፡ በዚሁ፡ በስራቸው፡ የታወቁና፡ የተለዩ፡ ከጋፋትና፡ ከፈላሻ፡ ዘር፡ ናቸው። እኒህም፡ ምን፡ ክርስቲያን፡ ቢሆኑ፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ይጋባሉ፡ እንጂ፡ ጨዋ፡ ከሚባል፡ ክርስቲያን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ የሚጋቡቸው፡ የለም።

ስለ፡ ነገደ፡ ጋፋት፡ ታሪክ፡ በጼ፡ ሱስንዮስ፡ ታሪክ፡ አባ፡ ጢኖ፡ በጻፈው፡ ከምዕራፍ፡ ፫፡ እስከ፡ ምዕራፍ፡ ፲፩፡ ብዙ፡ ይገኛልና፡ በዚያ፡ ተመልከት። ስለ፡ ነገደ፡ ጋፋት፡ ከሚናገር፡ ከረጅም፡ በጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ይበቃናል፡ ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የነገደ፡ ጋላን፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

## ፲፬፡ ነገደ፡ ጋላ።

ስለ፡ ነገደ፡ ጋላ፡ የሚነገር፡ ቁም፡ ነገርና፡ ሐሰት፡ እውነትና፡ ተረት፡ የሆነ፡ በያይነቱ፡ ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ታሪክ፡ አለ።

አቶ፡ አጽሜ፡ በጻፉት፡ የታሪክ፡ መጽሐፍ፡ ስለ፡ ጋላ፡ ሲናገር፡ እንዲህ፡ ይላል፤ ጋላ፡ የሚሉት፡ ሕዝብ፡ ካገሩ፡ የወጣበት፡ ምክንያት፡ እጅግ፡ አይታወቅም። ባለ፡ ታሪኮች፡ እኒህ፡ የጋላ፡ ሕዝብ፡ ከእስያ፡ ፈልሰው፡ ወደ፡ ማዳጋስካር፡ እንደ፡ ተሻገሩ፡ ከዚያም፡ ፈልሰው፡ በባሳ፡ አጠገብ፡ ከባሕር፡ ወደብ፡ ተቀመጡ። በባሳ፡ ማለት፡ በጋሊኛ፡ ለሰውም፡ ለከብትም፡ መሰማሪያ፡ ማለት፡ ነው። ከዚያም፡ ገናሌ፡ የሚባለውን፡ ወንዝ፡ ተከትለው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ወጡ፡ ይላሉ። ካገራቸው፡ ሲወጡ፡ ግን፡ ሁሉ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ አልወጡም። የወደደ፡ ወጣ፡ ያልወደደ፡ ቀረ፡ እንጂ።

ይህ፡ ጋላ፡ የተባለ፡ ሕዝብ፡ ከዚያ፡ ተነሥቶ፡ መጣና፡ በባሌ፡ ዳር፡ ገባና፡ በሚሉት፡ ወንዝ፡ ተቀመጠ። ላሙንና፡ ፍየሉን፡ በጉን፡ እያረ



www.ethiopianorthodox.org

ባ፡ እንደ፡ ዘላን፡ ሁኖ፡ ኖረ። ከመጣም፡ ከጼ፡ ልብነ፡ ድንግል፡ ስመ፡ መንግሥታቸው፡ ወናግ፡ ሰገድ፡ ከርሳቸው፡ መንግሥት፡ በፊት፡ ፻፬፡ ዓመት፡ ሁኖት፡ ነበር። ይህም፡ አጼ፡ ይስሐቅ፡ በነሡ፡ በ፳ዓመት፡ በ፮ ሺ፱፻፬፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በ፲፬፻፬፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ነው፡ የሚሉ። እ ውነተኛው፡ የጋሎች፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መውጣት፡ ግን፡ መሬ፡ ተክ ለ፡ ሃይማኖት፡ ስመ፡ መንግሥቱ፡ ዘጓ፡ በነገሠ፡ በ፲፡ ዓመት፡ በ፲፭፻፵፩፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ነው።

ፈረንጆች፡ ስለ፡ ጋላ፡ የጻፉት፡ በራስ፡ አውቀትና፡ በምርምር፡ ነው። እኛ፡ ግን፡ ከገፉ፡ ውስጥ፡ የሚገኘውን፡ አዘጋጁ፡ ጤኖ፡ የጻፈውን፡ ታሪክ፡ አይተን፡ ነው።

ጋሎች፡ ሲመጡ፡ በገላኔ፡ ወንዝ፡ መጥተው፡ ሆር፡ ውላቦ፡ በሚባል፡ አገር፡ ገቡ። በሆር፡ ውላቦ፡ ዋንተኛ፡ በዋና፡ የሚቆርጣትና፡ የሚሻገሯት፡ ትንሽ፡ ኩሬ፡ ባሕር፡ አላት። ጋሎች፡ አባታችንና፡ ፍጥረታችን፡ ከዚህ፡ ወጣን፡ ይላሉ። ስለዚህም፡ ኡሜን፡ ውላቦ፡ ቡቴ፡ ይላሉ። ይህም፡ ከውላቦ፡ ውሃ፡ ወይም፡ ባሕር፡ ፍጥረት፡ ወጣ፡ ማለት፡ ነው። ስለዚህ፡ ጋሎች፡ ለውሃ፡ ይሰግዳሉ። ሰውም፡ እንስሳም፡ ከዝያች፡ ውሃ፡ አይጠጣም፡ ክልክል፡ ነው። ጋላ፡ ሁሉ፡ ከዚያ፡ ለውሃዶቱ፡ ይሰግዳል። ከዚያ፡ ብዙ፡ ሰንጋ፡ ፍሪዳ፡ በግ፡ ፍየልም፡ ያርዳሉ። በሆር፡ ውላቦ፡ ልዩ፡ ቋንቋ፡ ያላቸው፡ ጥቂት፡ ሕዝብ፡ አሉ፡ ዶራስ፡ ይባላሉ። የጋላ፡ ሕዝብ፡ ይመስላሉ። ከሲዳሞ፡ እስከ፡ ውላቡ፡ ፴፡ ቀን፡ ከውላቡ፡ እስከ፡ ቦረን፡ ፳፡ ቀን፡ ያስኬዳል።

ስለ፡ ጋላ፡ ትውልድ፤ የጋላ፡ ትውልድ፡ እንዲህ፡ ነው። ጋሎች፡ ሁለት፡ ነገድ፡ ናቸው፤ በርቱማ፡ ቦረን፡ ይባላሉ። ወንድማማች፡ ናቸው። በርቱማ፡ ፮፡ ቦረን፡ ፲፩። ሁለቱ፡ ወንድማማች፡ ፲፯፡ ልጆች፡ ወለዱ። የበርቱማ፡ ልጆች፡ እሌሁ፡ ናቸው፤ ከረዩ፡ መረዋ፡ ኢቱ፡ አከቹ፡ ወረንሻ፡ ሁበና፡ ናቸው። የከረዩ፡ ልጆች፡ ስምንት፡ ናቸው፤ ሊበን፡ ሜጫ፡ ቱለማ፡ ወሎ፡ ጅሌ፡ አቦ፡ ሉባ፡ በላአ። የመረዋ፡ ልጆች፡ ፬፡ ናቸው፤ ወርድያን፡ አሩሲ፡ ኢቱ፡ ጥሙጋ፡ ናቸው። ወርድያን፡ ፫፡ ይወልዳል፤ አና፡ ኡር፡ አበጢ። እኒህ፡ ሁሉ፡ የመረዋ፡ ልጆች፡ በኃይልና፡ በብዛት፡ ከሁሉ፡ ይበልጣሉ። የኢቱ፡ ልጆች፡ ፪፡ ናቸው፤ ጅሌ፡ ሉባ። የአከቹ፡ ልጆች፡ ፪፡ ናቸው፤ ጅንጉር፡ ጨፋ። የወረንሻ፡ ልጆች፡ ፰፡ ናቸው፤ ሰዶ፡ አቦ፡ ጫቦ፡ ይሉ፡ ጉድሩ፡ ኩታይ፡ አምሩ፡ ሁሮ፡ ናቸው። የሁበና፡ ልጆች፡ ፫፤ ራያ፡ አዘቦ፡ ሀሽንጌ፡ ናቸው። ከነዚህ

www.ethiopianorthodox.org

የሜጫ፡ ልጆች፡ ከጋላ፡ ቤት፡ ሜጫ፡ ከታላላቆች፡ ተነሥተው፡ ለኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ የጌታ፡ አደሩ፡ ንጉሡም፡ አጼ፡ ዐምደ፡ ጽዮን፡ ነው። እርሱም፡ በመልካም፡ ተቀብሎ፡ በጣና፡ በሕርና፡ በዳሞት፡ መሀከል፡ አገር፡ ሰጣቸው። እነርሳቸው፡ ያን፡ አገር፡ ተቀብለው፡ ያዙና፡ ስሙን፡ በባታቸው፡ ስም፡ ሜጫ፡ አሉት። ከዚህ፡ በኋላ፡ ክርስትና፡ ተነሥተው፡ አብያተ፡ ክርስቲያናትን፡ በተቀበሉት፡ አገር፡ ሁሉ፡ ሠርተው፡ ክርስትያኖች፡ ሁነው፡ ተቀመጡ። በማራ፡ ሕዝብ፡ መሀከል፡ ጋልኛን፡ ፈጽመው፡ አጥፍተው፡ በማርኛ፡ ቋንቋ፡ ብቻ፡ ይናገራሉ።

የወሎ፡ ልጆችም፡ የያዙት፡ አገር፡ በማራ፡ ሕዝብ፡ መከከል፡ ስለ፡ ሆነ፡ ጋልኛን፡ አጥፍተው፡ በማርኛ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ። ጥንት፡ ክርስቲያን፡ ሁነው፡ ብዙ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ የከበሩ፡ አድባራት፡ አትሮንስ፡ ማርያም፡ መከነ፡ ሥላሴ፡ ደብረ፡ ገነት፡ ገነተ፡ ጊዮርጊስ፡ እኒህን፡ የመሰሉ፡ ብዙ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ነበሩባቸው። አገሩ፡ ጥንት፡ ላኮ፡ መልዛ፡ ይባል፡ ነበር፤ በኋላ፡ የወሎ፡ ልጆች፡ ከያዙት፡ ግን፡ ያገሩን፡ ስም፡ ለውጠው፡ በባታቸው፡ ስም፡ ወሎ፡ አሉት። ግራኝ፡ በግራቸው፡ ውስጥ፡ የነበሩ፡ አብያተ፡ ክርስቲያኖችን፡ አጥፍቶ፡ አቃጥሎ፡ መጻሕፍትን፡ ቆነጻጽሎ፡ ባጠፋቸው፡ የሐረርጌ፡ እስላሞችና፡ ቱቅሮች፡ ገብተው፡ የመሐመድን፡ ሃይማኖት፡ በቁርዓን፡ ባስተማርዋቸው፡ ጊዜ፡ የወሎን፡ ሰዎች፡ ፈጽመው፡ አስለሙ። አሁን፡ አጼ፡ ዮሐንስ፡ ባዋጅ፡ በግድም፡ ክርስትና፡ ቢያነሡት፡ ከንዳንድ፡ ጥቂቶች፡ በቀር፡ የቀረው፡ የወሎ፡ ሕዝብ፡ በሜዳ፡ ክርስቲያን፡ ቢመስል፡ በውስጥ፡ ግን፡ ምንም፡ እስልምናን፡ አልተውም፡ ነበር። ስለዚህ፡ አጼ፡ ዮሐንስ፡ ከሞቱ፡ ወዲህ፡ ከንዳንዶች፡ በቀር፡ በክርስትናው፡ የጸና፡ የለም። ሁሉም፡ ፈጽሞ፡ በግልጥ፡ ወደ፡ እስላምነቱ፡ ተመለሰ።

ከሁበና፡ ልጆችም፡ ከራያና፡ ከዘቦ፡ ተለይቶ፡ ሀሸንጌ፡ የትግሬ፡ ጎረቤት፡ ስለ፡ ሆነ፡ የሚበልጡት፡ ክርስትና፡ ተነሥተዋል። በስም፡ ክርስቲያኖች፡ ይባላሉ። የሚያንሡት፡ እስላሞች፡ ናቸው። በስም፡ እስላሞች፡ ይባላሉ፤ በግብራቸው፡ ግን፡ ክርስቲያኖች፡ እስላሞች፡ የሚበሉትም፡ ነፍስ፡ በመግደል፡ ደም፡ በማፍሰስ፡ ፍጹም፡ እንደ፡ ራያና፡ እንደ፡ አዘቦ፡ ጋሎች፡ ናቸው። የሀሸንጌ፡ ጋሎች፡ ጋልኛን፡ አጥፍተው፡ በትግሬኛ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ። ከመካከላቸው፡ ጥቂቶች፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈሩ፡ ክርስቲያኖች፡ ይገኛሉ፤ የቀሩት፡ ግን፡ በስም፡ ክርስቲያኖች፡ ሲባሉ፡ ግብራቸው፡ ሁሉ፡ የአረማውን፡ ስራ፡ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ፲፫፡ የበረን፡ ልጆች።

ዶጨ፡ ጅሌ፡ ከኖ፡ በቾ፡ እኒህ፡ ቱለማ፡ ይባላሉ። አከኮ፡ ወበ፡ ሉባ፡ እኒህ፡ ሰደቻ፡ ይባላሉ። ጭሌ፡ ሊበን፡ ጉድሩ፡ ሆኮ፡ እኒህ፡ ሆኮ፡ ይባላሉ። እኒህ፡ ፲፩ዱ፡ የበረን፡ ልጆች፡ ፳፡ ልጆች፡ ወለዱ። የዶጨ፡ ልጆች፡ ፪፡ የጅሌ፡ ፪፡ የከኖ፡ ፫፡ የበቾ፡ የ፪፡ አከኮ፡ ፪፡ የወበ፡ ፪፡ የ ጭሌ፡ ፪፡ የሉባ፡ ፪፡ የሊበን፡ ፩፡ የጉድሩ፡ ፩፡ የሆኮ፡ ፩፡ ሁሉም፡ በድምሩ፡ ፳፡ ይሆናሉ።

ስማቸውም፡ እኒህ፡ ናቸው፡ የዶጨ፡ ልጆች፡ ፪፡ ሌቃ፡ ጨለባ፡ የጅሌ፡ ልጆች፡ ፪፡ ወሊጋ፡ ጉማ፡ የከኖ፡ ልጆች፡ ፫፡ ሊሙ፡ ጅማ፡ ጌራ፡ የበቾ፡ ልጆች፡ ፪፡ አብቹ፡ ግምብቹ፡ ያከኮ፡ ልጆች፡ ፪፡ ወበራ፡ ገላን፡ የወበ፡ ልጆች፡ ፪፡ ሉሜ፡ ሊበን፡ የሉባ፡ ልጆች፡ ፪፡ ሜታ፡ ቀዬ፡ የጭሌ፡ ልጆች፡ ፪፡ ጉለሌ፡ ስላሌ፡ የሊበን፡ ልጅ፡ ፩፡ አብቹ፡ የጉድሩ፡ ልጅ፡ ፩፡ ደራ፡ የሆኮ፡ ልጅ፡ ፩፡ በረና። እኒህ፡ የበርቱማ፡ ፳፯፡ የበረን፡ ፳፡ ድሙሩ፡ ፵፯፡ ዋኖች፡ የገላ፡ አባቶች፡ ናቸው።

እኒህም፡ በጥቂት፡ ተራቡና፡ እጅግ፡ በዙ። ከብዛታቸውም፡ የተነ ሣ፡ እየገፉ፡ ክርስቲያኑን፡ እያጠፉና፡ እያቃጠሉ፡ የክርስቲያንን፡ አገር፡ ሁሉ፡ በኢትዮጵያ፡ ወረሱ። በኢትዮጵያ፡ ያ፡ ሁሉ፡ ጉዳትና፡ ጥፋት፡ የሆነ፡ በነገሥታቱ፡ ቸልተኝነት፡ በመኳንንቱ፡ ትዕቢትና፡ እርስ፡ በር ሳቸው፡ ፍቅር፡ በማጣት፡ በሕዝቡም፡ እርስበርሱ፡ ባለመስማማት፡ በ መለያየት፡ መንግሥት፡ ቢደክም፡ አገርም፡ እርስበርሱ፡ በሁከት፡ ተበ ላሽቶ፡ አንድነትና፡ መሰማማት፡ ብርቱ፡ ኃይል፡ የሚሆን፡ ቢጠፋ፡ ነው።

ዛሬ፡ ጋላ፡ በያዘው፡ አገር፡ ውስጥ፡ ጥንት፡ የክርስቲያን፡ አገር፡ እንደነበረ፡ በግልጥ፡ የሚያስረዳ፡ ከሐረር፡ እስከ፡ በላይ፡ በረና፡ ከከፋ፡ እስከ፡ ራያና፡ አዘቦ፡ ባለው፡ ጋላ፡ በያዘው፡ አገር፡ ሁሉ፡ የመንግሥት፡ ቤት፡ የኖራ፡ ግምብ፡ ፍራሽ፡ ከተማ፡ የነበሩ፡ የከበሩ፡ አብያተ፡ ክርስ ቲያናት፡ የንዋየ፡ ቅድሳት፡ የጻሕል፡ የጻውድ፡ የመስቀል፡ የአክሊል፡ የመቋሚያ፡ የጻናጽል፡ ስባሪና፡ ሌላም፡ ሁሉ፡ ደኅና፡ ተፍራሽ፡ ውስጥ፡ ተቀብሮ፡ የኖረው፡ አፈር፡ ሲልቶት፡ አሁን፡ በዘመናችን፡ በደግማዊ፡ ምኒልክ፡ ጊዜ፡ እየተቆፈረ፡ በብዙ፡ ስፍራ፡ ወጣ። ደግሞ፡ በየዋሻው፡ ጋላ፡ ሲዘርፋቸው፡ ሸሽገው፡ ያኖሩት፡ ብዙ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ አል ባሳት፡ ከብዙ፡ ዘመን፡ መኖር፡ ብል፡ በልቶት፡ የሌት፡ ወፍ፡ ቀዳጅቶ፡ ንዋየ፡ ቅድሳት፡ መጻሕፍትም፡ እስከ፡ ዛሬ፡ እየተመረመረ፡ ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

ስለ፡ ጋላ፡ ታሪክ፡ በውነትም፡ በሐሰት፡ ተረትም፡ የተጻፈ፡ ብዙ፡ ነውና፡ በምሉ፡ ታሪኩን፡ ልትመረምርና፡ ልታውቅ፡ ብትወድ፡ በክብረ፡ ነገሥት፡ ተጽፎአልና፡ ከገጽ፡ ፻፶፱፡—፪፻፵፫፡ ልብ፡ አድርገህ፡ ተመልከት።

ስለ፡ ጋላ፡ ከሚነገር፡ ታሪክ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ይበቃናል። ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የእናሪያን፡ ሕዝብ፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

## ፲፮፡ ነገደ፡ እናሪያ።

የእናሪያ፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ የካም፡ ዘር፡ ነው። ነገደ፡ ዮቅጣን፡ መመጥተው፡ የነገደ፡ ኩሳን፡ መንግሥት፡ በወሰዱ፡ ሕዝቡንም፡ በጦር፡ አጥፍተው፡ የተረፈውና፡ ባሳደዱ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ዶቡብ፡ ዳር፡ ለዳር፡ በወላሞ፡ በሲዳሞ፡ በኩሎ፡ በከንታ፡ በአማር፡ በዝንጀሮ፡ የሚኖር፡ ሕዝብ፡ ነው። እርሱም፡ ከጦር፡ በኋላ፡ ከነገደ፡ ዮቅጣን፡ ገብቶ፡ ለነርሳቸው፡ እጅ፡ ነሥቶ፡ ተገዝቶ፡ ታዞ፡ ገብሮ፡ የሚኖር፡ ነው። ቀድሞ፡ ጋሎች፡ ሳይዙት፡ ሉቅማ፡ ጅማ፡ ሌቃ፡ ትቤ፡ ከፋ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የእናሪያ፡ ሕዝብ፡ አገር፡ ነበር።

ይህ፡ ሁሉ፡ ከቀድሞ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ ዘመን፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ እስከ፡ ዘመነ፡ ክርስትና፡ ተያይዞ፡ እንደ፡ መጣ፡ አንድ፡ እናሪያ፡ ተብሎ፡ ከንጉሠ፡ ነገሥት፡ በታች፡ አንድ፡ ንጉሥ፡ ይሾምበት፡ ይነግሥበት፡ ነበር።

ይህም፡ ሊታወቅ፡ ስለ፡ ቀዳማዊ፡ ምኒልክ፡ በሚናገረው፡ ዙዋይ፡ በተገኘው፡ ታሪክ፡ እንዲህ፡ ይላል፤ አብሂል፡ ከብንያም፡ ነገድ፡ አልጋው፡ ዙፋኑ፡ ከብሮ፡ የተሠራለት፡ ንጉሥ፡ ነበር። ግዛቱም፡ ሉቅማ፡ ጅማ፡ ሌቃ፡ ትቤ፡ ጉማ፡ ከተማውም፡ ከፋ፡ አገር፡ እናሪያ፡ ነው። እሱም፡ ለንጉሠ፡ ነገሥት፡ ይታዘዛል፡ በማለቱ፡ ይታያል።

የእናሪያ፡ ከተማ፡ የወላሞ፡ ዳሞት፡ ሀዲያ፡ ኪንዶ፡ ወይም፡ ሀንድ፡ የሚባል፡ ነበር። ቀድሞ፡ ተጠቅልሎ፡ ባንድ፡ ንጉሥ፡ ይገዛ፡ ነበር። እንደ፡ ገበዘ፡ አክሱም፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ የዝንጅሮ፡ ንጉሥ፡ ነበረ። በረበኛ፡ ዝርን፡ ማለት፡ ባለ፡ ግርማ፡ የሚያንቀጠቅጥ፡ ማለት፡ ነው። ጅሮ፡ ማለት፡ ድሮ፡ ዘመን፡ ይመስላል፡ ስለዚህ፡ ዝንጅሮ፡ ማለት፡ የድሮ፡ ባለ፡ ግርማ፡ ንጉሥ፡ ማለት፡ ይሆናል፡ እርግጡ፡ ግን፡ አልታወቀም።

www.ethiopianorthodox.org

የእናሬያ፡ ሕዝብ፡ በጼ፡ ያግብአ፡ ጽዮን፡ ዘመን፡ በ፲፡ ፻፰፭፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ በአቡነ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት፡ ስብከት፡ አምኖ፡ ተቀብሎ፡ ክርስቲያን፡ ሁኖ፡ የነበረ፡ የኢትዮጵያ፡ ነገሥታት፡ ኃይል፡ እየደከመ፡ እየጣረ፡ ወደኋላ፡ እያለ፡ በሄደ፡ ጊዜ፡ ጋላ፡ ወረሳ፡ እየመታ፡ አገሩን፡ እየወረረ፡ መምህራኑን፡ ካህናቱን፡ እየገደለ፡ መጻሕፍቱን፡ ቤተ፡ ክርስቲያኑን፡ እያቃጠለ፡ ቢያጠፋው፡ ከሞት፡ የተረፈው፡ ሕዝቡም፡ የሚያስተምረው፡ ቢያጣ፡ እንደ፡ ገና፡ ተመልሶ፡ አረማዊ፡ ሆነ። የክርስትናን፡ ሃይማኖት፡ አጥፍቶ፡ በዘንዶና፡ በዛር፡ አመለከ። ጥንት፡ የእናሬያ፡ አገር፡ ክርስቲያን፡ እንደነበረ፡ ዛሬውን፡ የሚያስረዳ፡ በገሩ፡ ውስጥ፡ በብዙ፡ ስፍራ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሕንጻ፡ ፍፍራሽ፡ የመስቀል፡ የጽና፡ ሴላም፡ የንዋየ፡ ቅድሳት፡ ስባሪና፡ ምልክት፡ የመጻሕፍትም፡ ቍራጭ፡ ይገኛል። በንዳንድ፡ ስፍራም፡ በአየዋሸው፡ ታቦታቱ፡ መጻሕፍቱ፡ ንዋየ፡ ቅድሳቱ፡ አልባሳቱ፡ ሁሉ፡ ይገኛል።

ክርስትና፡ ከጠፋባቸው፡ ወዲህ፡ የእናሬያ፡ ሕዝብ፡ በዘንዶና፡ በዛር፡ እንዳመለኩ፡ የሚያስረዳ፡ ከዚያ፡ ወዲህ፡ የሚነገሥ፡ የጅንጀሮ፡ ንጉሥ፡ ለዘንዶ፡ ይገብራል፡ ንጉሡም፡ በለ፡ ብዙ፡ ምሽት፡ ነው። ደግሞ፡ በግዛቱ፡ ውስጥ፡ ያለችውን፡ የጨዋ፡ ወገን፡ የምትባል፡ የበለጌም፡ የድሀም፡ የበለጸጋም፡ ልጅ፡ ብትሆን፡ ሳይለይ፡ ይደርስባታል። ብዙም፡ ይወልዳል፡ በሞተ፡ ጊዜ፡ ልጆቹን፡ ሁሉ፡ ይሰበስቡዋቸዋል። ፶ም፡ ፷ም፡ ከስከ፡ ፻ም፡ ቢሆኑ፡ ከዘንዶው፡ በታ፡ ይወስድዋቸዋል። መናገሻው፡ ከዚያ፡ ነውና፡ ልጆችም፡ ከዚያ፡ በንድ፡ በታ፡ ይቀመጣሉ። ያልታወቁም፡ ልጆች፡ በዚያን፡ ሌት፡ ይመጣሉ። እናቶቻቸው፡ እኛም፡ ከንጉሡ፡ ነው፡ የወለድናቸው፡ እያሉ፡ ያመጥዋቸዋልና፡ ያቀላቀላቸዋል። ብዙ፡ ከብትም፡ በያይነቱ፡ ይታረዳል። የተሰበሰበው፡ ሕዝብ፡ ፩፡ ሺህ፡ ከንድ፡ የሚሆን፡ ከልጆቹ፡ ርቆ፡ ቁሞ፡ ከልቡ፡ እየጮኸ፡ በልዩ፡ ልዩ፡ ዜማ፡ እየዘፈነ፡ ይጨፍራል። ጬኸቱና፡ ዘፈኑ፡ ማጉራቱም፡ በደመቀ፡ ጊዜ፡ ዘንዶው፡ ከጕሬው፡ መዘዝ፡ ብሎ፡ ይውጣል። ከታረደው፡ ከደሙ፡ ሁሉ፡ ይቀምሳል።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ከልጆቹ፡ ባንዱ፡ ላይ፡ ይጠመጠማል። የቀሩቱ፡ ወንድሞቹ፡ ፈጥነው፡ ተነሥተው፡ በግምባራቸው፡ ተደፍተው፡ ይሰግዳሉ። ከሩቅ፡ ያለው፡ ዘፋኙና፡ ጨፋሪው፡ ሕዝብም፡ እየሮጠ፡ ይቀርባል፡ ሰግዶም፡ ይደፋል፡ ቀቢው፡ ዘንዶው፡ ተተርትሩለት፡ ይሄዳል፡ ከጕሬውም፡ ይገባል።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ፡ የተቀባ፡ ንጉሥ፥ ይነሣል፡ ሕዝቡንም፡ ተነሣ፥ ይለዋል፤ ሕዝብም፡ ተነሥቶ፥ ይሰግድለታል። የቀሩቱ፡ ወንድሞቹ፥ ግን፡ ከዚያ፡ ቀን፡ ወዲህ፡ እንደ፥ ሕዝቡ፡ ናቸው፥ እንጂ፡ ከንጉሥ፡ ዘር፡ ቍጥር፡ የላቸውም። የሰጊዱን፡ ሥራት፡ ከፈጸመ፥ በኋላ፥ እንደ፡ ወግ፥ ግብር፡ ይገባል። ያ፡ የታረደው፥ ሥጋ፥ ቀርቦ፡ ይበላል፥ የተረፈውንም፥ ከቤት፥ አያገቡትም። ከዚያው፡ ጥለውት፡ ይሄዳሉ። ሥራታቸውና፡ ወጋቸው፡ እንዲሁ፡ ነውና።

የተሰበሰበው፥ ልዩ፡ ልዩ፡ ጎሳ፥ ልዩ፡ ልዩ፡ ነገድ፡ ስለሆነ፥ የሚበላውን፡ እንደ፥ ጠባዩ፡ እንደ፥ ጠባዩ፡ ያቀርቡለታል። አሁን፡ አማሮችና፥ ትግሮች፥ የሹልዳ፥ ሥጋ፥ አይበሉም፤ የእስራኤል፡ ልጆች፥ ነን፥ ይላሉና፥ ይልቁንም፥ ነገሥታትና፥ የነገሥታት፡ ዘር፡ አለን፡ የሚሉ፡ ሁሉ፥ አይበሉም። እርማቸው፡ ነው። በኦሪት፡ ዘፍጥረት፡ ምዕራፍ፡ ፴፪፡ ቍጥር፡ ፴፪፡ እንደ፡ ተጻፈ፡ ስለዚህ፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ ሹልዳ፡ አይበሉም፥ እስከ፡ ዛሬ፥ ድረስ። እግዚአብሔር፡ የያዕቆብን፡ ጭን፡ (ሹልዳ፡) ዳሰ፡ አፍዝዞታልና፡ ያለውን፡ ይዘው። በዚህም፡ አማሮችና፡ ትግሮች፡ ይከሩበታል። ሹልዳ፡ አንበላም፡ በማለት፥ የእስራኤል፡ ልጆች፡ መሆናቸውን፡ ይመሰክራሉ።

እንዲሁም፡ እኩሉ፥ በሬት፡ ወይም፡ ዳሞት፥ የሚባሉት፡ የአናሬያ፡ ሕዝብ፡ ፍየል፡ የማይበሉ፡ አሉ። በግም፥ የማይበሉ፥ ዶሮም፡ ዓሣም፥ ተልባም፥ የማይበሉ፡ አሉ። በየጠባያቸው፡ ያቀርቡላቸዋል፡ የተባለ፡ ስለዚህ፡ ነው። ስለዚህም፡ በየክህናታቸው፥ በየዘር፡ ፈረሱ፥ በየቃልቻው፡ እንደ፡ ወጉ፡ ይቀርብላቸዋል።

ይህን፡ መሥዋዕት፡ ከበሉ፡ ከጠገቡም፥ በኋላ፡ የተረፈውን፡ ከዚያው፡ ጥለው፥ ንጉሡን፡ እያጀቡ፥ እየዘፈኑ፥ ወደ፡ ቤተ፡ መንግሥቱ፡ ያገቡታል። እሱም፡ ከቤቱ፥ ገብቶ፥ ከዝሙት፥ በቀር፡ ሌላ፡ ስራ፥ የለውም።

ከዚህ፡ በኋላ፡ በዙሪያው፥ ያሉ፡ ነገሥታት፡ ወደርሱ፡ መልክተኞቻቸውን፡ ይልካሉ። ሕያው፡ ንጉሥ፥ ለማለትና፡ ከመንፈሱ፡ እንዲልክላቸው፡ በረከቱም፡ እንዲደርስላቸው፡ በየመንግሥቱ፥ ያለው፥ የዘር፡ አለቃ፡ ሁሉ፥ ይሄዳል፡ ከንጉሡ፡ ይባረካል። በዘንዶ፡ መጠምጠም፥ የለዘበ፡ ገላውን፥ ይዳስስና፡ እጁን፡ ጨብጦ፥ ከሰው፥ ሳይነጋገር፡ ወዳገሩ፡ ንጉሥ፥ በግስገሳ፡ ይደርሳል። የንጉሡንም፡ ገላ፥ በዚያ፡ እጁ፡ ይዳስስና፥ ከእጁ፥ እንዳይቀር፥ በውሃ፥ ከንጉሡ፡ ራስ፡ ላይ፡ ይታጠባል፥ በዚያ፥ ይባረካል።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ፡ ሥራት፡ እስከሁን፡ እስከ፡ ዘመናችን፡ ይደረግ፡ ነበር። እስከ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘመን፡ ድረስ፡ ይሆን፡ ነበር። የሚልኩ፡ ነገሥታትም፡ የከፋ፡ የኩሎ፡ የከንታ፡ የከምባታ፡ የወላሞ፡ የቀፉትም፡ ሁሉ፡ በዙሪያው፡ ያሉ፡ አገሮች፡ ነገሥታት፡ ናቸው።

በዚያው፡ ንጉሡ፡ በተዳሰሰበት፡ ቀን፡ ታላቅ፡ በዓል፡ ያደርጋል፡ የዛር፡ ዘፈን፡ ይዘፈናል። በነዚህ፡ ነገሥታት፡ የሚሾመው፡ የዛር፡ አለቃ፡ በሴትና፡ በግዛት፡ እየተቃኑ፡ ከንጉሡ፡ ጋራ፡ አይጣሉ፡ አይፋቀፉም። ስለዚህ፡ አሁን፡ በኛ፡ ጊዜ፡ የነገሡ፡ የከፋ፡ ንጉሥ፡ ከሞ፡ የሮ፡ የሚባል፡ ከገርንጅሮ፡ ከተቀበ፡ በኋላ፡ የዛርንም፡ አለቅነት፡ ጨምሮ፡ ይዞ፡ ንጉሥና፡ የዛር፡ አለቃ፡ ሆነ። ከዚህ፡ በኋላ፡ ልጆቹም፡ እንደዚሁ፡ የቀፉቱም፡ ነገሥታት፡ የዛር፡ አለቅነትን፡ ደርበዋል።

ዛርን፡ የሰደበ፡ የሚፈርድበት፡ ከገርንጅሮ፡ ነው። በተፈረደበትም፡ ጊዜ፡ ለዘንዶው፡ ይሰጣልና፡ ይውጠዋል። ጥንት፡ ነገሥታቱ፡ ክርስቲያኖች፡ ሳሉ፡ ለዚህ፡ ፍርድ፡ አሳልፈው፡ አይሰጡም፡ ነበሩ፡ አሁን፡ ግን፡ አረማውያን፡ ሁነው፡ የዛር፡ አለቅነትን፡ ከደረቡ፡ በኋላ፡ ሰጡ።

አስቀድመን፡ እንደ፡ ጻፍነው፡ በእናሬያ፡ በዘመኑ፡ ክርስትና፡ የክርስቲያን፡ ጨዋ፡ ወታደር፡ ተሰራበትና፡ ከክርስቲያን፡ ተቋርጦ፡ የቀረ፡ የቄሱ፡ ልጅ፡ ቄስ፡ የሹም፡ ልጅ፡ ሹም፡ የጨዋው፡ ልጅ፡ ጨዋ፡ እየሆነ፡ በየተሠራበት፡ አገር፡ ይኖር፡ ነበር።

እንደዚሁም፡ ሁሉ፡ ሰንጋ፡ በከ፡ በላይ፡ ብለት፡ የምትባል፡ አገር፡ ትንሽ፡ ከረፍታ፡ አለች። ዛሬ፡ ያቡን፡ ተክለ፡ ሃይማኖት፡ ታቦት፡ ተተክሎበታል፡ ጥንት፡ በዚያ፡ ስፍራ፡ ታላቅ፡ ቤተ፡ ጣዖት፡ ቤተ፡ ደስክ፡ የሚባል፡ የዛር፡ መቅደስ፡ ነበር። የክርስቲያን፡ ነገሥታት፡ መኳንንቱም፡ ዘመቻ፡ ሲነሡ፡ ከዚያ፡ ይሰፍሩና፡ ከዛሩ፡ አለቃ፡ ምክር፡ ተቀብለው፡ ይዘምቱ፡ ነበሩ። ባገሩም፡ የነበሩ፡ የጋፋት፡ ሕዝብ፡ አምልኳቸው፡ በዚህ፡ ቤተ፡ ደስክ፡ ነበረ። ይህነንም፡ ቤተ፡ ደስክ፡ በኋላ፡ አቡነ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት፡ አፈረሱት፡ ይባላል።

ስለ፡ ነገደ፡ እናሪያ፡ ከሚነገር፡ ታሪክ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ይበቃናል፡ ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የነገደ፡ እስላምን፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

www.ethiopianorthodox.org

## ፲፯፡ ንገደ፡ እስላም።

በ፮፻፰፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ የእስላሞች፡ ነቢይና፡ ንጉሥ፡ በምስራቅ፡ አገር፡ በእስያ፡ መሐመድ፡ ተነሣ፡ የምስራቅን፡ አገር፡ ገለባበጠ። ወደ፡ ሐበሻ፡ ግን፡ አልቀረበም፡ ነገር፡ ግን፡ በዓረብ፡ አገር፡ የነበረውን፡ እስከ፡ ሱዳን፡ ያለውን፡ የኢትዮጵያን፡ ግዛትዋን፡ እስከ፡ ሀብትዋ፡ ወሰደባት። እንዲሁም፡ በሰሜን፡ በኩል፡ አጉደለባት፡ የሚያስፈራው፡ ክበዳው፡ ሰይፉ፡ ግን፡ አልደረሰባትም። በተራራ፡ የታጠረች፡ ኢትዮጵያ፡ በክርስቲያን፡ መጠበቅ፡ ዳነች።

አጼ፡ ዓምደ፡ ጽዮን፡ በነገሡ፡ በ፲፡ ዓመት፡ በሺ፡ ፫፻፲፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ከብዙ፡ ትዕግሥት፡ በኋላ፡ ከረሺት፡ የሚባሉ፡ የእስላም፡ ሕዝብ፡ ዐሚሮች፡ እየሆኑ፡ ከዓረብ፡ አገር፡ ተነሥተው፡ መጥተው፡ የበሕሩን፡ ወደብ፡ ዳርዳሩን፡ ይይዙ፡ ጀመሩ። ነገር፡ ግን፡ ከሐበሻ፡ ንጉሥ፡ በታች፡ ሁነን፡ እንገብራለን፡ ብለው፡ ነበሩ። እንዲህም፡ ማለታቸው፡ እስክንበረታ፡ ብለው፡ ነው፡ እንጂ፡ ቃላቸው፡ እውነት፡ አልነበረም። የመጡትም፡ ዱዋሮን፡ ታሪሂን፡ ገድኤትን፡ አዴልን፡ ይፋትን፡ ባሊን፡ ደራን፡ ሌላም፡ አገር፡ ያዙ።

የኢትዮጵያ፡ ነግሥታት፡ በችሎታኛነት፡ በመታለል፡ ዝም፡ ባላሉዋቸው፡ እነዚህ፡ ሳይጠነክሩ፡ ቢወጉዋቸው፡ በኋላ፡ መከራ፡ አይጠነክርባቸውም፡ ነበር፡ ነገር፡ ግን፡ በዚያ፡ ዘመን፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሁከትና፡ ሽብር፡ ሁኖ፡ ነበርና፡ ይህ፡ ለእስላሞች፡ ብዙ፡ ጥቅም፡ ሆነላቸው።

በይፋት፡ ያሉ፡ እስላሞች፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ ናቸው፤ አርጎባ፡ ዶባ፡ ሽጉራ፡ ቃጭና፡ የዓሊ፡ ገዳዮች፡ ናቸው። ዓሊ፡ የመሐመድ፡ አማች፡ የፋጢማ፡ የልጁ፡ ባል፡ ነው።

የእስላሞች፡ የመጀመሪያ፡ ንጉሥና፡ ነቢይ፡ መሐመድ፡ በመዲና፡ ነገሠ። መዲና፡ ማለት፡ በግዕዝና፡ በረብ፡ ቋንቋ፡ ከተማ፡ ማለት፡ ነዉ። መሐመድ፡ ፷፫፡ ዓመት፡ ነገሠ፡ ሞተም። ከርሱ፡ ቀጥሎ፡ አበጋዝ፡ ዐሚር፡ አቡበከር፡ ሰዲቅ፡ ከሊፋ፡ ሆነ፤ ማለት፡ ነገሠ፡ ዘመነ፡ መንግሥቱ፡ ፪፡ ዓመት፡ ከ፫፡ ወር፡ ነው። ከርሱ፡ ቀጥሎ፡ ዑመር፡ እብኑ፡ አልሐጣብ፡ ከሊፋ፡ ሆነ፡ ኢየሩሳሌምን፡ ምስስርንም፡ ያዘ። ፲፡ ዓመት፡ ነገሠ፡ ሞተም። ከርሱ፡ ቀጥሎ፡ ኡስማን፡ እብኑ፡ ሐፋን፡ ከሊፋ፡ ሆነ፡ እስክንድርያን፡ ያዘ። የኢትዮጵያ፡ አገሮች፡ መርዌ፡ በለውና፡ ከለው፡ በርሱ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘመን፡ አሰለሙ። ይህን፡ ሁሉ፡ አገር፡ አስልሞ፡ በነገሠ፡ በ፡ ፲፱፡ ዓ ምት፡ ሞተ። ከርሱ፡ ቀጥሎ፡ ዓሊ፡ የፋጢማ፡ ባል፡ ነገሠ። በነሱ፡ ቁ ጥር፡ በ፡ ፴፫፡ ዓመት፡ እሱም፡ ዓሊ፡ በነግሠ፡ ጊዜ፡ ከነኸርዋን፡ ኸዋር ጅን፡ የሚባሉ፡ ከእስላሞች፡ የማይጋጠሙ፡ ሽፍቶች፡ ነበሩ፡ ዓሊ፡ ፈጃቸው። ከ፡ ፬ሺ፡ ፻፡ ሰዎች፡ ብቻ፡ ሲያመልጡ፡ ሁሉን፡ አረዳቸው። ከነኸረዋን፡ ቀጣሚት፡ የምትባል፡ አንዲት፡ ሴት፡ ነበረች፡ ከኸዋርጀ ዋን፡ ነበሩና፡ አባትዋን፡ ባልዋን፡ ወንድሞችዋንም፡ ዓሊ፡ ፈጃቸው።

እኒህ፡ ከዓሊ፡ ሰይፍ፡ ያመለጡ፡ ሰዎች፡ እናግበሽ፡ አሉዋት። እ ሱዋም፡ እኔን፡ የሚያገባ፡ ዓሊንና፡ መዐውያን፡ አልአስን፡ እኒህን፡ ሶ ስቱን፡ የገደለ፡ ነው፡ ያለዚያ፡ ወንድ፡ አለ፡ ብዬ፡ አላገባም፡ አለቻቸ ው። እኒህም፡ ሶስቱ፡ ሶስቱን፡ ለመግደል፡ በእጣ፡ ተከፈሉ። አንዱ፡ ወደ፡ መዐውያ፡ ሄደ። መዐውያን፡ ረጅም፡ ነበረና፡ ጉልበቱን፡ አቈስ ለው፡ ሳይገድለው፡ ተያዘና፡ ተደብድቦ፡ ሞተ። መዐውያ፡ ግን፡ ከቈሰ ለው፡ በኋላ፡ ጉልበቱ፡ ደከሞአልና፡ አልወለደም። ይህ፡ መዓውያ፡ የ መሐመድ፡ ታላቁ፡ አበጋዝ፡ ነው።

ወደ፡ አልአስ፡ የሄደው፡ አሳስቶ፡ ምስለኔውን፡ ገደለና፡ ተያዘ፡ በምስር፡ ከተማ፡ በካይሮ፡ ተሰቀለ። አብነ፡ አልአስም፡ የመሐመድ፡ ታ ላቅ፡ አበጋዝ፡ ነው፡ እሱም፡ ምስርን፡ ይገዛ፡ የነበረው፡ ነው።

ወደ፡ ዓሊ፡ የሄደው፡ በመስጊድ፡ መንገድ፡ ተሸምቆ፡ ቆየውና፡ በመርዛም፡ ጦር፡ ወጋው፡ በ፫ው፡ ቀን፡ ሞተ። ዘመኑ፡ መንግሥቱ፡ ፬፡ ዓመት፡ ተ፱፡ወር፡ ነው። ገዳዩም፡ ስሙ፡ አብድራሑማን፡ ይባል፡ ነበረ። እሱም፡ ተይዞ፡ ተሰቀለ።

በይፋት፡ ያሉ፡ አርጎቦች፡ የዚህ፡ የዓሊ፡ ገዳይ፡ የአብዱራሑማን፡ ዘሮች፡ ናቸው፡ ስለዚህ፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ በዓረብ፡ አገር፡ ለመኖር፡ የማ ይቻላቸው፡ ሆነ።

ዓሊ፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ ከፋጢማ፡ የተወለደውን፡ ልጁን፡ ሐሰንን፡ አነገሡት፡ ሐሰን፡ ግን፡ እኔን፡ ልትገድሉኝ፡ ነውን፡ ብሎ፡ አልነግሥ ም፡ አለ። ስለዚህ፡ ከሊፋነትን፡ ማለት፡ አልጋን፡ በሽም፡ አበጋዝ፡ ለ ነበረው፡ ለመዐውያ፡ ሰጡት፡ እሱም፡ ከሊፋ፡ ሆነ። ስለዚህም፡ የአብ ዱራሑማን፡ ዘሮች፡ የዓሊን፡ ደም፡ በቀል፡ ስለ፡ ፈሩ፡ በይፋት፡ መጡ፡ ማለት፡ በግልጥ፡ ይፋት፡ ማለት፡ ግልጥ፡ ማለት፡ ነው።እኒህ፡ እስላሞ ች፡ በዓረብ፡ እስላሞች፡ ዘንድ፡ ከእስላም፡ አይቈጠሩም፡ ስማቸው፡ ወይም፡ አበጋዛቸው፡ ወላስማ፡ ይባላሉ። ወላስማ፡ ማለት፡ ወላ፡ እስላ

www.ethiopianorthodox.org

ም፣ ማለት፣ ነው፤ ወላ፡ እስላም፡ ማለትም፡ እስላም፡ ያይዶለ፡ ማለት፣ ነው። አባታቸው፣ ዓሊን፣ ስለ፡ ገደለ፡ ይህን፡ ስም፣ ከዓረቦች፡ ተቀበሉ፡ ይባላል። መልካቸው፣ ዓረቦችን፣ ይመስላሉ፡ ቀዮች፡ ናቸው። ቋንቋቸውም፣ ዓረብኛ፣ ነው፤ ግዕዝን፡ ይመስላል። መጀመሪያ፡ በሐበሻ፡ የገቡ፣ እስላሞች፡ ናቸው። ጥንት፡ በኢትዮጵያ፣ የነበሩ፡ ሕዝብ፡ የኢትዮጲስ፡ ልጆች፣ ሳባ፡ኖባ፡ በለው፤ ከለው፡ ናቸው። በትግሬ፡ ያሉ፣ ሕዝብ፡ የሳባ፣ ወገኖች፡ ናቸው።

የበለው፣ ልጆች፣ በድሆና፣ በሐርንን፡ በምጥዋ፡ ያሉ፣ ናቸው፤ አለቃቸው፡ ናይብ፡ ይባላል። እነሱ፣ በዓሊ፣ ጊዜ፡ አስለሙ።

የኖባ፡ አገር፣ ከአትባራ፣ ከተከዜ፣ በመለስ፡ እስከ፡ ነጭ፣ አባይ፣ ድረስ፡ ነው። ቅዱስ፡ ማቴዎስ፡ ወንጌላዊ፡ አጥምቋቸው፡ ክርስቲያኖች፡ ሁነው፣ ነበሩ፡ በዓሊ፡ ጊዜ፡ ሰለሙ። ከተማቸው፡ ከርቱም፡ ነው።

በኢትዮጵያ፣ የገቡ፣ እስላሞች፣ አራት፣ ዓይነት፣ ናቸው። መጀመሪያ፣ ሕምሬያ፡ ወይም፣ ሕምያር፡ ይባላሉ፣ ቀዮ፣ ማለት፣ ነው። ሁለትኛ፣ ትግሬ፡ ይባላሉ፡ ነጋዴ፣ ማለት፣ ነው። ሶስተኛ፣ አርጎቦች፡ ናቸው። አራተኛ፣ በመዐውያን፡ ጊዜ፣ ከዓረብ፡ አገር፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፣ ተሰድው፤ የመጡ፤ ናቸው።

ስለ፡ ነገደ፡ እስላም፡ ከሚነገር፣ ከብዙ፣ በጥቂቱ፡ ከረጅም፡ በጭሩ፡ ይህ፡ ይበቃናል፡ ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የወረሴሆችን፣ ታሪክ፣ እንጽፋለን።

## ፲፩፣ ነገደ፣ ወረሴህ።

የወረ፡ ሴሆች፣ ነገርና፣ ትውልድ፡ እንዲህ፣ ነው፤ ግራኝ፡ አሕመድ፡ ኢትዮጵያን፣ በጠፋ፣ ጊዜ፡ በሺ፡ ፭፻፲፰፣ ዓመተ፡ ምሕረት፣ ከባሕር፣ ማዶ፣ ከዓረብ፡ አገር፡ ሸህ፡ ዑመር፡ የሚባል፡ የብር፡ ዘንግ፡ የብር፡ ርከት፣ አሲዞ፡ መጣ፡ በየጁ፡ ገብቶ፡ ተቀመጠ። ሸህ፣ ዑመር፣ ብዙ፡ ሴቶች፡ አግብቶ፣ ብዙ፡ ልጆች፣ ወለደ። መንደሩ፣ ቢበዛ፡ ወረ፡ ሺህ፡ ተባለ። አሁን፡ ወረሴህ፡ የሚባሉ፡ የሱ፣ ዘሮች፡ ናቸው። ወረሸህ፡ ማለት፡ የሺህ፡ መንደር፣ ማለት፣ ነው። ልጆቹ፣ ከወረሸህ፡ ወረሴህ፡ የመባል፣ ስም፡ ተቀበሉ።

ከሼህ፣ ዑመር፡ ልጆች፣ የበህሩ፣ ወሌ፣ ይባል፡ ነበር። ወሌ፣ አብዬን፡ ወለደ። አብዬ፡ ቢወልድ፡ ባባቱ፡ ስም፣ ወሌ፡ አለው። ወሌ፡ አባ፡ ገትየን፡ ወለደ፤ አባ፡ ገትየ፡ አባ፡ ሴሩ፣ ጓንጉልን፡ ወለደ።

www.ethiopianorthodox.org

አባ፡ ሴፉ፡ ጓንጉል፡ መልኩ፡ አጅግ፡ ያማረ፡ የተዋበ፡ ነበረ። ኃይለኛ፡ ጀግና፡ ፈረሰኛ፡ ሆነ። ጀግንነቱ፡ ኃይሉም፡ በቤተ፡ መንግሥት፡ የታወቀ፡ ሆነ። ክርስትና፡ ተነሥቶ፡ የላስታንና፡ የሰለዋን፡ ባለባት፡ የራስ፡ ፋሬስን፡ እኅት፡ ወይዘሮ፡ ገለቡን፡ አገባ። ክርስትናም፡ አልተነሣ፡ በእስልምና፡ እንዳለ፡ ላስታ፡ ሂዶ፡ ዘርፎ፡ አምጥቶ፡ አገባት፡ የሚሉም፡ አሉ። ነገር፡ ግን፡ ይህ፡ እውነት፡ አይደለም፡ ሐሰት፡ ነገር፡ ነው። ጓንጉል፡ ክርስትና፡ ተነሥቶ፡ ወይዘሮ፡ ገለቡን፡ አግብቶ፡ ከወይዘሮ፡ ገለቡ፡ ራስ፡ ዓሊን፡ ወይዘሮ፡ ከፈይን፡ ራስ፡ አሊጋዝን፡ ወለደ። ራስ፡ ዓሊ፡ ደጃች፡ ፋሪስን፡ ወለዱ። ደጃች፡ ፋሪስ፡ ደጃች፡ አበይን፡ ወለዱ። የደጃች፡ አበይ፡ ልጆች፡ ብዙ፡ ናቸው።

ወይዘሮ፡ ከፈይ፡ የኢልማን፡ ዖርማን፡ ባላባት፡ መርሶ፡ በሬንቶን፡ አግብተው፡ ራስ፡ ጉግሳን፡ ደጃች፡ አሉላን፡ ወለዱ። ደጃች፡ አሉላ፡ ከወሉ፡ ይማሞች፡ ልጆች፡ ወይዘሮ፡ መነንን፡ በኋላ፡ አጼ፡ ሳህሉን፡ አግብተው፡ እቴጌ፡ የተባሉትን፡ አግብተው፡ ራስ፡ ዓሊን፡ ወለዱ። ራስ፡ ጉግሳ፡ ወይዘሮ፡ ለሚታን፡ አግብተው፡ ራስ፡ ማርየን፡ ራስ፡ ይማምን፡ ራስ፡ ዶሬን፡ ወይዘሮ፡ ሂሩትን፡ ወለዱ። ወይዘሮ፡ ሂሩት፡ የስሜኑን፡ ባላባት፡ የራስ፡ ገብሬን፡ ልጅ፡ ደጃች፡ ኃይሉ፡ ማርያምን፡ አግብተው፡ ደጃች፡ ብጡልን፡ ደጃች፡ መርሶን፡ ወንዘሮ፡ የውብ፡ ዳርን፡ ወለዱ።

ደጃች፡ ብጡል፡ የሚጫዩቱን፡ ወይዘሮ፡ የውብ፡ ዳርን፡ አግብተው፡ እቴጌ፡ ጣይቱን፡ ፊተውራሪ፡ አሉላን፡ ራስ፡ ወሌን፡ ወይዘሮ፡ ደስታን፡ ወለዱ። እቴጌ፡ ጣይቱ፡ የዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ሚስት፡ መክን፡ ናቸው። ፊት፡ አውራሪ፡ አሉላ፡ ወይዘሮ፡ የተመኙን፡ ወለዱ። ራስ፡ ወሌ፡ ራስ፡ ጉግሳን፡ ወይዘሮ፡ ከፈይን፡ ደጃች፡ አመዴን፡ ደጃች፡ ኃይሌን፡ ወለዱ። ወይዘሮ፡ ደስታ፡ ደጃች፡ ወልደ፡ ሀናን፡ አግብተው፡ ደጃች፡ ገሰሰን፡ ወይዘሮ፡ አሰለፈችን፡ ወለዱ። ደጃች፡ መርሶ፡ ደጃች፡ ትኩን፡ ወይዘሮ፡ ላቀችን፡ ወለዱ። ራስ፡ አሊጋዝ፡ ደጃች፡ ጎጆን፡ ደጃች፡ ብሩን፡ ወለዱ። ደጃች፡ ጎጆ፡ ልጅ፡ ዘለቀን፡ ልጅ፡ ዘለቀ፡ አባ፡ ግርሻን፡ ወለዱ። ደጃች፡ ብሩ፡ ደጃች፡ ዘገየን፡ ወለዱ። ደጃች፡ ዘገየ፡ ደጃች፡ ጓንጉልን፡ ደጃች፡ ዓሊን፡ ደጃች፡ አሊጋዝን፡ ወይዘሮ፡ ሂሩትን፡ ደጃች፡ ኃይሉን፡ ወለዱ። ደጃች፡ ጓንጉል፡ ደጃች፡ ይማምን፡ ደጃች፡ ዓሊን፡ ወለዱ።

እኒህ፡ ወረ፡ ሴሆች፡ የጓንጉል፡ ልጆች፡ ከታላቁ፡ ዓሊ፡ እስከ፡ ታናሹ፡ ዓሊ፡ በክርስትና፡ ሃይማኖት፡ ጸንተው፡ ከነየልጅ፡ ልጆቻቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፡ መሰፍንት፡ የጁን፡ ላስታን፡ አገውን፡ ዋድላን፡ ደላንታን፡ ወሎን፡ ቤገምድርን፡ ስሜንን፡ ጎንደርን፡ ወገራን፡ ደምቢያን፡ ቋላን፡ አገው፡ ምድርን፡ ዳሞትን፡ ጐጃምን፡ አንድ፡ አድርገው፡ የጎንደርን፡ መንግሥት፡ አጥፍተው፡ ፻፳፭፡ ዓመት፡ ገዙ። ፸፩፡ ዓመት፡ የሚሉም፡ አሉ፡ ነገር፡ ግን፡ ቢቈጠር፡ አይሞላም። በእርግጥ፡ የወረ፡ ሴሆች፡ ግዛት፡ የራስ፡ አሥራትንና፡ የራስ፡ ወልደ፡ ገብሬልን፡ ፲፡ ዓመት፡ ጨምሮ፡ ፻፴፭፡ ነው።

እኒሀ፡ ወረ፡ ሴሆች፡ በፊት፡ እንዳልነ፡ ክርስትናቸው፡ በኀንጉል፡ ጊዜ፡ ነው፡ ልጆቹ፡ ክርስቲያኖች፡ ሁነው፡ ታላቁ፡ ራስ፡ ዓሊ፡ በገራቸው፡ በየጁ፡ ፲፡ ደብር፡ ተክለዋል። እርሳቸውም፡ ጉባርጃ፡ ማርያም፡ ጉበለፍቶ፡ አቡነ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት፡ ወልያ፡ ገብርኤል፡ ኪቢ፡ ቃለ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ዘምል፡ ጊዮርጊስ፡ ገዶ፡ መድኀኔ፡ ዓለም፡ ሾዋና፡ ማርያም፡ ናቸው።

የጁ፡ ጥንተ፡ ስምዋ፡ ገነቴ፡ ትባል፡ ነበር። የጁ፡ የተባለችበት፡ ምክንያም፡ እንዲህ፡ ነው፡ ጉባርጃ፡ ማርያም፡ በገነቴ፡ ምድር፡ የከበረች፡ ደብር፡ ናት፡ በርስዋ፡ ጳጳሳት፡ ይኖሩበት፡ ነበር፡ ፲፡ ጳጳሳት፡ ተቀብረውበታል፡ ይባላል።

በዚያች፡ አገር፡ ጣዖታትን፡ የሚያመልኩ፡ በስማታቸው፡ የሚመኩ፡ አስማተኞች፡ ሰዎች፡ ነበሩ። በዚያ፡ ዘመን፡ የነበረ፡ ጳጳስ፡ ንስሐ፡ ግቡ፡ በወንጌል፡ አመኑ፡ አስማት፡ ማድረግን፡ ጣዖት፡ ማምለክን፡ ተው፡ ብሎ፡ ቢገሥጻቸውና፡ ቢመከራቸው፡ እጅግ፡ አጥብቀው፡ ጠሉት፡ ቃሉን፡ አልተቀበሉት። እኒህ፡ አስማተኞች፡ ሲቀሩ፡ የቀሩት፡ ያገር፡ ታላላቆች፡ ወደ፡ ጳጳሱ፡ እየሄዱ፡ የወንጌልን፡ ትምህርትና፡ ሃይማኖት፡ እየሰሙ፡ ከዕለት፡ ወደ፡ ዕለት፡ ብዙች፡ ወደ፡ ክርስትና፡ ይገቡ፡ ጀመሩ። አስማቶኞችም፡ ክብራቸውን፡ እንደ፡ ተገፈፉ፡ በስራቸው፡ እንደ፡ ተነቀፉ፡ በዩ፡ ጊዜ፡ አንድ፡ ሕጻን፡ ሰርቀው፡ በስውር፡ አርደው፡ ለጳጳሱ፡ ወጥ፡ ስራ፡ ይህን፡ ወጥ፡ ሰርተህ፡ ጳጳስ፡ ግብር፡ በሚያበላበት፡ ጊዜ፡ ከጳጳሱ፡ ፊት፡ ይህን፡ አቅርብልነ። ይህ፡ ምንድር፡ ነው፡ ቢሉህ፡ የወትሮ፡ ግብርዎ፡ ነው፡ ብለህ፡ በሰው፡ ሁሉ፡ ፊት፡ አሳፍርልነ፡ ብለው፡ እጅግ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ሰጡት። መማለጃ፡ የፈራጆችን፡ ዓይን፡ ያሳውራል፡ እንዳለ፡ መጽሐፍ፡ ዘሰአት፡ ፳፫፡ ፳፡ እሱም፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ተቀብሎ፡ እንዳሉት፡ አደረገ። የወጡ፡ ሰታቴ፡ ድስት፡ በተከፈተ፡ ጊዜ፡ የዚያ፡ ሕጻን፡ ሁለቱ፡ እጆቹ፡ ከሌላው፡ ሥጋው፡ ጋራ፡ ወጥ፡ ተሠር

www.ethiopianorthodox.org

ቶ፡ አዩ። ጳጳሱም፡ አብርዋቸው፡ የተቀመጠውም፡ ሰው፡ እጅግ፡ አጥ ብቀው፡ ደነገጡ። አንተ፡ ዛሬ፡ ያደረግኸው፡ ነገር፡ ምንድር፡ ነው፤ ቢ ሉት፡ እንደ፡ ተመከረው፡ ጌታዬ፡ እኔ፡ ዛሬ፡ አዲስ፡ ነገር፡ አላመጣሁ ም፤ ያው፡ የወትሮ፡ ግብርዎ፡ ነው፡ አላቸው። ሰውም፡ ሁሉ፡ ደነገ ጠና፡ ፈራ። ጳጳስም፡ እጅግ፡ አዘኑና፡ እኔ፡ የሰው፡ ሥጋ፡ ከሁን፡ በፊ ት፡ ስበላ፡ ታውቀኛለህን፤ የሰው፡ ሥጋ፡ ከነእጁ፡ ሠርተህ፡ ያቀረብህ ልኝ፡ አንተ፡ ከጠላቶቼ፡ በገንዘብ፡ ተገዝተህ፡ ይህን፡ ታላቅ፡ ድፍረ ትና፡ ክፋት፡ በገንዘብ፡ መውደድ፡ ልብህ፡ ጠፍቶ፡ አድርገሃልና፡ ለዘ ለአለም፡ ርጉም፡ ሁን። ንቡዝ፡ ልብ፡ ሁን፡ ብለው፡ ረገሙት። ያን፡ ጊ ዜውን፡ ልብሱን፡ ጥሎ፡ ሱሪውን፡ ቀዶ፡ ራቁቱን፡ ሁኖ፡ በሰዎች፡ ፊ ት፡ አብዶ፡ በረረ፡ ገደል፡ ገብቶም፡ ሞተ። ይህንንም፡ ያዩ፡ ሁሉ፡ ብዙ ች፡ ከነዚያ፡ ወገን፡ ወደ፡ ክርስትና፡ ገቡ። አገሩንም፡ ረገሙት፡ እንዲ ህ፡ ሲሉ፤ የዚህ፡ አገር፡ ሰውም፡ ለኔ፡ ስም፡ ማክፋት፡ ብለው፡ ሰውን፡ ገድሎ፡ እጁን፡ ቈርጦ፡ እናቱን፡ ፈጥፍጦ፡ በሰው፡ እንዳ፡ ተጫወተ፡ የእጁን፡ ይስጠው፡ ሁልጊዜ፡ ደም፡ ይፍሰስበት፡ እስበሱ፡ ይተላለቅበ ት፡ ጳጳስም፡ አይቀመጥበት፡ ብለው፡ ረገሙት፡ ከዚያ፡ ወዲህ፡ ገነቴ፡ መባሉ፡ ቀርቶ፡ አገሩ፡ የጁ፡ ተባለ። እስበሱም፡ በወፉ፡ ውጊያ፡ ሁል ግዜ፡ የሰው፡ ደም፡ የሚፈስበት፡ በከንቱ፡ ነፍስ፡ የሚወድቅበት፡ የተ ረገመ፡ አገር፡ ሆነ።

የየጁ፡ ሰዎች፡ ይህ፡ መርገም፡ ስለ፡ ጳጳሳቸው፡ አገር፡ ላትገዙበት፡ ጠጅ፡ ላትጠጡበት፡ ቀሚስ፡ ላትለብሱበት፡ ስም፡ ላታወጡበት። ስለም ን፡ እስበሳችሁ፡ በከንቱ፡ ትጋደላላችሁና፡ ወገን፡ ከወገኑ፡ ይጋባል፡ ቢ ልዋቸው፡ ቆሌይቱ፡ ደም፡ ትወዳለችና፡ ወፉ፡ ውጊያ፡ ሲቀር፡ ከፉፍ፡ ላይ፡ ዘልቃ፡ እሪ፡ ትላለች። ስለዚሁ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ጋሻ፡ ጦሩን፡ እየያ ዘ፡ ከያገሩ፡ ይወጣልና፡ በየመልካው፡ ይወርዳል። በያላ፡ ወንዝ፡ በጥቁ ር፡ ውሃ፡ በሸሊ፡ በሚሌ፡ እየወረደ፡ ወፉ፡ ይዋጋል፡ ይላሉ።
ይህስ፡ ቢሆን፡ ክርስቲያን፡ ከሆናችሁ፡ በክርስቶስ፡ ካመናችሁ፡ ይህን፡ ከንቱና፡ ክፉ፡ ስራ፡ ብትተውት፡ ምነው፤ ቢልዋቸው፡ ያገሩ፡ ቆሌ፡ የ ሰው፡ ደም፡ የለመደች፡ ናትና፡ ወፉ፡ ውጊያ፡ ሲቀር፡ ከሰማይ፡ ዝና ብ፡ ያንስብናል፡ ብናርስም፡ እህሉ፡ ይጠፋብናል፡ አገራችንም፡ ይራ ብብናል፡ በሽታም፡ ይነሣብናል፡ ወፉ፡ በተዋጋን፡ ጊዜ፡ ግን፡ ዝናብ፡ በበረከት፡ ይወርዳልና፡ እህልም፡ ይወጣልና፡ አገራችንም፡ ጥጋብ፡ ጤ ናም፡ ይሆናል፡ ይላሉ።

www.ethiopianorthodox.org

በጠገባቸውም፡ በዙሪያቸው፡ ያሉ፡ ጉረቤቶቻቸው፡ አረማውያን፡ በስም፡ ክርስቲያን፡ የሚባሉ፡ ሳይቀሩ፡ ይህን፡ ከንቱ፡ ወሬ፡ እየሰሙ፡ ባገራቸው፡ ዝናብና፡ በረከት፡ የሀል፡ ብዛት፡ ጤናም፡ እንዲሆን፡ እስ በው፡ ይህን፡ ወፋ፡ ውጊያ፡ ለመዱ።

ይህም፡ ወፋ፡ ውጊያ፡ እስከ፡ ሸዋ፡ ደምበር፡ እስከ፡ ዶባ፡ እስከ፡ መሬ፡ ቤቱ፡ ተለምዶ፡ እስከሁን፡ እስከ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ዘመን፡ ድረስ፡ ይዋጉ፡ ነበሩ። ጃንሆይ፡ አጼ፡ ምኒልክ፡ በመንግሥትዎ፡ አገር፡ ያለኑ፡ ወፋ፡ ተዋጊን፡ ሁሉ፡ ይህን፡ ከንቱ፡ ጥፋት፡ በዋጅ፡ አስተው ት። ብዙ፡ ቀንም፡ በሰውር፡ ተጣቅሶ፡ ወርዶ፡ እርስበሱ፡ እየተዋጋ፡ እስቸግሮ፡ ነበር። በገዳይና፡ በሙዋች፡ ቤት፡ ዕዳ፡ እያስከፈሉ፡ አስተ ውት። ይህም፡ ሁኖ፡ በማመስገን፡ ፈንታ፡ ይህን፡ በከንቱ፡ መሞት፡ አ ስቀሩብን፡ ብሉ፡ ያዝናል፡ ጃንሆይንም፡ ያማል፡ ልብ፡ ያለውና፡ ያስ ተዋለ፡ ግን፡ በወፋ፡ ውጊያ፡ መቅረት፡ እግዚአብሔርንና፡ ጃንሆይን፡ ያመሰግናል። በለፈውም፡ በዘመዶቹ፡ በከንቱ፡ ጥፋት፡ እጅግ፡ ያዝናል፡ ይጠጠታል።

ስለ፡ ወረ፡ ሴሆች፡ ትውልድና፡ አመጣጥ፡ ከሚነገር፡ ከብዙ፡ በ ጥቂቱ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ይህ፡ ይበቃናል፡ ከዚህ፡ ቀጥለን፡ የነገደ፡ ጉራጌን፡ ታሪክ፡ እንጽፋለን።

---

## ፲፱፡ ነገደ፡ ጉራጌ።

የነገደ፡ ጉራጌ፡ ነገር፡ እንዳህ፡ ነው፤ በጼ፡ ዐምደ፡ ጽዮን፡ ዘመን፡ ከትግሬ፡ ጉርዓ፡ ከሚባል፡ አገር፡ ከኩሉ፡ ግዛይ፡ ክፍል፡ የወጣ፡ ሠራ ዊት፡ ከአዝማች፡ ሰብሓት፡ ጋራ፡ መጥቶ፡ በአይመለል፡ ተሠራ። ስለ ዚህም፡ ያ፡ አገርና፡ ሕዝብ፡ ጉርዓጌ፡ ይባላል። አጼ፡ ዐምደ፡ ጽዮን፡ የነገሡ፡ ከንድ፡ ሺ፡ ፫፻፳፯—ሺ፫፻፶፰፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ዘመን፡ መን ግሥታቸው፡ ፴፡ ዓመት፡ ነው።

የጉርዓጌ፡ ሕዝብ፡ ከጉርዓ፡ ተነሥተው፡ ወደ፡ አይመለል፡ የገቡ፡ በዚያ፡ ዘመን፡ ነው። ጉርዓጌ፡ ማለት፡ የጉርዓ፡ ሰዎች፡ ምድር፡ ወይም፡ አገር፡ ማለት፡ ነው።

ዳግመኛም፡ ከንጉሡ፡ ሰፈር፡ ግራ፡ ስለ፡ ሰፈሩ፡ ግራጌ፡ ተብሉ፡ በቀን፡ ብዛት፡ ግን፡ ግራጌ፡ ተለውጦ፡ ጉራጌ፡ ተብሉ፡ ይላሉ።

---

www.ethiopianorthodox.org

## ፳፡ ከምጥዋ፡ እስከ፡ መተማ፡ በኢትዮጵያ፡ ዳር፡ ለዳር፡ በቆላው፡ ስላሉ፡ ሕዝብ።

ከምጥዋ፡ እስከ፡ መተማ፡ ወይም፡ እስከ፡ ቋራ፡ ጥግ፡ ያሉ፡ ሕዝብ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ወገኖች፡ ናቸው። በፊት፡ እንዳሰየኑ፡ የሳባ፡ ልጆች፡ በትግሬ፡ ይኖራሉ፡ እነሆ፡ የኢትዮጲስ፡ ልጆች፡ ናቸው። ከነዚህም፡ የተለዩ፡ የበለው፡ ልጆች፡ በደሆኖ፡ በሐረርጌን፡ በምጥዋ፡ በምንኩሉ፡ ያሉ፡ ሕዝብ፡ ናቸው። አለቃቸው፡ ናይብ፡ ይበላል።

የከለው፡ ልጆች፡ በፊት፡ እንዳልኑ፡ ከሳባ፡ ወደ፡ ምዕራብና፡ ወደ፡ ደቡብ፡ ያሉ፡ ያማሬ፡ የወልቃይት፡ የጠገዴ፡ የጠለምት፡ ያርማጭሆ፡ የዳዋ፡ የቋራ፡ አባት፡ ነው።

የኖባ፡ ልጆች፡ ደግለሎች፡ ጃሊሎች፡ ምንዳሚሮች፡ ናቸው። ከነዚህም፡ ሌላ፡ በቆላው፡ የሚኖሩ፡ የከም፡ ልጆች፡ ኩናሞች፡ ሱዳኖች፡ ትክሪሮች፡ ግንጃሮች፡ ፈግኖች፡ ሸንቅሎች፡ ናቸው።

ከበለው፡ ገለባትና፡ የባሪያ፡ ሻጭ፡ (ሻግያ፡) ባለመከራ፡ የሚባሉ፡ ወገን፡ አሉ። ለምልክት፡ ገላቸውን፡ ይበጣሉ። ከአዲያቦ፡ በስተ፡ ሰሜንም፡ ባሪያ፡ ተብለው፡ የሚጠሩ፡ ሕዝብ፡ አሉ። ከነርሱ፡ መሀከልም፡ ኢልግ፡ የሚባሉ፡ ጨዋዎች፡ አሉ። የሰውነታቸው፡ መልክ፡ ሁሉ፡ ከኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በምንም፡ አይለዩም። የብቻቸው፡ ቋንቋና፡ ፊደል፡ መጻሕፍትም፡ አልዋቸው፡ ይላሉ። ከወገናቸው፡ ያልሆነ፡ ሰው፡ እንዳያውቀባቸው፡ እነዚያን፡ መጻሕፍታቸውን፡ በብዙ፡ ጥንቃቄ፡ ይጠብቋቸዋል። ይህ፡ ትምህርት፡ እንደ፡ ምስጢር፡ ከባት፡ ወደ፡ ልጅ፡ እየተያያዘ፡ ይወርዳል። ከነሱም፡ የሚማሩት፡ አድግ፡ ጥቂቶች፡ ናቸው። ከምድር፡ በታች፡ እንደ፡ አዳራሽ፡ የሆነ፡ አድግ፡ ሰፊ፡ ሰፊ፡ ዋሻ፡ አላቸው። በድንገት፡ በሜዳ፡ ሳሉ፡ አደጋ፡ ካልጣሉባቸው፡ ጠላት፡ ሊያገኛቸው፡ አይችልም። እምልኳቸው፡ ከክርስቲያንና፡ ከእስላም፡ የተለየ፡ ነው።

---

## ፳፩፡ ከሐረርጌ፡ እስከ፡ ምጥዋ፡ ወሰን፡ ስላሉ፡ ሕዝብ።

ከሐረርጌ፡ እስከ፡ ምጥዋ፡ ወሰን፡ ቆላ፡ ቆላውን፡ በረሃውን፡ የያዙ፡ ሕዝብ፡ በፊት፡ ከዮቅጣን፡ ልጆች፡ ነገደ፡ አባልና፡ ኦፊር፡ ነበሩ። ነገደ፡ አልባ፡ የአዳልንና፡ የሱማሌን፡ ምድር፡ በነገደ፡ ኦፊር፡ የኢሳንና፡

www.ethiopianorthodox.org

የውጋዴን፡ ምድር፡ ይዘው፡ ነበር፡ የነገደ፡ አፌር፡ ከተማ፡ ዛሬ፡ ከፌር የሚባለው፡ በውጋዴን፡ ውስጥ፡ ነበር። ዛሬ፡ ግን፡ ነገደ፡ ኢሳ፡ ነገደ፡ ሱማሊ፡ ነገደ፡ አዳል፡ ነገደ፡ ዳንከሊ፡ ነገደ፡ ሻሆ፡ ነገደ፡ ቶርን፡ ነገ ደ፡ አሳሁርታ፡ ነገደ፡ ጥልጣል፡ ከእስያ፡ መጥተው፡ ነገደ፡ አበልን፡ አ ስለቅቀው፡ አገሩን፡ ወረሱ። ነገደ፡ ሱማሊ፡ ነገደ፡ ኢሳ፡ የአፌርን፡ ሕ ዝብ፡ አስለቅቀው፡ አገሩን፡ ወረሱ። ከነገደ፡ አባልና፡ ከነገደ፡ አፌር፡ ከዚያ፡ የተሰደዱ፡ ከደጋው፡ ኢትዮጵያ፡ ወጥተው፡ ከነገደ፡ ሳባ፡ ከወን ድሞቻቸው፡ ተቀላቀሉ። የጥንት፡ አገራችን፡ እንለቅም፡ ያሉ፡ ለመከ ደድ፡ ጉልበትና፡ ኃይል፡ ያጡ፡ ግን፡ ከነዚያ፡ ተመሳስለው፡ የቀሩ፡ አ ሰለሙና፡ ተቀላቀሉ።እኒህ፡ ሁሉ፡ ሕዝብ፡ በየጊዜው፡ ከእስያ፡ እየፈለ ሱ፡ የገቡ፡ ናቸው።

ኢሳ፡ የተባሉ፡ ሕዝብ፡ የኤሳው፡ ዘሮች፡ ናቸው። አዳል፡ ሱማሌ፡ ዳንከሌ፡ የካም፡ ልጆች፡ ናቸው። ሻሆ፡ ቶርን፡ አሳሁርታ፡ ጥልጣል፡ ከዓረብ፡ ዘር፡ ናቸው። ሻሆ፡ አሳሁርታ፡ ቶርን፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ተ ቀላቅለዋል፡ ስለዚህም፡ አገራቸው፡ በቶርን፡ ወይም፡ በአሳሁርታ፡ ስም፡ ይጠራል።

አዳሎችና፡ ጥልጣሎችም፡ ተቀላቅለዋልና፡ እንዲሁም፡ ቋንቋቸው፡ አስበሱ፡ ይመሳሰላል። ሁሉም፡ በዓሊ፡ ዘመን፡ አሰለሙ፡ ይባላል። ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የወጡበት፡ ጊዜና፡ ዘመን፡ አይታወቅም።

---

## ፳፱፡ ሐ ረ ር ጌ ፡ ሕ ዝ ብ ።

ከሐረርጌ፡ ግምብ፡ የሚኖሩ፡ ሕዝብ፡ ከሐማሴን፡ የመጡ፡ ሕዝብ፡ ናቸው። በሐማሴን፡ አንድ፡ ኃይለኛ፡ ጀግና፡ ሰው፡ በጼ፡ ዳዊት፡ ዘመ ን፡ ነበረ። በኃይለኛነቱ፡ ሰው፡ ጠልቶት፡ ከሰው፡ ተለይቶ፡ ምሽቱንና፡ ልጆቹን፡ ይዞ፡ ለብቻው፡ በችፍግ፡ ዱር፡ ውስጥ፡ ቤት፡ ሰርቶ፡ ተቀመ ጠ። ከእለታት፡ አንድ፡ ቀን፡ ብዙ፡ ቅቤ፡ ምሽቱ፡ አጠጣችው። እርሱ ም፡ ደክሞ፡ ለብቻው፡ ከቤት፡ ተኝቶ፡ ቀረ። ምሽቱ፡ ግን፡ አዝመራ፡ ለመሰብሰብ፡ ልጆችዋን፡ ሁሉ፡ ሰብስባ፡ ይዛ፡ ወደ፡ ስራ፡ ሄደች። ማታ፡ ልጆችዋን፡ ይዛ፡ ብትመለስ፡ ባልዋን፡ አንበሳ፡ ጕትቶ፡ ከወለሉ፡ ሙቶ፡ ተንዘራግቶ፡ ቈያት። የጠጣውን፡ ቅቤ፡ ከሆዱ፡ ቀዳ፡ በዕቃ፡ ቀድታ፡



www.ethiopianorthodox.org

ለወንዶች፥ ልጆችዋ፡ ሁሉ፥ አቀመሰቻቸው። ይህነንም፡ ማድረጉዋ፥ ጠንቋይ፥ ባልሽ፡ ሊሞት፥ ጊዜው፥ ደርሰዋል፥ በድንገት፥ ሳይታሰብ፡ አንበሳ፡ ይገድለዋልና፡ ቅቤ፡ አጠጭው፥ አንበሳ፡ ከገደለው፡ በኋላ፥ ሆዱን፡ ቀድሽ፡ ከሆዱ፡ ያለውን፡ ቅቤ፡ በዕቃ፥ ተቀብለሽ፡ ለልጆችሽ፡ አጠጪቸው፥ እንደ፡ አንበሳ፡ ባለ፥ ግርማ፥ ይሆናሉ፥ ጠላትም፥ ከፊታቸው፥ አይቆም፥ አሸናፊች፥ የሚያስፈሩ፥ ይሆናሉ፥ ብልዋት፥ ነበረና፥ ስለዚሁ፡ ነው፥ ይላሉ። ይህ፡ ታሪክ፡ በገድለ፡ ማርቆስ፡ ተጽፎአልና፥ በዚያ፥ ተመልከት።

ከዚሁ፥ በኋላ፡ ጠላቶች፡ ያባታቸውን፡ ሞት፡ ሰምተው፥ እንግዲሁ፡ የዚያን፥ የርጉም፡ ልጆች፥ ከምድር፡ እናጥፋቸው፥ ብለው፥ ተነሡባቸው፡ በተዋጉም፡ ጊዜ፥ እኒህ፥ ልጆች፥ ድል፥ አድርገው፡ ጠላቶቻቸውን፥ ፊቶዋቸው፥ ጦርም፡ ከፊታቸው፡ የማይቆም፡ ሆነ። አገር፡ እያሴሩ፥ እንደገና፥ ጦር፡ እየሆነ፡ ቢያስቸግራቸው፥ ጓዛቸውን፡ አንሥተው፥ ከብታቸውን፡ ነድተው፥ እየተዋጉና፡ እየተከላከሉ፡ እስከ፥ ሐረርጌ፡ ተሰደዱ፥ በዚያም፡ ተቀመጡ። ከብዙ፥ ዘመን፡ በኋላ፥ በዙሪያቸው፥ ያለ፥ ጋላ፡ የማያኖራቸው፥ ቢሆን፥ ከወንድሞቻቸው፥ አንዱን፡ በላያቸው፡ አለቃ፡ ሾመው፥ ጋላውን፡ እየተዋጉ፥ ድል፥ እያደረጉ፥ በዙሪያውቸው፥ ያለውን፥ አሸንፈው፥ ገዙት። ሌት፡ አደጋ፡ እየጣለ፡ ቢያስቸግራቸው፥ አገራቸውን፡ ዙሪያውን፥ በብርቱ፡ ግምብ፡ አጠሩ፥ ፩፥ በርም፡ አደረጉለት። ከዘመን፥ ብዛት፡ ቋንቋቸው፥ ትግርኛ፡ የነበረ፡ ተለውጦ፡ ሌላ፥ ሆነ፥ ነገር፥ ግን፥ ዛሬም፡ ቢሆን፥ ከትግርኛ፡ ብዙ፥ ይመሳሰላል። በፊት፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፥ ሳትደክም፡ ለኢትዮጵያ፥ መንግሥት፥ ይገዙ፡ ይገብሩ፥ ነበሩ፥ በኋላ፥ ግን፥ ለቱርክ፡ መንግሥት፥ ተገዙ።

ከዚህ፡ በኋላ፥ በ፲፰፻፸፱፡ ዓመተ፥ ምሕረት፥ ጃንሆይ፡ አጼ፡ ምኒልክ፥ አረርጌን፥ ከፍተው፥ ንጉሡን፥ ድል፥ ነሥተው፥ ያዙ፥ ራስ፡ መኰንንን፥ ሹመው፡ ተመለሱ። የሐረርጌ፡ ቋንቋ፡ ከግምብ፡ ውስጥ፥ ነው፥ እንጂ፡ ከውጭ፡ የለም።

ይህ፥ ሁሉ፥ የተቈጠረ፥ ሕዝብ፡ ጥንት፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፥ ዜጋ፡ ነበር። ዛሬ፡ ግን፥ ኢትዮጵያ፡ ከታላቅነትዋ፡ ከስፋትዋ፡ እያነሰች፥ እየጠበበች፥ ሄዳችና፥ የዛሬ፡ አገርዋ፡ ፫፥ ክፍል፥ ብቻ፥ ቀረች። እኒህም፥ ፫፥ ክፍሎች፥ ቆላ፥ ወይና፡ ደጋ፥ ይባላሉ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፳፫ ፡ ኢትዮጵያ፡ ወሰንና፡ ደግ፡ አገር፡ እንደ፡ ነበረች።

የጥንት፡ ደንበርዋ፡ ከጅቡቲ፡ ባሕር፡ ዳር፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ሰናር፡ እስከ፡ ነጭ፡ አባይ፡ ድረስ፡ ነበር። በሰሜንም፡ ከ፲ተኛው፡ ሃገረ፡ ናግራን፡ ወዲያ፡ በርበር፡ የምስር፡ ወገን፡ ይመልሰው፡ ነበር።

በቆላው፡ ብዙ፡ ልዩልዩ፡ አትክልትና፡ ፍሬ፡ ይገኝበታል። በደቡብ፡ ቆላ፡ በባሌ፡ በቦረና፡ በጅጅጋ፡ አውራጃ፡ የዕጣን፡ የላስቲክ፡ ዛፍ፡ የሰንደል፡ እንጨት፡ ከርቤ፡ ሌላም፡ ብዙ፡ ቅመምና፡ የሚበላ፡ ፍሬ፡ ይገኝበታል፤ የከበረ፡ የጠራ፡ ወርቅም፡ ዕንቍም፡ ሉልም፡ በኢትዮጵያ፡ ይገኛል፤ ዝበድም፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ሽቱም፡ አለበት። ኢዮብ፡ ፳፰፡ ፲፮—፲፱፡ ፩፡ ነግ፡ ፲፡ ፲—፲፫፡ ፪፡ ዜና፡ ፱፡ ፱—፲፪፡ ተመልከት። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ግን፡ ኃይልዋ፡ እየደከመ፡ ፍቅርና፡ አንድነት፡ እውቀትም፡ እያዳረ፡ ቢጕልበት፤ ይህን፡ የመሰለ፡ አገሩዋን፡ ሁሉ፡ ከውጭ፡ የመጡ፡ ባዕዳን፡ ሕዝብ፡ ያዙበት።

ጥበብንም፡ ከብልሃተኞች፡ መጠየቅን፡ ናቀችና፡ ቸል፡ አለች። በቀድሞው፡ እውቀትዋ፡ እንደ፡ ተሰበረ፡ መኪና፡ ቁማ፡ አኖራለሁ፡ ብላ፡ ተመከች። ነገር፡ ግን፡ ይህ፡ ሳይቀር፡ ደግሞው፡ ከቀድሞው፡ እውቀትዋ፡ እጅግ፡ በረደችና፡ ቀዘቀዘች፡ ብዙም፡ አነሰች።

የቀድሞ፡ ታሪክ፡ ጻፊ፡ ግን፡ ሄሮዶቱስ፡ የሚባል፡ የግሪክ፡ አገር፡ ሰው፡ ፬፻፹፬፡ ዓመት፡ ከልደት፡ በፊት፡ የነበረ፡ ከርሱ፡ ዘመን፡ በፊት፡ ምስርን፡ ጨምረው፡ የገዙትን፡ የኢትዮጵያን፡ ነገሥታት፡ ታሪክ፡ ሲናገር፡ ፲፰፡ ነገሥታት፡ ምስርን፡ ጨምረው፡ ገዙ፡ ሲል፡ በታሪክ፡ መጽሐፉ፡ ጽፍዋል።

ዳግመኛም፡ ይህ፡ ሄሮዶቱስ፡ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ደግነት፡ ሲናገር፡ እንዲህ፡ ይላል፤" በኢትዮጵያ፡ እጅግ፡ ያማሩ፡ ሕዝብ፡ ባለ፡ ዳመ፡ ግበት፡ ቆንጆች፡ ውቦች፡ ሰዎች፡ አሉበት። ርኃራኄያቸውም፡ እንደ፡ እግዚአብሔር፡ ነው። በሰፊ፡ ሜዳ፡ ለመንገድ፡ አላፊ፡ የሚሆን፡ ድግስ፡ እየደገሱ፡ ያሰናዳሉ፤ ምንም፡ ቢሆን፡ መንገደኛ፡ በመንገድ፡ የሚበላውን፡ አያጣም፤ ዕድሜያቸው፡ ከ፻፡ እስከ፡ ፻፳፡ እስከ፡ ፻፴ም፡ ይቀመጣሉ። ነውር፡ ክፉ፡ ነገርም፡ ባገራቸው፡ የተጠላ፡ የተጸየፈ፡ ነው፡ የጤና፡ ምንጮች፡ የሚሆኑ፡ ውሆች፡ አሉዋቸውና። እሱ፡ በጠጡ፡ ጊዜ፡ ሰውነታቸው፡ ይታደሳል። በሀብትም፡ እጅግ፡ ባለ፡ ጠጎች፡ ናቸው።"

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁ፡ ያለች፡ እጅግ፡ ያማረች፡ በልዩ፡ ወገን፡ ሰው፡ በባዕድ፡ አፍ፡ የተመሰገነች፡ የከበረች፡ የነበረች፡ አገር፡ ዛሬ፡ ግን፡ ፍቅር፡ በማጣት፡ እርስበርስዋ፡ ባለመስማማት፡ ያንድነት፡ ኀይልዋን፡ አፍርሳ፡ በመለያየት፡ የደም፡ መፍሰስ፡ የግፍ፡ የከፋት፡ የነውር፡ ሁሉ፡ ከተማ፡ ሆነች። ኢ.ሳ. ፲፱፻፡ ፫—፲፫፡ ተመልከት።

ኢትዮጵያ፡ ቆላው፡ ሙቀቱ፡ ያመት፡ ሙቀቱን፡ ቢያከፍሉት፡ ከ፳—፳፰፡ ዴግሪ፡ (ማዕርግ) ይደርሳል።

ወይና፡ ደጋው፡ እጅግ፡ ጤናማ፡ አገር፡ የሰጡትን፡ ዘር፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ አትክልትም፡ የሚያበቅል፡ ነው። ሙቀቱም፡ በዓመት፡ ቢያከፍሉት፡ ከ፲፭—፲፱፡ ዴግሪ፡ ይደርሳል።

ደጋው፡ ግን፡ ከደጋው፡ እህልና፡ ዛፍ፡ በቀር፡ ሁሉን፡ አያበቅልም፡ ሙቀቱም፡ ከ፯—፰፡ ዴግሪ፡ እስከ፡ ዜሮ፡ ይደርሳል።

ስለ፡ ኢትዮጵያና፡ በውስጥዋ፡ ስለሚኖሩ፡ ሕዝብ፡ ከሚነገር፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ይህ፡ ይበቃናል።

www.ethiopianorthodox.org

## ከልደት፡ በኋላ፡ በኢትዮጵያ፡ የነገሡ፡ ነገሥታት፡ ዘመን፡ መንግሥት።

| ስም። | ዘመን። | ዓመተ፡ ምሕረት። |
|---|---|---|
| ባዜን፡ ከልደት፡ በፊት፡ ፰ዓመት፡ ከልደት፡ በኋላ፡ ፱፡ ዓመት፡ ዘመን፡ መንግሥቱ፡ ድምር፡ ፲፯፡ ዓመት፡ ምሕረት። | ፱፡ | ፱። |
| ሠርጡ፡ ስመ፡ መንግሥቱ፡ ጸንፈ፡ አስገድ፡ | ፳፮፡ | ፴፡ |
| ጽንፈ፡ አርእድ፡ | ፬፡ | ፴፱። |
| ሰጥታህ፡ | ፫፡ | ፵። |
| ሆርኤምተኩ፡ | ፬፡ | ፵፱። |
| ገርስሞት፡ ንግሥት፡ | ፫፡ | ፶። |
| ሀተዘ፡ ባሕር፡ አስገድ፡ | ፳፫፡ | ፸፫። |
| ምሲንህ፡ ግርማሶር፡ | ፯፡ | ፹፯። |
| ስጥዋ፡ ግርማ፡ አስፈር፡ | ፩፡ | ፺፩። |
| አድገሉ፡ ፪ኛ፡ | ፲፡ ዓ፡ ፯፡ ወ | ፻፩። |
| አግባ፡ | ፯፡ | ፻፯። |
| ሰርኣዳ፡ | ፲፯፡ | ፻፳፬። |
| መሊስ፡ አላሚዳ፡ | ፩፡ | ፻፳፯። |
| ሀቀቢ፡ ኩሉ፡ ጽዮን፡ | ፯፡ | ፻፴፩። |
| ሀቅሊ፡ ሰርጓይ፡ | ፲፱፡ | ፻፵፲። |
| ድድሜ፡ ዘርኣይ፡ | ፲፡ | ፻፶፲። |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| አውጥጥ፡ | ፱፡ | ፻፶፰። |
| አልአይ፡ በጋማይ፡ | ፪፡ | ፻፷፱። |
| አውዱ፡ ዝርን፡ አሰገድ፡ | ፴፡ | ፻፺፱። |
| ዛግን፡ ጽዮን፡ ሓግዝ፡ | ፪፡ | ፻፺፪። |
| ሬማ፡ ጽዮን፡ ግዛ፡ | ፰፡ | ፻፱። |
| አዜጋን፡ መአልበጋድ፡ | ፪፡ | ፱፻፪። |
| ገፊሌ፡ ሰብአ፡ አሰገድ | ፭፡ | ፱፻፲። |
| ጽጋዮን፡ ብአሴ፡ ሰርቅ፡ | ፬፡ | ፱፻፲፱። |
| ጋዛ፡ አግዱር፡ | ፱፡ | ፱፻፳፭። |
| አግዱር፡ አስንን፡ | ፯፡ | ፱፻፳፮። |
| ጸዊዛ፡ | ፭፡ | ፱፻፴። |
| ዋከና፡ ንግሥት፡ | ፪፡ | |
| ሀውዱስ፡ | ፬፡ ወር፡ | |
| አስላል፡ ሰን፡ ሰገል። | ፰፡ | ፱፻፴፰። |
| አስፍሓ፡ አስፍሓ፡ | ፲፬፡ | ፱፻፶፪። |
| አጽገበ፡ ሰይፈ፡ አርአድ፡ | ፮፡ | ፱፻፶፰። |
| አይበ፡ | ፲፪፡ | ፱፻፸። |
| ጸሓም፡ ላክንዱን፡ | ፰፡ | ፱፻፸፰። |
| ጽጋብ፡ | ፲፡ | ፱፻፹፰። |
| ታዜር፡ ታዚና፡ | ፲፡ | ፱፻፺፰። |
| አሀየዋ፡ ሰፍያ፡ ንግሥት | ፪፡ | ፲፻፪። |

www.ethiopianorthodox.org

# ዘመን፡ ክርስትና፡ በኢትዮጵያ።

| ስም። | ዘመን። | ዓመተ፡ ምሕረት። |
|---|---|---|
| አብርሃና፡ አጽብሓ፡ | ፳፯፡ | ፫፻፴፪። |
| እኒህ፡ ሁለት፡ ወንድማማች፡ በ ንገሡ፡ በ፲፭፡ ዓመት፡ በበ፡ ሰላማ፡ ከሣቴ፡ ክርስትና፡ በኢትዮጵያ፡ መጣ፡ | | ፫፻፳፯። |
| አብርሃ፡ ለብቻው፡ | ፲፪፡ | ፫፻፷፩። |
| አስፍሓ፡ ዳልዝ፡ | ፯፡ | ፫፻፸፫። |
| ሣህል፡ | ፲፬፡ | ፫፻፹፫። |
| አርፍድ፡ ገብረ፡ መስቀል፡ | ፬፡ | ፫፻፹፱። |
| አድሃና፡ ንግሥት፡ | ፮፡ | ፫፻፺፬። |
| ርትዕ፡ | ፩፡ | ፫፻፺፮። |
| አስፍሓ፡ ፪ተኛ፡ | ፩፡ | ፫፻፺፯። |
| አጽብሓ፡ ፪ተኛ፡ | ፮፡ | ፫፻፹፩። |
| አሜዳ፡ ፩ኛ፡ | ፲፮፡ | ፫፻፺፯። |
| አብርሃ፡ ፪ተኛ፡ | ፯፡ ወር፡ | |
| አሊ፡ ሣህል፡ | ፪፡ ወር፡ | |
| አሊ፡ ገበዝ፡ | ፪፡ | ፫፻፺፫። |
| ሣሃል፡ | ፬፡ | ፬፻፪። |
| አብርሀ፡ | ፲፡ | ፬፻፲፪። |
| አድሄና፡ ንግሥት፡ | ፯፡ | ፬፻፲፰። |
| ኢዮአብ፡ | ፲፡ | ፬፻፳፰። |
| ጸሓም፡ ፪ተኛ፡ | ፪፡ | ፬፻፴። |
| አሜዳ፡ ፪ተኛ፡ | ፩፡ | ፬፻፴፩። |
| ሣህል፡ ሣህለ፡ አሕዛብ፡ | ፪፡ | ፬፻፴፫። |
| ጽባህ፡ መሐረነ፡ ክርስቶስ፡ | ፫፡ | ፬፻፴፯። |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ጸሐዎም፡ ፫ተኛ፡ | ፰፡ | ፬፻፴፫። |
| ኢ̈ሉ፡ ገበዝ፡ ፪ተኛ፡ | ፯፡ | ፬፻፵፩። |
| ኢጋቤ፡ | ፮፡ | ፬፻፵፰። |
| ሌዊ፡ | ፪፡ | ፬፻፶፬። |
| ኢሜዴ፡ ፫ተኛ፡ ያዕቆብ፡ | ፫፡ | ፬፻፶፮። |
| አርማህ፡ ዳዊት፡ | ፲፬፡ | ፬፻፶፱። |
| አምሲ፡ | ፩፡ | ፬፻፸፫። |
| ሰልአዶባ፡ | ፱፡ | ፬፻፸፬። |
| አልዓሜዳ፡ | ፲፡ | ፬፻፹፫። |
| ታዜና፡ ፪ተኛ፡ ሰሙ፡ ኤዛና፡ | ፯፡ | ፬፻፺፫። |
| ካሌብ፡ | ፴፡ | |
| ዘእስራኤል፡ | | ፭፻፴። |
| ገብሩ፡ | ፩ወር፡ | |
| ገብረ፡ መስቀል፡ | ፲፬፡ | ፭፻፴፪። |
| ቆስጠንጢኖስ፡ ማህል፡ | ፳፬፡ | ፭፻፵፮። |
| ወሰን፡ ሰገድ፡ መሐረነ፡ ክርስቶስ፡ | ፲፭፡ | ፭፻፸። |
| ፍሬ፡ ሰናይ፡ | ፳፫፡ | ፭፻፹፭። |
| አድርአዝ፡ | ፳፡ መሐመድ፡ ተነሣ፡ | ፮፻፰። |
| አክሊ፡ ውድም፡ | ፲፡ በ፮፻፳፡ | ፮፻፳፰። |
| ግርማ፡ አስፈሬ፡ | ፲፭፡ | ፮፻፴፰። |
| ዝርጋዝ፡ | ፳፡ | ፮፻፶፫። |
| ድግና፡ ሚካኤል፡ | ፳፮፡ | ፮፻፸፫። |
| ባሕር፡ ኢክላ፡ | ፲፱፡ | ፮፻፺፱። |
| ጉም፡ | ፳፬፡ | ፯፻፲፰። |
| አስጉምጉም፡ | ፭፡ | ፯፻፵፪። |
| ለትም፡ | ፲፮፡ | ፯፻፵፯። |
| ተላትም፡ | ፳፩፡ | ፯፻፷፫። |
| አደ፡ ጎሽ፡ | ፲፫፡ | ፯፻፹፬። |

www.ethiopianorthodox.org

አይዛርር እስከ ቀትር

| | | |
|---|---|---|
| ድድም | ፰ | ፯፻፹፰ |
| ውድድም | ፲ | ፯፻፺፰ |
| ውድማ አስፈሬ | ፴ | ፰፻፳፰ |
| አርማህ | ፳ | ፰፻፵፰ |
| ድግናዣን | ፲፱ ፲ወር | ፰፻፷፰ |
| ግጻዣን | ፲ ወር | ፰፻፹፯ |

ስለ ጉዲት መንግሥት

| | | |
|---|---|---|
| ጉዲት | ፵ | ፰፻፺፯ |
| አንበሳ ውድም | ፳ | ፱፻፲ |
| ድል ነአድ ማዕደይ | ፲ | ፱፻፴ |

የዛጔ መንግሥት መሬ ትክለ ሃይማኖት

| | | |
|---|---|---|
| ስመ መንግሥቱ ዛጔ | ፲፫ | ፱፻፵፫ |
| ጠጠውድም | ፵ | ፱፻፷፫ |
| ጃን ሥዩም | ፵ | ፲፻፲፫ |
| ግርማ ሥዩም | ፵ | ፲፻፶፫ |
| ይመርሐነ ክርስቶስ | ፵ | ፲፻፺፫ |
| ቅዱስ አርቤ | ፵ | ፲፩፻፵፫ |
| Lalibala ላሊበላ | ፵ | ፲፩፻፷፫ |
| Naakueto Laab ነአኵቶ ለአብ | ፵ | ፲፪፻፲፫ |
| ይትባረክ ወልዱ ለላሊበላ | ፲፯ | ፲፪፻፵፯ |
| መይራሪ | ፲፰ | ፲፪፻፶፫ |
| ሀርበይ | ፰ | ፲፪፻፶፩ |

ያጼ ይኩኖ አምላክና የልጆ
ቸው መንግሥት

| | | |
|---|---|---|
| ይኩኖ አምላክ | ፲፭ | ፲፪፻፸፫ |
| ያግብአ ጽዮን | ፱ | ፲፪፻፹፮ |
| ጽንፈ አርአድ | ፩ | ፲፪፻፹፯ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሕዝበ፡ አሰገድ፡ | ፩፡ | ፲፪፻፸፱። |
| | ቅድመ፡ አሰገድ፡ | ፩፡ | ፲፪፻፹። |
| | ጀን፡ አሰገድ፡ | ፩፡ | ፲፪፻፹፩። |
| | ሰብአ፡ አሰገድ፡ | ፩፡ | ፲፪፻፹፪። |
| | ውድማ፡ አርአድ፡ | ፲፭፡ | ፲፪፻፺፯። |
| Amda Syon | ዐምደ፡ ጽዮን፡ | ፴፡ | ፲፫፻፰፯። |
| | ሰይፈ፡ አርአድ፡ | ፳፰፡ | ፲፫፻፶፭። |
| | ውድማ፡ አስፈሬ፡ | ፲፡ | ፲፫፻፳፭። |
| | ዳዊት፡ | ፴፡ | ፲፫፻፺፭። |
| | ቴዎድሮስ፡ | ፬፡ | ፲፫፻፺፱። |
| | ይስሐቅ፡ | ፲፭፡ | ፲፬፻፲፬። |
| | እንድርያስ፡ | ፯፡ | |
| | ሕዝበ፡ ናኝ፡ | ፬፡ | ፲፬፻፲፰። |
| | በድል፡ ናኝ፡ ፯፡ ከእንድርያስ፡ | ፯፡ ወ ፩፡ | ፲፬፻፲፱። |
| | ዐምደ፡ ኢየሱ፡ | ፯፡ | ፲፬፻፳፩። |
| Zara Yaqob | ዘርአ፡ ያዕቆብ፡ ዘርአ፡ | ፴፬፡ | ፲፬፻፳። |
| Baeda Maryam | በእደ፡ ማርያም፡ | ፲፡ | ፲፬፻፷። |
| Eskender | እስክንድር፡ | ፲፯፡ ፰፡ ወ፡ | ፲፬፻፹፯። |
| Amda Syon II | ዐምደ፡ ጽዮን፡ | ፯፡ ወ ፩፡ | ፲፬፻፹፪። |
| Naod | ናዖድ፡ | ፲፫፡ | ፲፭፻። |
| Lebna Dengel | ልብነ፡ ድንግል፡ | ፴፪፡ | ፲፭፻፩። |
| Galawdewos | ገላውዴዎስ፡ | ፲፱፡ | ፲፭፻፴፪። |
| Minas | ሚናስ፡ | ፬፡ | ፲፭፻፶፫። |
| Sarsa Dengel | ሰርጸ፡ ድንግል፡ | ፴፬፡ | ፲፭፻፹፪። |
| | ያዕቆብ፡ | ፯፡ | ፲፭፻፺፬። |
| | ዘድንግል፡ | ፩፡ | ፲፭፻፺፭። |
| | ሱስንዮስ፡ | ፳፰፡ | ፲፮፻፳፫። |
| | ፋሲል፡ ጎንደርን፡ የሰራ፡ | ፴፯፡ | ፲፮፻፴፱። |
| | ደጉ፡ ዮሐንስ፡ | ፲፭፡ | ፲፮፻፷፬። |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| አድያም፡ ሰገድ፡ ኢያሱ፡ | ፳፬፡ | ፲፮፻፸፮። |
| ተክለ፡ ሃይማኖት፡ | ፪፡ | ፲፯፻። |
| ቴዎፍሎስ፡ | ፫፡ | ፲፯፻፫። |
| ዮስጦስ፡ | ፭፡ | ፲፯፻፭። |
| ዳዊት፡ | ፭፡ | ፲፯፻፲፫። |
| በካፋ፡ | ፱፡ | ፲፯፻፳፪። |
| ዓለም፡ ሰገድ፡ ኢያሱ። | ፳፭፡ | ፲፯፻፴፩። |
| ኢዮአስ፡ | ፲፭፡ | ፲፯፻፶፮። |
| ዮሐንስ፡ | ፭፡ ወር፡ | |
| ተክለ፡ ሃይማኖት፡ | ፯፡ ወር፡ ፯፡ | ፲፯፻፸። |
| ሰሎሞን፡ | ፪፡ | ፲፯፻፸፯። |
| ተክለ፡ ጊዮርጊስ፡ | ፭፡ | ፲፯፻፸፱። |

## የመሳፍንቶች፡ ምስፍና፡ በጎንደር።

| | | |
|---|---|---|
| ታላቅ፡ ዓሊ፡ | ፬፡ | ፲፯፻፹፩። |
| ራስ፡ አሊጋዝ፡ | ፭፡ | ፲፯፻፹፭። |
| ራስ፡ አስራትና፡ ራስ፡ ወልደ፡ ገብርኤል። | ፯፡ | ፲፯፻፺፪። |
| ራስ፡ ጉግሳ፡ | ፳፯፡ | ፲፰፻፲፫። |
| ራስ፡ ይማም፡ | ፪፡ | ፲፰፻፳። |
| ራስ፡ ማርዬ፡ | ፫፡ | ፲፰፻፳፫። |
| ራስ፡ ዶሪ፡ | ፫፡ ወር፡ | |
| ራስ፡ ዓሊ፡ | ፳፪፡ | ፲፰፻፴፩። |
| አጼ፡ ቴዎድሮስ፡ | ፲፭፡ | ፲፰፻፶። |
| አጼ፡ ተክለ፡ ጊዮርጊስ፡ | ፫፡ | ፲፰፻፶፫። |
| አጼ፡ ዮሐንስ፡ | ፲፷፡ | ፲፰፻፷፩። |

## የቤት፡ ያዕቆብ፡ ዘር፡ መንግሥት፡ በሸዋ።

| | | |
|---|---|---|
| ነጋሢ፡ | ፯፡ | ከ፲፮፻፹፯—፲፮፻፺፫። |
| ስብስትያኖስ፡ ልጁ፡ | ፲፭፡ | ፲፮፻፺፭። |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ኣብዮ፡ ልጁ፡ | ፳፭፡ | ፲፯፻፴፯። |
| አምሃ፡ ኢየሱስ፡ ልጁ፡ | ፴፩፡ | ፲፯፻፷፯። |
| አስፋወሰን፡ ልጁ፡ | ፴፫፡ | ፲፰፻። |
| ወሰን፡ ሰገድ፡ ልጁ፡ | ፭፡ | ፲፰፻፭። |
| ሣህለ፡ ሥላሴ፡ ልጁ፡ | ፴፬፡ | ፲፰፻፴፱። |
| ኃይለ፡ መለኮት፡ ልጁ፡ | ፰፡ | ፲፰፻፵፯። |

ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ የኃይለ፡ መለኮት፡ ልጅ፡ ከ፯ሺ፫፻፶፯፡ — ፯ሺ፫፻፹፩፡ ፳፬፡ ዓመት፡ በሸዋ፡ ብቻ፡ ነገሡ፡ በ፯ሺ፫፻፹፪፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በ፲፰፻፹፪፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ በዘመነ፡ ማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡ በጥቅምት፡ ፳፭፡ ቀን፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ተብለው፡ በእንጦጦ፡ ማርያም፡ በአቡነ፡ ማቴዎስ፡ ተቀብተው፡ ነገሡ። በንጉሠ፡ ነገሥትነት፡ ፳፬፡ በንጉሥነት፡ ሸዋን፡ ብቻ፡ ፳፬፡ ድምሩ፡ ፵፰፡ ዓመት፡ ገዙ።

ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ፳፬፡ ከ፲፰፻፹፪። — ፲፱፻፮፡
ልጅ፡ ኢያሱ፡ ፫፡ ፲፱፻፱።

ንግሥተ፡ ነገሥታት፡ ዘውዲቱ፡ በ፯ሺ፬፻፱፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ በ፲፱፻፱፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ በመስከረም፡ ፳፪፡ ቀን፡ በባትም፡ አልጋ፡ ተቀመጡ፡ በየካቲት፡ ፬፡ ቀን፡ በደብረ፡ ጊዮርጊስ፡ በአቡነ፡ ማቴዎስ፡ እጅ፡ በዕለተ፡ እሁድ፡ ቅብዐ፡ መንግሥትን፡ ተቀብተው፡ ንግሥተ፡ ነገሥታት፡ ተብሉ።

www.ethiopianorthodox.org

# Table des Matières contenues dans ce volume –

፶፩።

## በዚች ፣ መጽሓፍ ፣ የሚገኙ ፣ ክፍሎች ።


| | |
|---|---|
| ነገደ፡ ኦሪት፡ | ገጽ፤ ፭። |
| ነገደ፡ ካም፡ | ፮። |
| ቅማንት፡ | ፯። |
| ወይጦ፡ | ፲። |
| ሽናሽ፡ | ፲፩። |
| ዮቅጣን፡ | ፲፬። |
| ትግሬ፡ | ፲፮። |
| አማራ፡ | ፲፯። |
| የእስራኤል፡ ሕዝብ፡ መምጣት፡ | ፳፩። |
| አገው፡ | ፳፮። |
| አበማክህ፡ | ፳፯። |
| ፈላሻ፡ | ፳፱። |
| ጋፋት፡ | ፴፩። |
| ጋላ፡ | ፴፫። |
| የቦረን፡ ልጆች፡ | ፴፮። |
| አፍሬያ፡ | ፴፯። |
| እስላም፡ | ፵፩። |
| ወረሴህ፡ | ፵፫። |
| ጉራጌ፡ | ፵፯። |
| ደርለደር፡ ያሉ፡ ሕዝብ፡ | ፵፰። |
| ከሀረርጌ፡ እስከ፡ ምጥዋ፡ ያለ፡ ሕዝብ፡ | ፵፰። |
| የሐረርጌ፡ ሕዝብ፡ | ፵፱። |
| የኢትዮጵያ፡ ወሰንና፡ ደግ፡ አገር፡ እንደነበረች፡ | ፶፩። |
| ከልደት፡ ወዲህ፡ የነገሡ፡ ነገሥታት፡ | ፶፫። |


www.ethiopianorthodox.org